ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ጥቅምት 13 ቀን 2005 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 61 | ዋጋው፡- 6 ብር

## “ስልጣን ከታጋይ እጅ መውጣቱ ጥሩ ነው”

**አቶ አስራት አብረሃ የአረና ለፍትህና ሉዓላዊነት ፓርቲ /አረና/ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ**

9



# መንግስት በመምህራን ላይ የበቀል በትሩን አሳረፈ

ባለፈው አመት የመጋቢት ወር ለመምህራን ተጨምሯል ከተባለው የደሞዝ ስኬል ማሻሻያ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ስራ የማቆም ውሳኔ ማሳለፋቸውና ይህንኑ መተግበራቸው አይዘነጋም፡፡ መንግስት አስተማሪዎቹን አነሳስተዋል ካላቸው መምህራን ውስጥ ስድስት ያህሉን ከስራ ገበታቸው በማፈናቀል ለሚበዙት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፡፡

በያዝነው አመት መጀመሪያ ላይ ለአምስት ቀናት የትምህርት ጥራት ፓኬጅን በማስመልከት ውይይት ተደርጎ ነበር፡፡ በውይይቱ ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ አስተማሪዎች ወደ ስራቸው ከተመለሱ ጥቂት ቀናት በኋላ ያልጠበቁት ነገር እንደገጠማቸው ስማቸውን መግለጽ ያልፈቀዱት መምህራን ይናገራሉ፡፡ 120 የሚደርሱ ነባር መምህራን ያለ ፍላጎታቸውና ያለ ማህበራቸው ተሳትፎ ወደ ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲዘዋወሩ ተደርገዋል፡፡ የዝውውራቸውን ምክንያት በመግለጽ የደረሳቸው አንድ ገጽ ወረቀት ዝውውሩ “ለተሻለ ስራና አገልግሎታቸውን ለማቃናት” ስለመሆኑ የምትገልጽ ናት፡፡ ነገር ግን በዝውውሩ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉ መምህራን በመጀመሪያ በነበሩባቸው ትምህርት ቤቶች ከተማሪዎቻቸው ጋር ጥሩ ግኑኙነት የመሰረቱና የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ባበርከቱት አስተዋእጾ በየጊዜው የምስጋና እና የምስክር ወረቀቶች የተሰጣቸው ናቸው፡፡ መምህራኑ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስተምሩ የነበረ ሲሆን በአዲሱ ዝውውር ከደረጃቸው ዝቅ ተደርገው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲያስተምሩ ተደርገዋል፡፡ ዝውውሩ በትምህርት ሚኒስትርና በመምህራን የውስጥ ደንብ መሠረት የተከናወነ አለመሆኑን የሚያወሱት መምህራኑ “አንድ መምህር ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ሊዘዋወር የሚችለው በመምህሩ ጥያቄ፣ ከሚሰራበት ትምህርት ቤት ጋር በመነጋገርና በመምህራን ማህበሩ እውቅና ነው፡፡ነገር ግን የአሁኑ ዝውውር ያለ መምህሩ ጠያቂነትና ያለ ምንም አይነት ምክክር የተደረገ በመሆኑ ህገወጥ ነው” ይላሉ፡፡

በ2004 ለመምህራኑ የደሞዝ ስኬል ማሻሻያ ተደርጓል መባሉን በመቃወም ድምጻቸውን አሰምተው ከነበሩ የኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት መምህራን መካከል 10ሩ እንዲሁም በወንድራድ ትምህርት ቤት የመብት ጥያቄ ካነሱ መምህራን አራቱ በዝውውሩ ከቦታቸው በመነሳታቸው ለተጨማሪ የትራንስፖርት ወጪ ተዳርገዋል፡፡ ዝውውሩን የበቀል እርምጃ በማድረግ እንደሚመለከቱት የሚጠቅሱት መምህራኑ ለሚመለከተው አካል ቢያመለክቱም ከዚህ የከፋ ነገር ሊደርስባቸው እንደሚችል እንደተነገራቸው በሀዘን ስሜት ይጠቅሳሉ፡፡

## ኦህዴድ ለአራት ለመሰንጠቅ ጫፍ ደርሷል

7

## የቃሊቲና ቂሊንጦ ወህኒ ቤቶች ገመና

14

## እኛ ነጋሲ ስንላቸው እርሳቸው “ሌጋሲ” እያሉ እስከመቼ?

አቤ ቶኪቻው

5

## ከሰለሞን ወደ ሮብአም እየመጣን እንዳይሆን ?

“. . . አባቴ በአለንጋ ገርፏችሁ ነበር፥ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ”

12

## የኃይለ ማርያም ወርቃማ ጠጠሮች

6

## በፍራቻ የሚነጥፍ ብዕርም ሆነ በአፈና የሚንበረከክ የትግል ማንነት የለንም!

4

## የትልቅ ህዝብ ትንሽ ድርጅት - ኦህዴድ

2

# የትልቅ ህዝብ ትንሽ ድርጅት - ኦህዴድ



ሰለሞን ስዩም
Era4st@yahoo.com

**ነገር ግን ምንም አይነት ድርጅቱን የማጠናከር እድል ቢገጥመውም የኦህዴድ አንጋፋ አመራር በጠቅላላ የህወሓት ምርኮኛ መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡ በመሆኑም አቶ መለስ ይህንን የኦህዴድ "ነፃ ነኝ" መንፈስ ለመደርመስ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ አባዱላ የኦህዴድ ምክር ቤት እንኳ ሳያውቅ ለፌዴራል ም/ቤት እንዲወዳደሩ ተደረገ፡**

ቡርኬ አያኔ የኦህዴድን ጉዳይ ከሚከታተሉ ሰዎች ተርታ ናት፡፡ ነገር ግን ሰዎች ኦህዴድንና የኦሮሞን ህዝብ በተምታታ ሁኔታ አንዱን በአንዱ እየወከሉ መናገራቸው ያናድዳታል፡፡ ቡርኬ ‹‹ብዙ ወዳጆቼ ኦህዴድን መተቸት ቀላል ነው ይሉኛል፡፡ እኔ ግን መተቸት እየከበደኝ ነው፡፡ ኦህዴድ አባ ዱላ አሊያም ሽፈራው ጃርሶን መተቸት የኦሮሞ ህዝብን እንደመተቸት ተደርጎ እንዲወሰድለት ይፈልጋል፡፡›› ሲትል ትናገራለች፡፡

ህወሓት የኦሮሞ ህዝብን ‹‹እወክላለሁ›› የሚለውን ኦህዴድ፣ በዱላ የኦሮሞ ህዝብ ላይ ስለመጫኑ ማረጋገጥ ቀላል ነገር ነው፡፡ በአናቱም የክልሉን መንግስት ከመጋረጃ ጀርባ የሚመሩ ባለሙሉ ስልጣን "አምባሳደሮች" ይመድብ ነበር፡፡ በርግጥ አንድ የቀድሞ የኦህዴድ አመራር ይህንን ከህወሓት ለመማር በፍቃዳቸው የሚያደርጉት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ህወሓትም ተግባሩን ከራሱ አንፃር ረኸርም እድሜ ላላስቆጠረው ኦህዴድ ልምድ አካፋይ የሚሆን ሰው መመደቡ እንደሆነ ቢናገርም እንደ ሀሜት ይነገር የነበረው የህወሓት ሁሉንም የግንባሩን ድርጅቶች የመቆጣጠር ስልት በጊዜ ሂደት ግልፅ እየሆነ መጣ፡፡

የኢህአዴግ አድራጊ ፈጣሪ የሆነው ህወሓት፣ በግንባር ድርጅቶቹ ላይ ትንሽ ጥርጣሬ ያደረበት እንደሆነ የክልል ፕሬዚዳንቶቻቸውን ጭምር ለመቀየር አያመነታም፡፡ ሌሎች አመራሮችን መቀያየር ቀላል ተግባሩ ነው፡፡ ምንም እንኳ የፌዴራሉ መንግስት በዚህ መልኩ ጣልቃ መግባት እንደማይችል ህገ መንግስቱ ቢደነግግም አቶ መለስ ዜናዊ ግን በጥሰቱ የተካኑ ነበሩ፡፡ በውጤቱም በኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ታሪክ ከሶማሌ ክልል ቀጥሎ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ፕሬዚዳንቶች የቀያየረው ክልል ኦሮሚያ ነው፡፡ ለዚህ ሰፊ ጣልቃ ገብነት ሌላው ምክንያት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የተሰጠው የመገንጠል ጥያቄ በስፋት የሚስተዋልባቸው ክልሎች መሆናቸው ነው፡፡ ይህ በየትኛውም ሰላማዊ መንገድ ቢጠየቅ ተግባራዊነቱ ለኤርትራ ብቻ ሆነ፡፡

ኢህአዴግ ግንባር ድርጅት ቢሆንም የህወሓት የበላይነት በትልቁ የሚታይበት ነበር፡፡ ከዚያ በመለስ የተሻለ የትጥቅ ትግል ታሪክ ያለው ብአዴን በሁለተኝነት ይከተላል፡፡ ኦህዴድ በራስ መተማመን መንፈሱ ከደኢህዴን ቢበልጥም ሌላ ዕንቅፋት ነበረበት፡፡ ኦህዴድ ግዙፉን የኦሮሞ ህዝብ በአማራው ላይ በነፍጠኛ ስም በማነሳሳት ለመግዛት ቢሞክርም በብአዴን በመልካም ጎኑ አልታየለትም፡፡ ብአዴን የአማራ ውክልና አለው ባይባልም በተላይ ኦነግ የአማራውን ህዝብ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በቅኝ ገዥነት በመሳሉ ኦህዴድ ያንኑ ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ በመሆኑም ከኦህዴድ የሚጠብቀውን ፉክክር አይወደውም፡፡ ከህወሓት ቀጥሎ በብአዴን የተያዘው የሁለተኝነት ቦታም ኦህዴድን ስለማያስደስተው ከብአዴኖቹ ቀና አስተያየት አልነበረውም፡፡ ህወሓት ግን ሁለቱን ‹‹ግላዲያተሮች›› እያጋጠመ በመሀል አናሳ ብሔር የተሰበሰቡበትን ደኢህዴንን እንደትሮይ ፈረስ ለመጋለብ ስራ ሰራ፡፡

ህወሓት የኦህዴድን ታማኝነት ለማረጋገጥ ከተጠቀማቸው መንገዶች አንዱ ድርጅቱ በተማሩ አባላት እንዳይጠናከር መከላከል ነበር፡፡ ህወሓት ከ1995 ዓ.ም በኋላ የኦህዴድን አንጋፋ አመራር ታማኝነት በትክክል ማረጋገጡን ካወቀ በኋላ ይበልጥ የተሻለ ታማኝ ያለውን ሰው ወደ መሾም ገባ፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ በዚህ ረገድ በተለይ ከኦነግ ጋር በምንም መልኩ የመደራደር ዕድል እንደሌላቸው በመገመት ምንም ቢሆን የህወሓት ታማኝ ሆነው እንደሚቆዩ የተማመኑት በአባዱላ ነበር፡፡

ለአቶ መለስ ዜናዊ እጅግ ታማኝ ከነበሩት ምድብ የመጀመሪያው ረድፍ ላይ የነበሩት ሜጀር ጀነራል አባዱላ ገመዳ በመለስ ዜናዊ ምርጫ ወደ ኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንትነት ሲመጡ ወታደራዊ ማዕረጋቸውን እንኳ በህግ አግባብ ለመተው ጊዜ አልተሰጣቸውም፡፡ ነገር ግን አቶ አባዱላ ገመዳ ወደ ኦሮሚያ ፕሬዚደንትነት የመጡበት ወቅት በአንፃራዊነት ከመለስ ዜናዊ ቁጥጥር ውጭ እንዲሰሩ አስችሏቸዋል፡፡ የመጀመሪያው አጋጣሚ በ1997 ዓ.ም የነበረውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ አቶ መለስ ዜናዊ የገቡበት ውጥረት አባዱላን ለመከታተል አፍታ የሚሰጣቸው አልነበረም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የኦነግ ቀንደኛ ጠላት እንደሆኑ የሚነገርላቸው አባዱላ ህወሓትን በመክዳት የሚጠረጠሩ አልነበረም፡፡

አቶ አባዱላ ገመዳ ይህንን አጋጣሚ ለመጠቀም ከተገበሯቸው ዘዴዎች አንዱ ከዚያ ቀደም በኦነግ ልባቸው ተሰልቦ የነበሩትን የክልሉን ወጣት ምሁራን በተለያየ መልኩ ወደ ድርጅታቸው ኦህዴድና የመንግስት መዋቅር መሳብ ነበር፡፡ ይህን ለመተግበር የመጀመሪያ እርምጃ ያደረጉት ከዚያ ቀደም ድርጅቱንና የመንግስት የኃላፊነት ቦታዎችን ሞልተው የቆዩ የልምድ ታጋዮችና ባለ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ አባላትን በነዚህ አዳዲስና ምሩቃን አባላት መተካት ነበር፡፡ ይህም ቢሆን በቀላሉ የተሳካ አልነበረም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ ከፍተኛ የውሎ አበል በመክፈል እንዲሁም ከምርቃት በኋላ ስለሚሰጣቸው የስራ ዕድል (ኃላፊነት) በመስበክ ተማሪዎቹን የአባልነት ፎርም ማስሞላት፣ ስልጠና መስጠትና ተያያዥ ጉዳዮችን ያካተተ ስራ መስራት ነበረባቸው፡፡

ከምረቃ በኋላም ቢሆን ቃል ለተገባላቸው ተማሪዎች ኃላፊነት ከመስጠት በተጨማሪ ከፍተኛ የገንዘብና የቦታ ስጦታዎች ለማባበያነት አውለዋል፡፡ አባዱላ በግላቸውም ቢሆን አባታዊነትን በመላበስ አዳዲሶቹን ቴክኖክራቶች ለማለማመድ ደክመዋል፡፡ በተጨማሪም አዲሶቹ ተቀጣሪዎች ቀደም ሲል የነበረውን የጭቆናና የደካማ አስተዳደር ውጤቶችን እያዩ ከመፀፀት በዘለለ የሆነ ነገር የሚያበረክቱበት አቅም ላይ በመድረሳቸው የማይጨበጥ/መንፈስ ከሆነባቸው የኦነግ ነገር ይልቅ ኦህዴድን ቢያገለግሉ ከሁለት ያጡ እንደማይሆኑ እርግጠኞች ሆኑ፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ ከድህረ ምርጫ 97 ሁከትና ውጥረት ስነቁ በኦሮሚያ አንድ ‹‹ጥሩ አባት›› (The Good Father) ተፈጥረዋል፡፡ ከእንግዲህ ችግሮችን ለመፍታት፣ ለትልቁም ለትንሹም አቤቱታ አቶ መለስ ዜናዊ ጋ መሄድ እያቆመ ነው፡፡ አንደኛ የፕሬዚደንትነት ዘመናቸው እንኳ ሳያልቅ አባ ዱላ በኦሮሚያ ገነኑ፡፡ አባ ዱላን እንጂ መለስ ዜናዊን የሚያስታውስ በኦሮሚያ ምድር ሲጠፋ ‹‹ የናቁት ያስረግዛል›› ሆኖ አረፈው ነገሩ፡፡

ነገር ግን ምንም አይነት ድርጅቱን የማጠናከር እድል ቢገጥመውም የኦህዴድ አንጋፋ አመራር በጠቅላላ የህወሓት ምርኮኛ መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡ በመሆኑም አቶ መለስ ይህንን የኦህዴድ "ነፃ ነኝ" መንፈስ ለመደርመስ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ አባዱላ የኦህዴድ ምክር ቤት እንኳ ሳያውቅ ለፌዴራል ም/ቤት እንዲወዳደሩ ተደረገ፡፡ በመጨረሻም መጨረሻቸው ለማንም ሰው ሊሰጥ የሚችለው የአፈጉባኤነት ቦታ ሆነ፡፡ ቡርኬ ‹‹በርግጥ ይህ ሲሆን አባ ዱላ ከኦነግ ጋር ደመኛ የሆኑበትን ቀን ይረግማሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ በይሆኑ ኖሮ በክልል ያን ሁሉ ዝና አትርፈው ሳለ በአቶ መለስ ዜናዊ አፈ ጉባኤ ከሚሆኑ እንደ አልማዝ መኮ መኮብለል ይቀላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን እንኳን ሊኮበልሉ ቀርቶ እዚህም እያሉ አቶ መለስ ‹እምቢ ካላችሁ ኦነግን አምጥቼ ከነሱ ጋር እሰራለሁ› እያሉ እንደልጅ ያስበረግጓቸዋል›› ስትል ትዝብቷን ታስቀምጣለች፡፡

በርግጥ የአባዱላ በክልላቸው መወደድ ያሰጋቸው አቶ መለስ ዜናዊ ሌላ ሴራ ተጠቅመዋል፡፡ አባዱላ ከፍተኛ ሀብት በማካበት በሙስና እንዲዘፈቁ ቢያንስ በዝምታ አበረታቷቸው፡፡ በተጨማሪም የህዝብን ሀብት የኦነግ አባላት ለነበሩት እንዲሁም የኦነግ ነገር ለሚያማልላቸው አዲሶቹ ምልምሎችና ሹመኞች በመበተን በሙስና የተነሳ ግዑዝ ፖለቲከኛ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ባለበት የሚረግጥ አንዳች የለም፤ አሁን አቶ መለስ ዜናዊ የሉም፤ አባዱላም በሙስና ለደረሰባቸው ትችት ሂስ ውጠዋል፡፡ ከንግዲህ እንደጀማሪ ፖለቲከኛ መናገር እስኪዳዳቸው ድረስ በራስ መተማመን አዳብረዋል፡፡ በመሆኑም ኦህዴድ ድጋሚ ከአባ ዱላ ጀርባ ለመሆን ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ለዚህ የሚጠቀሱ ምክንያቶች፤

አንደኛ አባዱላ ኦሮሚያ እያሉ ከነበራቸው ክብር አንፃር የተሻለ ኃላፊነት ለማግኘት በፌዴራል መንግስት የተወካዮች ምክር ቤት ለመመረጥ መወሰናቸውን መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህ እቅዳቸው በተጻራሪ አፈጉባኤ በመሆናቸው ክፉኛ በሽቀዋል፡፡ ነገር ግን ለዚህ የዳረጓቸው ዋነኛው ሰው ዛሬ የሉም፡፡ ለዚህ የዳረጋቸው ሌላው ድርጊት ሀብት የማጋበስ ነበር፡፡ ይህን ድርጊት ዛሬ ሂስ ውጠውበታል፡፡ በመሆኑም አባዱላ በቆዩባቸው የስልጣን ዘመናቸው ሁሉ በጤና መታወክ በአግባቡ መስራት ካልቻሉት የወቅቱ የክልሉ ፕሬዚደንት አቶ አለማየሁ አቶምሳ የመተማመኛ ድምፅ እንዲያጡ ኢ-ኦፌሴላዊ ዘመቻ ከጀመሩ መቆየታቸው ይነገራል፡፡ አቶ አባዱላ ለጀመሩት ዘመቻ ስኬት የተለያዩ ቁልፍ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡

አቶ አለማየሁን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚደንት ሆነው እንዲሾሙ ለማድረግ ከ120 በላይ የሹመቱ ተቃዋሚዎችን ያሳሰሩትና ያስባረሩት አቶ መለስ ዛሬ የሉም፡፡ በወቅቱ የአግአዚ ኮማንዶዎች በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ዘልቀው በመግባት ነበር 120ዎቹን አመራሮች አንቀው የወሰዷቸው፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ አቶ አለማየሁ አቶምሳን ወደ ኦሮሚያ ፕሬዚዳንትነት ሲያመጧቸው የአባዱላን ሙሰኝነት ለመከላከል እንደነበር ለማሳመኛነት ተጠቅመዋል፡፡ የስልጣናቸውን ጊዜያት በህመም የተነሳ ቢሮ መሆን ባይችሉም እንኳ ከመንበራቸው እንዲነቃነቁ አልፈቀዱም፡፡ አሁን ግን የአባዱላን አውሎ ንፋስ ችሎ መንበሩ ላይ የሚያቆያቸውን ሰው ያጡት አቶ አለማየሁ በክብር ስልጣናቸውን ለመልቀቅ እንደተስማሙ የውስጥ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡ ባይስማሙ እንኳ መፈንቅለ ስልጣን እንደሚደረግባቸው መገመት አይከፋም፡፡ ለዚህ የሚሆኑ ምክንያቶች፡-

አንደኛ አቶ አለማየሁ በበኩላቸው ፕሬዚደንት ከሆኑበት የክልሉ የፖለቲካ አካላት ጋር ገባ ወጣ ካሉባቸው ያለፉት ሁለት አመታት የዘለለ ቁርኝት አልነበራቸውም፡፡ ይባስ ደግሞ ይህቺኑ ጊዜም ቢሆን በህመም ሲሰቃዩ ስለነበር ደንበኞች/ደጋፊዎች በማፍራቱ ረገድ ጊዜያቸውን በአግባቡ አልተጠቀሙበትም፡፡ በተጨማሪም አባዱላ በተለይ ድህረ 97 ድርጅቱን ለተቀላቀሉት አባላት ያስለመዱትን የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ በግልባጩ ግን ከትንታኔ ብቃታቸው በተሻለ በሙስና ላይ ያላቸው ፅኑ አቋም ብቸኛው ደጀናቸው ነው፡፡

ሁለተኛ በአባዱላ የፕሬዚደንትነት ዘመን ኦሮሚያ ከምን ጊዜውም በላይ ለውጦችን አስመዝግባለች፡፡ ይህ በስንት መከራ ከኦነግ መንፈስ ተነጥቀው በተገኙ ወጣት የፓርቲው አባላት እንዲሁም ሌሎች ቢሮክራቶች ዘንድ ከፍተኛ ክብር አሰጥቷቸዋል፡፡ ካለፉት ሁለት አመታት ክፍተት ጋር ሲነፃፀር የአባዱላ ወደ ኦህዴድ ሊቀመንበርነትና የኦሮሚያ ፕሬዚደንትነት መመለስ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን ፓርቲው አምኗል፡፡

ሦስተኛው ህወሓት በክልሉ ሲያደርግ የነበረው ጣልቃ ገብነት የፈጠረው እልህና ቁጪትን ነው፡፡ ይህ በተለይ አንጋፋ የተባሉ የክልሉ አመራሮችን ማዋረድ የማያቆመው ህወሓትን ለመከላከል ብቸኛው መፍትሄ አንድነት በመፍጠር መቆም መሆኑን ኦህዴድ በከፊልም ቢሆን ዘግይቶ የተረዳ ይመስላል፡፡ ይህ ስለመሆኑ ደግሞ ኦህዴድ የኢህአዴግን ስብሰባ ቀድሞና ተከትሎ ባደረጋቸው አስቸኳይ ስብሰባዎች የታየ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ክስተት ድህረ 97 ድርጅቱን የተቀላቀሉትና ባብዛኛው በመካከለኛ አመራር ደረጃ ያሉት ወጣቶች አሁን አጎብዳጅ ናቸው ለተባሉት አንጋፋ አመራሮች የእግር እሳት መሆናቸው ነው፡፡ ኦህዴድ በኢህአዴግ ውስጥ የተሰጠው ቦታ የወረደ መሆኑን የተመለከቱት እነዚህ የመካከለኛ ደረጃ አመራሮች ይህ ህወሓት ለአንጋፋዎቹ አመራር ካለው ንቀት እንደሚመነጭ ተረድተዋል፡፡ አመራሩም በህወሓትና በነዚህ የራሱ መካከለኛ አመራር መካከል የቡሄ ድፎ ይመስል በሁለት በኩል እሳት ይነድበታል፡፡ ወጣቶቹ ግን የአሁኑ ሹመት ቢያልፍም እንኳ ከ6 ወር በኋላ በሚደረገው የኢህአዴግ መደበኛ ጉባኤ ላይ አቅማቸውን አደራጅተው ለመገኘት ስራ ለመስራት ያሰቡ ይመስላል፡፡

በቅርቡ የኦህዴድን ሊቀመንበር ለመምረጥ በተከናወነው ስብሰባ ወቅት አባዱላ የመጀመሪያው ዕጩ ሆነው ቢጠቆሙም ‹‹በገለልተኛ ታዛቢነት›› የተገኘው ህወሓት ግን ስራውን መስራት ጀመረ፡፡ አባዱላ የፌዴራል መንግስት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ እንደመሆናቸው መጠን ለእጩነት መቅረብ እንደማይችሉ አሳሰቡ፡፡ በነሐሴው ወር የአዳማ ከተማ ስብሰባ ህወሓቶች ለረጅም ጊዜ ሲያዘጋጇቸው የነበሩትን ወ/ሮ አስቴር ማሞ እንዲመረጡ ግፊት አደረጉ፡፡ ኦህዴዶች ግን ከታሪካቸው በተቃራኒ ለህወሓት ባለማጎብደድ ከአባ ዱላ ሌላ ሰው በዕጩነት ለማስመዝገብ ካለመፍቀዳቸውም በላይ ለአስቴር እጅግ ዝቅተኛ ድምፅ በመስጠት አንድነታቸውን አሳዩ፡፡

ህወሓት አባዱላ እንዳይጠቆሙ ካነሷቸው ምክንያቶች አባዱላ በትጥቅ ትግል ተሳታፊ በመሆናቸው ለክልል ፕሬዚደንትነታቸው መምረጥ የለባቸውም የሚል ቢሆንም ለራሳቸው ክልል ግን የትጥቅ ትግሉ ተሳታፊ የነበሩትን አባይ ወልዱን ለመምረጥ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ ኦህዴዶቹ ይህቺን ምክንያት በማግኘታቸው አባዱላ ወደ መንበራቸው እንዲመለሱ በሙሉ ልባቸው ተከራከሩ፡፡ ነገር ግን የፀረ ኦህዴድ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የሚመሩት አቶ በረከት ችግሩን ከኦነግ ጋር ለማያያዝ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ ዋና ምክንያታቸው ደግሞ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ
ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡
ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነው፡፡ ማንኛውም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

ዋና አዘጋጅ፡- ነብዩ ኃይሉ
አድራሻ፡- ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10
የቤት ቁ. 320
ኢሜይል፡-nebiyuhailu@gmail.com

አዘጋጆች፡- ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል
ሰለሞን ስዩም

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን

አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ደረጀ መላኩ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትልና ስርጭት፡-
ወንድወሰን ክንፈ
0911-65 46 69
አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ
አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07
የቤት ቁ. አዲስ
አታሚ፡-ለቡ ኮን ህትመት ኃ/የ/የግ/ማህበር
አድራሻ፡-ቂርቆስ ክ/ከ ቀበሌ 13/14
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-
01 11249659 - 0923 50 45 75
09 22 11 17 62 -0926 81 46 81
09 23 11 93 74 - 09 13 05 69 42
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

## ርእሰ አንቀጽ

# በፍራቻ የሚነጥፍ ብዕርም ሆነ በአፈና የሚንበረከክ የትግል ማንነት የለንም!

ኢህአዴግ ከአቶ መለስ ሞት በኋላ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር አስቀምጧል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን አዲሱም ሰው የሚቿን ጠቅላይ ሚኒስትር ዱካ የሚከተሉ፣ መለስ የጀመሩትን አፈና የሚያስቀጥሉ፣በመለስ የሙት መንፈስ የሚመሩ በመሆናቸው አሁንም በኢትዮጵያችን አንጻራዊ የሚባል እንኳ ለውጥ ለማየት አልቻልንም፡፡

በተለይም "አዲሱ" መንግስት ስርዓቱን የሚተቹ ጋዜጦችን ከአደባባይ በማጥፋት የሀገሪቱን የፕሬስ ነፃነት ጉዞ ክፉኛ ወደኋላ መመለሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን የሚያስከትል መሆኑን ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡

የአቶ መለስ ሞት ይፋ ከመሆኑ አስቀድሞ ፍትህ ጋዜጣ እንዲሁም የጠ/ሚኒስትሩ ሞት በመንግስት ይፋ ከተደረገ በኋላ ደግሞ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ከህግ አግባብ ውጪ እንዳይታተሙ እቀባ ተጥሎባቸዋል፡፡ ይህ እቀባ በሀገራችን ኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት እና የመደራጀት መብት ቦታ እንዲኖራቸው አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት እንደማይፈልግ በማያወላዳ ሁኔታ በተግባር የገለፀበት ነው፡፡

ይህን አይነቱን ስርአት የሚሸከም ጫንቃ እንደሌለን በተግባር የመግለፅ ኃላፊነትም ሆነ ግዴታ እንዳለብን እንረዳለን፡፡ ስለሆነም ስርዓቱ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ደንታ ቢስ መሆኑ የትግል መንፈስን የሚያጠናክር እንጂ ተስፋ አስቆራጭ ሊሆን እንደማይችል በተለያዩ ሰላማዊ የመብት ማስከበሪያ ትግሎች ለኢህአዴግ ልናረጋግጥለት ይገባል፡፡

መለስ ዜናዊ የገነቡት አፋኝ ስርዓት ከሰውየው ጋር ቢቀበር የነፃነት ናፋቂ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ምኞት ነበር፡፡ ሆኖም የመለስ ሞት የመንግስቱን ስልታዊ አምባገነንነት ቀመር በማሳጣቱ አሁን ያሉት አንባገነኖች ያፈጠጠና ያገጠጠ የአፈና ተግባር ውስጥ ገብተዋል፡፡

በጋዜጣችን የሚንፀባረቁት የነፃነት ጥያቄዎች የህዝብ ናቸው፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን በማፈን የህዝብን የለውጥ ፍላጐት ማፈን እንደማይቻል ስርአቱ በሚገባው ቋንቋ ሊነገረው ይገባል የምንለውም ለዚሁ ነው፡፡ ራሱ የሚለውን እንደገደል ማሚቶ የሚያስተጋቡ አድርባይነትን ዋንኛ ተግባራቸው ያደረጉና ከስርአቱ በተለያየ ደረጃ የሚጠቀሙ ሆድአደር የመገናኛ ብዙሃንን በመደገፍ፤ በአንፃሩ ለህዝብ አማራጭ በመሆን በስርዓቱ ላይ ትችት የሚያሰሙትን መርጦ ማፈንና ማዳከም ኢህአዴግ ለሚመራው መንግስት አደገኛ ውጤት እንደሚኖረው መገንዘብ ያስፈልጋል ፡፡

በሀገራችን ለተረገጡት መብቶች እንዲከበሩ ሁነኛው መፍትሄ ኢትዮጵያን በአፈና ቀንበር ስር ያደረገውን አምባገነን ስርዓት ማስወገድ እንደሆነ እናምናለን፡፡ የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ አሳታሚ የሆነው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በሚያስተባብራቸው ሰላማዊ የትግል አቅጣጫዎች በመሳተፍ ሁሉን አቀፍ የመብት ማስከበር ትግል ማድረግ አማራጭ የለውም፡፡

እንደሚታወቀው ጋዜጣችን ለህዝብ ስታቀርባቸው በነበሩት መረጃዎች ተወዳጅ ለመሆን የበቃችው የአንድ አመት እድሜዋን በቅጡ ሳትደፍን ነበር፡፡ ጋዜጣዋ በህትመት ላይ የቆየችባቸው እነዚህ ወራት ግን ለጋዜጣዋ ባልደረቦች ፈታኝ ጊዜያት ነበሩ፤ የመንግስት የደህንነት አባላትና ማንነታቸው የማይታወቅ ግለሰቦች የተለያዩ ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎችን ያለማቋረጥ ሲያደርሱባቸው ቆይተዋል፡፡

በተለይ የአቶ መለስ ሞት ውስጥ ውስጡን መሰማት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ጋዜጠኞቻችን ላይ የሚደርሱት ዛቻና ማስፈራሪያዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የጋዜጣዋ አዘጋጆች ላይ የግድያ ዛቻ የደረሰ ሲሆን የእገታ ሙከራም ተደርጓል፡፡ ይህ ድርጊት የሚያሳየው በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነት ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነት በጋዜጣ መልክ እንዳትታተም በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በኩል በመንግስት ብትታቀብም፣ ጋዜጣዋን ለአንባቢያን ለማድረስ ያደረግነው ጥረት ሰምሮ እነሆ ዛሬ በመጽሄት መልክ ለህዝብ ደርሳለች፡፡

አምባገነኖቹ ባለስልጣናት ልብገዝተው ጋዜጣችን ህትመቷ እንዲቀጥል እንዲያደርጉ ዛሬም ጥሪያችንን እናቅርባለን፡፡ ሆኖም መብታችንን ለማስከበር የተለያዩ ሰላማዊ ትግሎችን በማድረግ ጋዜጣችን አንባቢዎቿ እጅ ውስጥ የምትገባበትን መንገድ ሁሉ ለመፍጠር እንተጋለን፡፡

አሁንም ለመንግስት የምንገልፀው በፍራቻ የሚነጥፍ ብዕርም ሆነ በአፈና የሚንበረከክ ማንነት እንደሌለን ነው፡፡

ጋዜጣችንን "ፍኖተ ነፃነት" ብለናታል "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው::





# እኛ ነጋሲ ስንላቸው እርሳቸው "ሌጋሲ" እያሉ እስከመቼ?



አቤ ቶኪቻው

ትላንት ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ (በቅንፍም ቢያንስ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር በመጥራቴ እኔም ደሳለኝ…!) በፓርላማ ጥያቄዎችን ለመመለስ ለመጀመሪያ ግዜ ቀርበው ነበር፡፡ በዚህ የመጀመሪያው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርላማ ላይ በርካታ ዋና ዋና የሚቹ ወዳጆች አልተገኙም ነበር አሉ፡፡ ወ/ሮ አዜብም ካልተገኙት ውስጥ ናቸው፡፡ ወ/ሮዋ ድሮ በሚቹ ጊዜ ስብሰባ ሲቀሩ ከፓርላማው ስብሰባ መልስ ለቀጣዩ መጂሊስ ስብሰባ ቤቱን ሞቅ ሞቅ አድርገው ሊጠብቋቸው ነው የቀሩት ብለን እናስብ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ምን ሆነው ቀሩ…? ብለን ስንጠይቅ "ላልተወሰነ ጊዜ ቤተመንግስቱን አምነው ርቀው አይሄዱም አሉ!" የሚል ሽሙጥ እናገኛለን፡፡

የሆነው ሆኖ ግን አቶ ሃይለማሪያም በትላንቱ ፓርላማ መለስን ሆነው ሲተውኑ ነው የተመለከትናቸው፡፡ እንደውም አንድ ወዳጄ ሲናገር እንደሰማሁት አፈ ጉባኤው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሲያስተዋውቁ "ቀጥሎ እንደ መለስ ዜናዊ ሆነው እንዲተውኑልን አቶ አርቲስት ሃይለማሪያም ደሳለኝን እጋብዛለሁ!" ማለት ነበረባቸው ብሎኛል፡፡፡

የምር ግን ሰውዬው መለስን ለመምሰል በሚያድርጉት ጥረት ራሳቸውንም መለስንም ሳይሆኑ መቅረታቸው ነው ያሳዘነኝ፡፡

እርግጥ ነው እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጊዜ ልንሰጣቸው ይገባል፡፡ ሲሉ መክረዋል፡፡ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉም በዛሬው ፓርላማ ሰውዬው እንዲህ ማድረጋቸው በርካታ የኢህአዴግ አባላትን ያማልልላቸዋል፡፡ እናም አማራጭ አልነበራቸውም ብለዋል፡፡
እኔ ግን ያልገባኝ ኢህአዴግ መስተፋቅሩን ያሰራባቸው ግለሰቦች (በቅንፍም መስተፋቅር ተብሎ የተገለፀው አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች መሆናቸው ይታወቅ) እነዚህ ግለሰቦች "ጀግና አይሞትም" ብለው ያሉን እኮ ለለቅሶ ማድመቂያ መስሎኝ ነበር፡፡
የምራቸውን መለስ አልሞቱም ብለው ነው የሚያስቡት እንዴ!? ግራ ነውኮ የሚያጋባው፡፡ ትላንት የኢቲቪው ተመስገን አቶ ሃይለማሪያም ቃል በቃል ያሉት ብሎ ስለ አቶ መለስ የተናገረው ነገር በእውነቱ ከሆነ ተስፋ አስቆራጭ ነው፡፡

"የአቶ መለስን "ራዕይ" ማስፈፀም ላይ እና መለስን ዘላለም መዘከር ላይ ድርድር የለም፡፡" "ወ…ይ ድርድር የለም!" ጋዜጠኛው የንግግሩ ዜማ ውስጥ እኮ አሁንም መለስ ይምሩን የሚል ነው የሚመስለው!
የስታድየም ልጆች እስከዚህም የማይደግፉት ክለብ ጨዋታ ላይ ተጫዋቾች የማይሆን አይነት ተደጋጋሚ ስህተት ሲሰሩ ሲያዩ "ምን አገባን እኛ ምን አገባን!" ሲሉ ያዜማሉ… ምክንያቱም ክለቦች እንዲህ ስህተት ከደጋገሙ ከስታድየም የፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ዝቅ ብለው ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን የጃንሜዳ ጨዋታ ይወርዳሉና የሚመቻቸውን እነርሱ ያውቃሉ ለማለት ነው፡፡

ኢህአዴግ ነብሴ ነብሱ እስክትወጣ መለስ መለስ ብሎ የመለስን መንገድ እከተላለሁ ካለ መጨረሻው ከመሬት ስር ነው፡፡ እርሳቸው ያሉት ከመሬት ስርነውና! የምመራው በአስከሬን ነው ያለ ሰው አስከሬን ከመሆን ውጪ ምርጫ የለውም! ለራሳቸው "ባትሪ ሎው" ብለው ለጥ ያሉ ሰውዬ እንደምን ለእኛ ሃይል ይሆናሉ!?

አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ እኛ ነጋሲ ስንላቸው እርሳቸው "ሌጋሲ" እያሉ እስከመቼ እንደሚቆዩ እንጃ! ሶስቱንም አመት እንዲሁ ከሆኑ "ምናገባን እኛ ምናገባን!" ብለን እናዜምላቸዋለን! ጥሩ ነው እንደውም በሚቀጥለው ምርጫ ኢህአዴግ አንደኛ ዲቪዚዮንን ቢያየው ለልምዱም መልካም ነው!

## መሳቂያው ፓርላማ

ያው እንደሚታወቀው የፓርላማ አባላቱ የምክር ቤት ስብሰባ ለማድረግ ሲሄዱ ወረፋ አይጠብቁ እንጂ የሆነ ኮሜዲ ፊልም ለመታደም ሲኒማ ቤት እንደሚገቡ አድርገው እንደሚያስቡት የታወቀ ነው፡፡ ይሄ ካልታወቀ ትልቅ የመረጃ ክፍተት አለ ማለት ነው!

በተለይ በአቶ መለስ አስተዳደር ጊዜ አባላቱ በሙሉ ለሳቅ ለጨዋታ ተሰነዳድተው ነበር ምክር ቤት የሚመጡት፡፡ (ዛሬ ማን ያጫውተን ዛሬ ማን ያጫውተን….! አረ ማን ያስቀን አረ ማን ያስቀን!) ብለን እናስነካው እንዴ!?

የምር ግን ኢትዮጵያ በየ ነገስታቱ አለቃ ገብረሃናን የመሰሉ አጫዋቾች ቤተ መንግስት አካባቢ አይጠፉም ነበር፡፡ በመንጌ ጊዜም አቶ ቆምጬ አምባው የአለቃ ገብረሃናን ያህል የኢሰፓ አባላትን እና የዘመኑን ሰው በድርጊታቸው ያዝናኑት ነበር ሲባል ሰምተናል፡፡

በአቶ መለስ ጊዜ ግን ገብረሃናውም፣ ቆምጬ አምባውም፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም እርሳቸው ነበሩ! (እዚች ጋ አንድ ማስታወቂያ አለኝ… "አቶ መለስን እስቲ ተዋቸው" ለምትሉኝ ወዳጆቼ በሙሉ እንደዚህ አትብሉኝ! አልተዋቸውም፡፡ ጋሽ ሃይሌ እንዳሉትም የሳቸው ነገር የምንተወው አይደለም እየተወሱ እየተዘከሩ ለዘላለም ይኖራሉ! በዚህ ላይ ድርድር የለም) ሳቄ ሳይመጣ ከቅንፍ ልውጣ!

እና አቶ መለስ ከጠቅላይነታቸው በተጨማሪ የምክር ቤቱ አጫዋችም ነበሩ!

ታድያ ለሃያ አንድ አመታት ጨዋታ የለመደ ምክር ቤት ዛሬ ማን ያጫውተው? ዛሬ ማን ያስቀው? አቶ ሃይለማሪያም እንደሆኑ ከአቶ መለስ እስካሁን በቅጡ የኮረጁት ቁጣቸውን ብቻ ነው፡፡

ሰሞኑን የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ "ሀገራችን ኢትዮጵያን እና ህዝቧን እግዚአብሔር በበረከቱ ይጎብኝ" ብለው ሲናገሩ ሙሉ የምክር ቤት አባላቱ ከት ብለው ሲስቁ የሚያሳይ ቪዲዮ የብዙዎች መነጋገሪያ ሆኖ አይተናል፡፡

በርግጠኝነት የፓርላማ አባላቱን ምን አሳቃችሁ? ብለን ብንጠይቃቸው "… እና ፓርላማ የመጣነው ምን ልናደርግ ነው!?|" ብለው ባይመልሱ ውርድ ከራሴ!

እውነታቸውን ነው ገና ለገና ዛሬ እርሳቸው ሞቱ ተብሎ ፓርላማው ሳይሳቅበት ይዋል እንዴ!?

የሚገርመው ግን "መለስ አልሞቱም" የሚለው ንግግር ያላሳቃቸው ተበካዮቻችን (በቅንፍ የታይፕ ግድፈት አለ የምትሉ እያስተካከላችሁ እንድታነቡ መፈቀዱን እገልፃለሁ!) "እግዚአብሔር ይባርከን!" ሲባል ከት ብለው መሳቃቸው ነው፡፡ ይሄኔ ነው መሳቀቅ ያለችው ማን ነበረች!? ለማንኛውም ፓርላማውን መሳቂያ አድርገውት የሄዱት እሳቸው ናቸው እና አዎ መላቀቅ የለም "ዘላለም እንደተዘከሩ" ይኖራሉ!

# የኃይለ ማርያም ወርቃማ ጠጠሮች

ዳዊት ሰለሞን

ኢትዮጵያን ላለፉት 21 ዓመታት በፕሬዘዳንትነትና በጠቅላይ ሚኒስትርነት የመሩት አቶ መለስ ዜናዊ ይህችን አለም በሞት መሰናበታቸውን ተከትሎ በእርሳቸው ልክ የተሰፋና የተዘጋጀ ተተኪ የለኝም በማለት ኑዛዜ ሲያሰማን የነበረው ገዢ ፓርቲ በመጨረሻው መጨረሻ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ ኃይለ ማርያምን የፓርቲው ሊቀመንበርና የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በማድረግ መሾሙን ካሳወቀ ሦስት ሳምንታት ተቆጥረዋል፡፡ የቀድሞው የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ መምህርና ዲን ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በመለስ ወንበር መቀመጣቸውን ተከትሎ ባደረጓቸው ንግግሮች የመለስን ውርስ ለማስቀጠል እንደሚሰሩ አስምረዋል፡፡ የደቡቡ ልጅ የአገሪቱን ከፍተኛ የስልጣን እርከን መቆናጠጣቸውን በመንተራስ ተገዢው ህዝብ ተስፋን በሌላ በኩል ስጋት የተሞላበትን ሃሳቡን ሲገልጥ ቆይቷል፡፡ በእኔ እይታ ግን ኃይለማርያም የመለስን ውርስ ለማስቀጠል ወገቤን አጥብቂያለሁ ከማለታቸው ባሻገር እንደ መለስ ይህችን አገር ሊመሯት እንደማይችሉ ይሰማኛል፡፡ ሰውዬው ከፓርላማውና ለቬኦኤ የእንግሊዝኛ ዘጋቢ ፒተር ላይን ከሰጡት አስተያየት በተቃራኒው አንድ ቀን ወደ ልባቸው በመመለስ የራሳቸውን አሻራ በተቀመጡበት መንበር ለማኖር ይከጅሉ ይሆናል፡፡ ያንግዜም የመለስን ምስል በማውረድ የራሳቸውን ምስል ለማኖር ይደፍሩ ይሆናል፡፡

ኃይለ ማርያም የፌስቡክ ደምበኞች እንደሚናገሩት "ኃይለ መለስ" በመሆን እቀጥላለሁ ካሉ ግን ለመሆን የሚፈልጉትን መለስን ሲፈልጉ የተፈቀደላቸው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ዘመን አልቆ አቶ በረከት ስምኦን እንደተናገሩት በአዲስ ካድሬ ሊተኩ ይችላሉ፡፡ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በእኔ እምነት እስከ ቀጣዩ አገር አቀፍ ምርጫ ድረስ በርዕሰ መስተዳድርነት በሚያደርጉት ቆይታ በትምህርት የቀሰሙትን እውቀት፣ በተራው ህዝብ ዘንድ በመኖር ያካበቱትን ማህበራዊ መስተጋብርና የህዝብ ልጅነት የሆነ ሳጥን ውስጥ በመክተት ታጋዩን መለስ ከመቃብር ለማውጣት ይጥራሉ በማለት ለማመን እቸገራለሁ፡፡ ተስፈኛ የሆንኩባቸውና ኃይለ ማርያም የመለስን ውርስ ለማስቀጠል ይቸገሩባቸዋል በማለት የማስባቸውን ነጥቦች በወርቃማ ጠጠርነት ፈርጂያቸዋለሁ፡፡ እነዚህን ጠጠሮች በአግባቡ ከኮሮጂቸው በማውጣት ለመጠቀም የሚጥሩ ከሆነም እንደ ጎልያድ የገዘፉ ችግሮቻችንን ሊያስወግዱ ይችላሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የጠጠሮቹ ወርቅነት በራሱ የሚዘይደው መላ አይኖርም፡፡ ወርቅ ተሸክሞ የተሸከሙትን ወርቅ ዋጋ አለማወቅ ደግሞ ያሳፍራል፡፡ ምን ይህ ብቻ እንደ ጅልነትም ሊያስቆጥር ይችላል፡፡ የኃይለማርያም የወርቅ ጠጠሮች ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን ጎላ ያሉትን ለመዘርዘር ልሞክር፡፡



## ጦረኛ አለመሆናቸው

አገርን የሚያስተዳድር መሪ ስለ ወታደራዊ ሳይንስ እውቀት ያለው ቢሆን ተመራጭ ነው፡፡ ነገር ግን የግዴታ ጦረኛ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት በወታደራዊ ሳይንስ ከሰለጠኑ ባለሞያተኞችና የጦር ሰዎች ምክር በማግኘት መጠቀም ይችላል፡፡ ተደጋግሞ ሲገለጽ እንደነበረው መለስ በወጣትነት እድሜያቸው የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን በማቋረጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ደደቢት በረሃ በመመሸግ እስከ አፍንጫው የታጠቀውን ደርግን ተፋልመዋል፡፡ ወታደሩ መለስ በለስ ቀንቷቸው በ1983 ምኒልክ ቤተመንግስት ገብተዋል፡፡ ነፍጠኛው ኢህአዴግ ስልጣኑን ከተረከበ በኋላ በምርጫ ስም በመማልና በመገዘት በብረት ሳይሆን በድምጽ ካርድ እንደሚያምን ሲነገረንና ሲያስነግረን ቆይቷል፡፡ ነገር ግን መለስ በምርጫ ዴሞክራሲ የሚያምኑ አልነበሩም፡፡ ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን የ1997ቱ ምርጫ ነው፡፡ ህዝቡ ድምጼን ተቀማሁ በማለት ተቃውሞውን ለማሳየት አደባባይ ሲወጣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አጥልቀውት የነበረውን ካባ በማውለቅ እውነተኛ ማንነታቸውን ገልጠዋል፡፡ በብቸኝነት በተቆጣጠሩት ሚዲያም ተቃዋሚዎቻቸውን "በሚፈልጉት ቋንቋ እናናግራቸዋለን" በማለት ፎክረዋል፡፡

መለስ በሰላሙ ጊዜ በህዝብ ድምጽ የሚያምኑ፣ በፈተና ወቅት ደግሞ ጦረኛ ነበሩ፡፡ ኃይለማርያም ግን የሚበዛ ጊዜያቸውን ከቀለም ጋር በመታገል ያሳለፉ የቀለም ሰው ናቸው፡፡ የእርሳቸው መሳሪያም "ጠመኔ" ብቻ ነበረች፡፡ እውቀትን በእውቀት፣ አንድን አስተሳሰብ በሌላ እንዴት መርታት እንደሚቻል ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ በአመራርነታቸው ዘመን ከተቃዋሚዎቻቸውና ከሚዲያው ለሚቀርብባቸው ወቀሳዎችና ትችቶች ምላሻቸውን ወደ እስር ቤት ማጋዝና በጥይት መደብደብን እንደማያደርጉት እምነት አለኝ፡፡ መለስ እንዲህ አይነት ፈተናዎችን ይሻገሩ የነበሩት በሰለጠነ መንገድ አልነበረም፡፡ የመለስን ውርስ እንዲቀጥል አደርጋለሁ የሚሉን ኃይለማርያም ከማንነታቸው በማፈንገጥ ወታደራዊ ርምጃ ለመውሰድ የሚሞክሩ ከሆነ የመጀመሪያዋ ወርቃማ ጠጠር ዋጋዋን ታጣለች፡፡

ኃ/ማርያም ሞጋች ሃሳቦችን በብረት በጠነከር ጡንቻ መደፍጠጥ እንደማይቻል በአካዳሚክ ቆይታቸው ያካበቱት ልምድ እንዳስተማራቸው አስባለሁ፡፡ በአንፃሩ መለስ የስልጣናቸውን ዕድሜ የሚያራዝም የመሰላቸውን እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ እንደማይሉ በምርጫ 97 ወደ ከተሞች ብረት ለበስ ታንኮችን በማስገባት አሳይተውናል፡፡ በዚህ በኩል በመለስና በኃ/ማርያም መካከል ትልቅ ልዩነት እንዲሚኖር ይሰማኛል፡፡ መለስ ተቃዋሚዎቻቸውንና የነፃ ሚዲያ አባላትን በማሰር፣ ከአገር እንዲወጡ በማድረግና በማሸማቀቅ ተለይተው የሚታወቁ ነበሩ፡፡ ኃ/ማርያም ህዝባዊ መነቃነቆች ተፈጥረው እንደ 97 አይነት የተቃውሞ ስሜቶች ወደ አደባባይ ገንፍለው ቢወጡ ጣት ለመቁረጥ ወታደሮችን ያሰማራሉ በማለት ለማመን የሚቸገሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ እርግጥ ነው አለማችን የውትድርና ልምድ በሌላቸው ዕድሜያቸውን በሙሉ በትምህርት ገበታ ባሳለፉ መሪዎች ተመርታ ታውቃለች፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቀለሜዋ የሚባሉ መሪዎች ከወታደሮቹ ባልተናነሰ አምባገነን በመሆን መታየታቸው አልቀረም፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወደ አራት ኪሎ የገቡ መሪዎቻችን ወታደር ቀመስ ነበሩ፡፡ ለዚህ መንግስቱንና መለስን ማስታወስ የሚበቃ ይመስለኛል፡፡ ከሁለቱ ወታደር መሪዎቻችን በኋላ ኃ/ማርያም ጥይት ሳይተኩሱና በጦር ግምባር ሳይውሉ ስልጣን በማግኘት የመጀመሪያው ናቸው፡፡ ወታደሮቹ ገዢዎቻችን በሚመሩት ስርዓት ላይ ለሚነሱ ተቃውሞዎች ይሰጧቸው የነበሩትን ብረት ለበስ ምላሾች በቅርበት የሚያውቁት ሃይማኖተኛው ኃይለ ማርያም የተለየ አማራጭ ይዘው በመቅረብ ከቀደሙት የሰለጠኑ መሆናቸውን ያሳዩናል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

## የአካዳሚክ ነፃነትን ይፈቅዳሉ

በዘመነ ኃይለ ሥላሴ የዩኒቨርስቲ ተማሪ የነበሩት መለስ የንጉሱ ስርዓት በተማሪዎች ነፃነት ላይ ምን ያህል ጣልቃ ገብ እንደነበር በመገንዘብ ተቃውሟቸውን ከአቻዎቻቸው ጋር ያሰሙ ነበር፡፡ የወቅቱ ተማሪ በዋናነት "መሬት ለአራሹ" በሚለው ህዝባዊ ጥያቄው ጎልቶ ይጠቀስ የነበረ ቢሆንም የአካዳሚክ ነፃነትን ስለመጠየቁ የተለያዩ መዛግብቶች ያወሳሉ፡፡ መለስ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ግን በነፃነት ተማሪው የሚመራውን መሪ፣ የሚወክለውን ማህበርና ሃሳቡን በነፃነት የሚያንሸራሽርባቸው መድረኮች እንዳይፈጠሩ ተፈጥረውም እንዳይሳለብቱ በነጭ ለባሾቻቸው አማካኝነት ያለመተካት ሰርተዋል፡፡ ዛሬ ዩኒቨርስቲዎቻችን ህዝባዊ ጥያቄዎች የማይነሱባቸው በጎሳ በመቧደን እርስ በርስ የሚደባደቡ፣ ለሚመገቡት ምግብ ለወጥ ካልሆነ በስተቀር ስለሌላው ግድ የማይሰጣቸው ተማሪዎች አፍርተዋል፡፡ መለስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በማሰብ ከዚህ ቀደም 41 የሚደርሱ ታላላቅ የዩኒቨርስቲ ዶክተሮችንና ፕሮፌሰሮችን ከስራ ገበታቸው እንዲፈናቀሉ አድርገዋል፡፡ ኃይለ ማርያም በዩኒቨርስቲ ከመማርና ከማስተማር አልፈው እስከ መሪነት ደርሰዋል፡፡ የስራ ዘመናቸውን የሚበዛ ጊዜ ያሳለፉትም በዩኒቨርስቲ ስራ በመሆኑ ለተማሪዎችና ለአስተማሪዎች የአካዳሚክ ነፃነትን መፍጠር ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡ መምህር የተማሪዎቹ የቀለም አባት እንደመሆኑ መጠንም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በመለስ ተጨፍልቆ የቆየውን የአካዳሚክ ነፃነትን ይፈቅዳሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችላቸው ወርቃማ ጠጠርም በኮሮጂቸው እንዲያዙ ይሰማኛል፡፡

## ፈሪሃ እግዚአብሄር

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ከአቡነ ጳውሎስ መስቀል ሲሳለሙ ከዚህ ቀደም በማየታችን ኦርቶዶክስ ናቸው ብለን እንመን፡፡ ነገር ግን ስልጣን ላይ በቆዩባቸው አመታት፣ የእግዚአብሄርን ስም ሲጠሩ ወይም እግዚአብሄርን እንደሚፈሩ በንግግሮቻቸውና በስራቸው አላሳዩንም፡፡ በዚህም መለስ እግዚአብሄርን በማወቅ የሚገኘውን ስብዕና እንዳጡት ይሰማኛል፡፡

ኃይለ ማርያም ወደ ስልጣን ከመምጣታቸው አስቀድሞ ከአንድ የሃይማኖት መጽሄት ጋር ባደረጉት ሰፋ ያለ ቃለምልልስ "እግዚአብሄር ለመሪዎቻችን ቅን ልቦና እንዲሰጥ እጸልያለሁ፡፡" ብለው ነበር፡፡ ህዝብን ለመምራት ቅን ልቦና እንደሚያሻ በታሪካችን የተሸከምናቸው መሪዎች የዚህ ልብ ማጣታቸው እንዳሰቃየን በመገንዘብ ኃይለማርያም ሲጸልዩ ቆይተዋል፡፡ አሁን ግን ተራቸው ደርሶ መንበሩን ተረክበዋል፡፡ ሌሎች እግዚአብሄር ቅን ልቦና ያለውን መሪ በዙፋኑ በማስቀመጡ በመደሰት ጸሎታቸውን ወደ ምስጋና እንዲለወጡ ማድረግ ግን ከኃይለማርያም ይጠበቃል፡፡ የዚህች አገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተግዳሮቶች እኔ ብቻ አውቃለሁ በሚል ፈሊጥ ሊፈቱ እንደማይችሉ እነ መለስ ጥሩ ምስክር ናቸው፡፡ ተቃዋሚዎችን በማሰር በመግደልና የህዝብ ልሳኖችን በማፈን ህዝባዊ ጥያቄዎችን መደፍጠጥ አይቻልም፡፡ ኃይለ ማርያም የሚያነቡት መጽሀፍ ቅዱስ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ እስካልተለወጠ ድረስ "መምህርና ጌታ" በማለት ደቀመዛሙርቱ የሚጠሩት የእግዚአብሄር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ በማድረግ የአገልጋዮቹን እግር አጥቧል፡፡ በዚህም መሪነት አገልጋይነት መሆኑን አሳይቷል፡፡ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከታላቁ መምህር የተማሩ ከሆኑም ኢትዮጵያችን በደም አበላ የሚያጥባት ሳይሆን ድህነቷን፣ ሰቆቃዋን፣ የፖለቲከኞቿን መለያየትና እያንዣበበባት ከሚገኘው የጎሳና የሃይማኖት ነውጥ የሚታደጋትን አገልጋይ መሪ አግኝታለች ማለት ይሆናል፡፡

## ቀለም የገባቸው ቀዳማይ እመቤት ማግኘታቸው

መለስ በዚህ በኩል እድለኛ አልነበሩም ወይዘሮ አዜብ መስፍን በለቅሶው ሰሞን እንደነገሩን ከመለስ ጋር የሚተዋወቁት ከልጅነታቸው አንስቶ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ነው፡፡ ተጋዳላይና ተጋዳላይት በነበሩበት ዘመን ሁለቱ ተጋዳላዮች በፍቅራቸው ጸንተው እስከ መጨረሻው መቆየት መቻላቸው ያስወድሳቸዋል (በእርግጥ አዜብ ከመለስ በፊት ሌላ አፍቃሪ እንደነበራቸው ይነገርላቸዋል፡፡) አዜብ ከዚህ ቀደም ለአንድ የውጪ ሚዲያ በሰነዘሩት አስተያየት "የመለስ ጭንቅላት ትልቅ ነው ፣ ከስልጣኑ ተነስቶ ጡረታ ቢወጣ በእርሱ ጭንቅላት የትኛውንም አይነት ስራ እየሰራን መኖር እንችላለን፡፡" ብለው ነበር፡፡ የቀድሞዋ ቀዳማዊት እመቤት በባለቤታቸው ጭንቅላት እንጂ በራሳቸው የሚመኩ አልነበሩም፡፡ አዜብ ከባለቤታቸው ጋር ወደ አራት ኪሎ ቤተመንግስት ከገቡ በኋላም በትምህርት ለመግፋት አልፈቀዱም፡፡ ከዚህ ይልቅ በተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ይፋዊ ባልሆነ መንገድ በመሰማራት ብዙ ነጋዴዎችን ከጨዋታ ውጪ ስለማድረጋቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የቀድሞው የኢህአዴግ ባለሚል ተስፋዬ ገብረ አብ ከአገር ከተሰደደ በኋላ ይፋ ባደረጋቸው መረጃዎቹ አማካኝነት አዜብ በጫት ንግድ የባለቤታቸውን ስልጣን ተገን በማድረግ መክበራቸውን ማጋለጡ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በተቃራኒው በመኝታ ቤታቸው የሚያገኟቸው ወይዘሮ እንደ እርሳቸው ሁሉ ለትምህርት ትልቅ ዋጋ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ወይዘሮዋ በአፍሪካ ህብረት ውስጥ መስራት መቻላቸው የአገራችንን ብሎም የአህጉራችንን ችግሮች ምን እንደሆኑ እንዲመላከቱ አድርጓቸዋል፡፡ ኃይለማርያም በስልጣን ዘመናቸው የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎችና መሰናክሎች ከባለቤታቸው ጋር በመማከር የሴት ብልሃትን በማግኘት ስኬትን መጨበጥ ይችላሉ፡፡ "ከእያንዳንዱ ታላቅና ስኬታማ መሪ በስተጀርባ ታላቅ ሴት አለች፡፡" የሚለውም ዘመን ተሻጋሪ ብሂልም ከአፄ ምኒልክ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በኃይለማርያም የስራ ዘመን ይታያል የሚል እምነት አለኝ፡፡የደቡቡ ሰው ከላይ ለመጠቃቀስ የሞከርኳቸውን ወርቃማ ጠጠሮች በመጠቀም ተስፋዬን ይሞሉታል በማለት እጠብቃለሁ፡፡ እናንተስ. . .

# ኦህዴድ ለአራት ለመሰንጠቅ ጫፍ ደርሷል

ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት በኋላ በተደጋጋሚ ተሰብስቦ መግባባት ያልቻለው ኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦህዴድ/ በአራት ቡድን ተከፍሎ ውዝግብ ውስጥ እንደገባ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ፡፡
ለፓርቲው ቅርበት ያላቸው የፍኖተ ነፃነት ታማኝ የዜና ምንጮች እንደሚያረጋግጡት ኦህዴድ በአሁኑ ጊዜ በግልጽ ለአራት ቡድኖች ተከፍሏል፡፡ ቡድኖቹ 1ኛ ኦህዴድ- መለስ 2ኛ ኦህዴድ-አባዱላ 3ኛ ኦህዴድ- ኦሮሚያ 4ኛ ኦህዴድ- አድፋጭ በሚል የሚታወቁ ሲሆን፣ የተካረረ ፍጥጫ ውስጥ የመግባት አዝማሚያ ታይቶባቸዋል፡፡

ምንጮቻችን እንደሚያስረዱት "ኦህዴድ-ለመለስ" የሚባለው ቡድን ከህውሓት ጋር የቀረበ ግንኙነት ያለውና "ከመለስ ራዕይ ውጪ ምንም ዓይነት ሐሳብና እንቅስቃሴ ማድረግ የለብንም" የሚል ክርክር በማንሳት ኦህዴድ ውስጥ የተጀመረውን የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ እንዲጠፋ ጥረት የሚያደርግ ነው፡፡ "የመለስ እቅድ" ሳንሸራርፍ መተግበር አለብን ብለው ራሳቸውን ያሳመኑት የዚህ ቡድን አባላት ከዚህ ሐሳብ ውጪ የሚያስቡትን እንደ ከሐዲ የሚፈርጁ ናቸው፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ ሙክታር ከዲር፣ ኩማ ደመቅሳ፣ አስቴር ማሞና ዘላለም ጀማነህ እንደሚገኙበት የዜናው ምንጮች ተቁመዋል፡፡

ሁለተኛው ቡድን "ኦህዴድ -አባዱላ" የሚባል ሲሆን የአባዱላን ወደ ክልሉ ፕሬዝዳንትነት ለመመለስ ከመጣር ውጪ ከመጀመሪያው ቡድን ጋር መሰረታዊ የሀሳብ ልዩነት የለውም፡፡ "ኦህዴድ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ከኢህአዴግ/ህውሓት የሚሰጠውን መመሪያ እየተቀበለና እያስፈፀመ መቀጠል አለበት፡፡ በድርጅት ስምና በኦሮሞ ህዝብ ስም የፌደራል ስልጣን መጠየቅ ከድርጅቱ ዓላማ መውጣት ነው፡፡ ክልላችንን እስካስተዳደርን ድረስ ለፌዴራል ሥልጣን መጨነቅ የለብንም፡፡ ከህውሓት ጋር ግጭት ውስጥ መግባት የለብንም" የሚሉት የቡድኑ አባላት ውስጥ ውስጡን ግን ኦህዴድ በፌደራል ደረጃ ተገቢውን ውክልና ባለማግኘቱ የተነሳውን ተዋውሞ በተወሰነ ደረጃ የመቀበል አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ አፈጉባኤ አባዱላ ገመዳና የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር አለማየሁ ተገኑ እንደሚገኙበት ምንጮቻችን አስረድተዋል፡፡


ኦህዴድ- ኦሮሚያ የሚባለው ቡድን "ኦህዴድ የኦሮሞን ህዝብ መብትና ጥቅም ማስከበር አለበት፡፡ ድርጅቱ ከህውሃት ጥገኝነት መላቀቅ ያለበት ሰዓት ላይ ደርሷል፡፡ ድርጅቱ በአማራ ህዝብ ላይ እንዲከተል የሚደረገው የጥላቻና የብቀላ ፖለቲካ ማቆም አለበት፡፡" የሚል ሀሳብ ይዞ የሚሟገት ሲሆን የኦህዴድ ተጠሪነትም ሆነ አገልግሎት ለአሮሞ ህዝብ ብቻ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ በድርጅቱ ውስጥ የህውሓት ተላላኪ የሆኑትን ግለሰቦች ከአመራርነት ማስወጣት አለብን፡፡ የሚል ጠንካራ አቋም የሚያራምድ ቡድን ነው፡፡ "የኦሮሞ ህዝብ በፌዴራል ደረጃ ተገቢውን ውክልና ማግኘት አለበት፡፡" የሚሉት የቡድኑ አባላት መካከለኛውንና ወጣት አመራሮችን ድጋፍ ማግኘት የቻሉ ሲሆን የድርጅቱን መካከለኛ ካድሬዎች ሀሳብ ወደ አመራሩ እዳመጡ ምንጮቻችን አስረድተዋል፡፡ ከመካከለኛውና ወጣት አመራሩ ውጭ አቶ አለማየሁ አቶምሳና አቶ ጁኔዲን ሳዶን ጨምሮ ሌሎች የድርጅቱ ጠንካራ አመራሮች በዚህ ቡድን ውስጥ እየተሰባሰቡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

አራተኛው ቡድን "ኦህዴድ- አድፋጭ" የሚባለው ሲሆን አቋማቸውን በግልፅ ያላወጡና ወደ አሸናፊው ቡድን ለመቀላቀል ያደፈጡ አባላትን የያዘ ቡድን እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የቡድኑ አባላት በተለያዩ ክርክሮች ላይ አቋም ወስደው ከመከራከርና ከመጋጨት ይልቅ እያንዳንዱን ጉዳይ አጉንብሰው ለማለፍ ሞክረዋል የሚባሉት በዚህ ቡድን አባላት የኦሮሚያ ም/ፕሬዝደንት አቶ አብዱላዚዝ ዮሱፍ፣ ግርማ ብሩ፣ የኦህዲድ መስራቹ ጌታቸው በዳኔን ያካተቱ መሆናቸውን ምንጮቻችን አብራርተዋል፡፡

ኦህዴድ በቅርቡ ማዕከላዊ ኮሚቴው ከሳምንት በላይ ስብሰባ ላይ ቆይቶ ስብሰባውን ቢያጠናቅቅም አሁንም ስብሰባው አዳማ ላይ ለመቀጠል ተገዷል፡፡ የአሁኑ ስብሰባ የዞንና የወረዳ አመራሮችን የየቢሮ ኃላፊና ም/ኃላፊዎችን ባካተተ መልኩ ተጀምሮአል፡፡ በከፍተኛ ሙስናና የአስተዳደራዊ በደል የሚታወቁት የከተማ ከንቲባዎች የወረዳና የዞን አመራሮች በዚህ ስብሰባ ተካተዋል፡፡ በየአካባቢያቸው በበርካታ ወንጀል የሚጠረጠሩት የአካባቢ ኃላፊዎች በግምገማ ላይ ይገኛሉ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት ኦህዴድ እንደ ድርጅት ለመቆም ወይም ለመሰነጣጠቅ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሷል ፡፡

# "ስልጣን ከታጋይ እጅ መውጣቱ ጥሩ ነው"

**የዛሬው እንግዳችን አቶ አስራት አብረሃ ይባላሉ፡፡የአረና ለፍትህና ሉዓላዊነት ፓርቲ /አረና/ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ናቸው፡፡ በአገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ከባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፡፡**



በኢህአዴግ በተለይም በህወሓት መካከል መከፋፈል ተፈጥሮአል ይባላል፡፡ ምናልባትም እርስዎ የተሻለ መረጃ ሊኖሮት ይችላል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ምን ይላሉ?

እውነት ነው እኔ ባለኝ መረጃ ህውሓት መግባባት አልቻለም፡፡ ሥራ አስፈፃሚው ተሰብስቦ መግባባት ባለመቻሉ ማእከላዊ ኮሚቴውን ጠርቷል፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው መግባባት ባለመቻሉ በመጨረሻ የተስማሙት ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ይወሰን የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ስለዚህ አሁን የሚጠበቀው ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡ አለመግባባት ብቻ ሳይሆን እስከመከፋፈል ሄደዋል፡፡

ሰሞኑን ኢህአዴግ ሊቀመንበሩንና ም/ሊቀመንበሩን መርጧል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ባለው ፖለቲካ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖር ይሆን?

ምርጫው ቢዘገይም የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ሊቀመንበሩ ከህወሓት ቢሆን ኖሮ ጥሩ አይሆንም ነበር፡፡ ህወሓት በኢህአዴግ ውስጥ ወሳኝ ሃይል ነው ፡፡ የቀሩት ድርጅቶች የይስሙላ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ የቀረፈ ነው፡፡ በተለይም ሥልጣኑ ከታጋይ እጅ መውጣቱም ሌላው ትልቅ ነገር ነው፡፡ ለተቃዋሚዎች ትርጉም አለው፡፡

ምንድነው ለተቃዋሚዎች የሚኖረው ትርጉም?

20 ዓመት ሙሉ የተቃዋሚ ፓርቲን እየመራ ለውጥ ማምጣት ያልቻለ መሪ ቦታውን መልቀቅ አለበት፡፡ ሰው በተፈጥሮው ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብም ያረጃል፡፡ አዲስ ሐሳብ አምጥቶ የሐሳብ የበላይነት አስመዝግቦ አዲስ የትግል ስልት ቀይሶ የለውጥ ኃይል አደራጅቶ ለውጥ ማምጣት አይችልም፡፡ ሁልጊዜ የሚመራው ለውጥ የሚያመጣ ኃይል ሳይሆን መግለጫ በማውጣት ተቀምጦ የሚቃወም ድርጅት ነው፡፡ ዛሬ የሚያስፈልገን ደግሞ ለ20 ዓመት እንዳየነው ያለ ድርጅት ሳይሆን መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ድርጅትና መሪ ነው፡፡

ሰሞኑን የህወሓት ም/ሊቀመንበርና የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ አባይ ወልዱ በትግርኛ ለሚተላለፍ የትግራይ ኤፍ ኤም እርቅ የለም በማለት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ አረና እርቅ ጠይቆ ነበር? እርቅ የለም ማለታቸውንስ እንዴትይመለከቱታል?

አቶ አባይ ያሉት እሱን ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህን እሾሆች በዲሞክራሲያዊ መንገድ ነቅለን እንጥላቸዋለን ሲሉም ሰምተናል፡፡ መንቀልንና ዲሞክራሲን ምን እንዳገናኘው አልገባኝም!! አቶ አባይ በጣም ተሳስተዋል፡፡ እኛ እርቅ አልጠየቅንም ምናልባትም አባሎቻቸው በፈጠሩባቸው ተጽእኖ የተናገሩት ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ በአገር አቀፍ ደረጃ ብሔራዊ እርቅ ያስፈልጋል ብለን እናምናለን፡፡ በ92 እንደነበረው ውስጣችን ገብተው ሊበጠብጡን ነውና በእርቅ ሰበብ ውስጣችን ሊገቡ ነው ብለው ስጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

ከአቶ መለስ ሞት ጋር ተያይዞ በአባሎቻችሁ ወይም በትግራይ ውስጥ በህዝብ ላይ የደረሰ ችግር ይኖር ይሆን?

አዎ በርካታ ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡ በመለስ ሞት ጨፍራችኋል፣ ዘፍናችኃል፣ ተደስታችኋል አላዘናችሁም ተብለው የታሰሩ አሉ፡፡ በተለይ በመቀሌ ከተማ በተደጋጋሚ እስር ተፈጽሟል፡፡ በዚህ ምክንያት ፓርቲያችን ለአባሎቹ አንድ መመሪያ አውርዷል፡፡ አሁን ያለው ውጥረት እስኪረግብ ድረስ በጊዜ እንዲገቡ፣ ህዝብ በሚበዛበት መንገድና ሥፍራ እንዲንቀሳቀሱና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አንድ የዩኒቨርስቲ መምህር በመለስ መሞት ተደስተሃል ተብሎ በመኪና ሊገጨት አሳደውት ከመንገድ ሸሽቶ በመውጣቱ አምልጧል፡፡ ይህ እንግዲህ እጅግ የሚያሳዝን ተግባር ነው፡፡

> **"በመለስ ሞት ጨፍራችኋል፣ ዘፍናችኃል፣ ተደስታችኋል አላዘናችሁም ተብለው የታሰሩ አሉ፡፡ በተለይ በመቀሌ ከተማ በተደጋጋሚ እስር ተፈጽሟል፡፡ በዚህ ምክንያት ፓርቲያችን ለአባሎቹ አንድ መመሪያ አውርዷል፡፡ አሁን ያለው ውጥረት እስኪረግብ ድረስ በጊዜ እንዲገቡ፣ ህዝብ በሚበዛበት መንገድና ሥፍራ እንዲንቀሳቀሱና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ አንድ የዩኒቨርስቲ መምህር በመለስ መሞት ተደስተሃል ተብሎ በመኪና ሊገጨት አሳደውት ከመንገድ ሸሽቶ በመውጣቱ አምልጧል፡፡ ይህ እንግዲህ እጅግ የሚያሳዝን ተግባር ነው፡፡**

ለ13 ቀን የተከናወነውን የሐዘን ቀን ተገቢ አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?

በህወሃት ወንድምህም ቢሞት ማልቀስ ክልክል ነበር፡፡ ሲያለቅስ የተገኘ ሰው ግለኝነት ያጠቃሃል ተብሎ ይገመገማል፡፡ ይህ ህጋቸው አቶ መለስ እስከሞቱበት ዕለት የተከበረ ነበር፡፡ በአቶ መለስ ሞት ግን ህጉ ተጥሷል፡፡ ራሳቸው ማልቀስ ብቻ ሳይሆን አስለቃሾችን ሰብስበውና ቀጥረው ደረት ሲያስመቱ ሰንብተዋል፡፡ ሐዘን በዘመቻ አከናውነዋል፡፡ እንደሰው አቶ መለስ መሞታቸው ያሳዝናል፡፡ የፈፀሙት የዘመቻ ሐዘን ግን ተገቢ ነው ብዬ አላስብም፡፡

ለምን እንዲህ የተደረገ ይመስልዎታል?

በለቅሶው ምክንያት የህዝብ ድጋፍ አለን ለማሰኘት ነው፡፡ በአገራችን ባህል እንኳን የምታውቀው ሰው ቀርቶ አይተኸው የማታውቀው መንገደኛ ቢሞትም ተሰብስቦ ወጥቶ መቅበር የተለመደ ነው፡፡ በለቅሶው ከተሳተፉ መካከል አንድ እናት ሲናገሩ እንደሰማሁት ልጄ ሥራ ባይገኝም በሰላም ውሎ ይመለሳል ማለታቸውን ሰምቻለሁ፡፡ ሌላዋ እናት ደግሞ ልጄ ምግብ መብላት የጀመረው አሁን ነው ብለዋል፡፡ ምን ማለት ነው?

የአቶ መለስ መሞትና የአቶ ኃ/ማርያም መተካት በኢህአዴግ ውስጥም ይሁን በመንግስት ሥራ ውስጥ የሚፈጥረው ነገር ምንድን ነው?

ኢህአዴግን እድልና ፈተና የሚገጥመው አሁን ነው፡፡ ኢህአዴግ ተስማምቶ መሄድ ከቻለ ጥሩ ነው፡፡ የራሱን የውስጥ ችግር ፈትቶ የተወሳሰበውን የአገሪቱን ፖለቲካ እየፈታ ሊሄድ ይችላል፡፡ መስማማት አቅቶት መናናቅ፣ አለመደማመጥና አለ መከባበር ከገጠመው ፈተና የከፋ ነው፡፡ አቶ ኃ/ማርያም ስብሰባ የመያዝና የመምራት አቅም አላቸው ብዬ አላስብም፡፡ ከዚህ በፊት አንድ የህወሓት ሰው በሌላ ተሹሞ ደብዳቤ ሲደርሰው ይህ ደግሞ ምንድነው ብሎ ወረቀቱን ቀዳዶ መጣሉን አውቃለሁ፡፡ መለስ በግሉ አምባገነን ነበር፡፡ ከአንድ አምባገነን አመራር እጅ የወጣ ስብስብ እንዴት ሆኖ ተረጋግቶ ዲሞክራት ሆኖ አብሮ ሊጓዝ ይችላል የሚለውን የምናየው ይሆናል፡፡

አቶ ኃ/ማርያም መከላከያውን፣ የደህንነት መዋቅሩንና የፖሊስ ኃይሉን መምራት ይችሉ ይሆን? የአገሪቱ ቁልፍ ቦታዎች የተያዘው በተለመደው ሁኔታ ነው፡፡ በአቶ ኃ/ማርያምና በእነዚህ መዋቅሮች መካከል ያለው ግንኙነት ህገ መንግስታዊ ብቻ ነው፡፡ አሁን የሚፈጠረው ጥያቄ ከህገ መንግስቱና ከልዩ ልዩ ግንኙነትና ትስስር የቱ ይበልጣል ነው?

ባለሥልጣናቱም መዋቅሩም ለህገ መንግስቱ ተገዢ ከሆኑ አቶ ኃ/ማርያም የሚቸገሩበት መንገድ ያለ አይመስለኝም፡፡ ከህገ መንግስቱ ጀርባ ያለው ልዩ ልዩ ግንኙነትና ትስስር ካሸነፈ ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ኢህአዴግ ሊቀመንበሩን ሳይመርጥና ጠ/ሚኒስትር ሳይሾም በሽግግር ወቅት ውስጥ 37 ጀነራል መሾም ለምን እንዳስፈለገ አነጋጋሪ ነው፡፡ ተሿሚዎቹ አምና ከጦሩ ከተሰናበቱት ጋር በዕድሜና በአገልግሎት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ነባር ታጋዮችን መሾም የተፈለገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ አቶ ኃ/ማርያም ደግሞ አገርን ተረክቦ ለመምራት አቅም የላቸውም ብለን መደምደም ባንችልም ብዙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ትግራይ ውስጥ ያለውን ፖለቲካዊ ድባብ እንዴት ይገልፁታል?

ሰሞኑን የመቀሌ ኤፍ.ኤም ሬዲዮ ሲናገር እንደሰማሁት 3ኛውን ወያኔ እንጀምራለን ብሎአል፡፡ ዘመኑ የወያኔ ወይም የአብዮት አይደለም፣ ወቅቱ ስለሰላማዊ ትግል የሚወራበት ነው፡፡ ስለ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር የሚሰበክበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት

ወደ ገፅ 11

# የኢህአዴግ የስህተት ጉዞና የተቃዋሚው ያለመስማማት ጉዞ



ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ

ኢህአዴግ ሀገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከዚች ሰዓድረስ ከሰራቸው መልካም ስራ ይልቅ ያጠፋው ጥፋቶች በይበልጥ ጎልተው ይታያሉ፡፡ የሀገሪቱን ህገመንግስት በመጣስም ቢሆን ኢህአዴግ ከሚከሳቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች በበለጠ ደረጃ ራሱ ሲጥስ ይስተዋላል፡፡ ኢህአዴግ ከግልጽነቱ ይልቅ ግልጽነት የጎደለው አሰራሩ ይበልጣል፡፡ ለዚህም አቶ በረከት ስምኦን ስለድርጅቱ ግልጽ አለመሆን በራሳቸው አንደበት ከቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር መታመም ጋር ተያይዞ ለህዝብ አለመነገሩ ከድርጅቱ ግልጽነት ማጣት እንደሆነ እንደመልካም ነገር አስረድተዋል፡፡

ኢህአዴግ ከቀድሞው የኢትዮጵያ ጠ/ሚ/ር ሞት ጋር በተያያዘ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ለማዳመጥ እንደቻልነው አብዛኛው የተጀመሩትንና የተሰሩትን ሁሉ እርሳቸው መሆናቸውን ሲናገሩ እንደነበረ ሰምተናል፡፡ ይህንን ሪፖርት ላዳመጠ ሰው ካድሬዎች ሁሉ ምንም ሥራ የመስራት፣ የማቀድና የማስወሰን አቅም እንደሌላቸው እና ላለፉት 21 ዓመታት ሙሉ ምንም ስራ እንዳልሰሩ በራሳቸው አንደበት መስክረዋል፡፡ በዚህም እስካሁን ድረስ የቀድሞው ጠ/ሚ/ር በነበሩ ጊዜ ሁሉ ካድሬዎቹ ሳይሰሩ ደመወዝ ይከፈላቸው ስለነበረ ያለአግባብ ይበሉ የነበረውን ደመወዝ ቢመልሱ መልካም ነበር፡፡

ለነገሩ እነርሱ የቱንም ያህል ራሳቸውን አሳንሰው ቢገልጹ ያቀዱትን ዓላማ ከማሳካት አንጻር ግባቸውን መተዋል፡፡ በወቅቱ እነርሱ ህዝቡንና ተቃዋሚውን በማዘናጋት የኢህአዴግን ህልውና ማስቀጠል ዋና ዓላማቸው ስለነበረ በዚህ መልኩ ህዝቡን በማዘናጋቱ ረገድ ትልቅ እመርታ ኣሳይተዋል፡፡ ምንም እንኳ እኛ ተቃዋሚዎች ቀድሞውንም እነርሱ ሳይደክሙ የተዘናጋን ቢሆንም ቅሉ፤ በዚህ መልኩ እያንዳንዱ ካድሬ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ድርጅቱን አሁን ባለው መልኩ እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡ ድርጅቱ ባለበት ከቀጠለ ደግሞ ካድሬዎቹ ያለጠያቂ መቀጠል ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ህገመንግስቱ ጠ/ሚ/ሩን በተመለከተ ምንም እንዳይል በማድረግ ስህተት የተፈጸመ ቢመስልም ዋናው ዓላማ ግን የኢህአዴግን የበላይነት ከማስጠበቅ አንጻር ትልቅ ስራ ሰርቷል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው በተቃዋሚው በኩል የሚሰሩ ስህተቶች ተቃዋሚውን ከመጥቀም አንጻር ሳይሆን እርስ በርስ ከመጠፋፋት አንጻር እየሰሩ ስለነበረና አሁንም እየሰሩ ስለሆነ ለኢህአዴግ ሰፊ የመጫወቻ ሜዳ ያለተቃናቃኝ እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡ ይህ የተቃዋሚዎች የተሳሳተ አካሄድ ለኢህአዴግ ረጅም ዓመታት ያለተቀናቃኛኝ እንዲገዛ ከማድረጉ በተጨማሪ ወደፊትም በዚህ መልኩ ረዘም ላለ ዓመታት እንደማይገዛ ምንም ዋስትና የለም፡፡

ሌላው የኢህአዴግ ስህተት ከነበረው ውስጥ አንዱ ከህግ ውጭ የጠቅላይ ሚንስትሩን አስከሬን ሳይቀብር ለሁለት ሳምንት ያህል ማስቀመጡ ሲሆን በዚህ ስህተቱ ኢህአዴግ ብዙ ፕሮፓጋንዳ ሰርቶበታል፡፡ በርካታ ሰዎች ከእርሳቸው በቀር ሌላ ሰው እንዳልነበረ እንዲረዳ አድርጎ የምርጫ ቅስቀሳ አድርጎበታል፡፡ በጠባቧ የቴሌቪዥን ስክሪን ጥቂት ደጋፊና ካድሬዎችን ምስል በማሳየት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳዘነ በማስመሰል የፕሮፓጋንዳ ትርፍ ለማግኘት ሞክሯል፡፡ ዓለም አቀፍ ህብረተሰብንና አንዳንድ ተቃዋሚዎችን ሳይቀር አሳስቶበታል፡፡ ስህተትን ለትርፍ ይጠቀሙበታል ማለት ይህ ነው፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ስራው ትልቅ ትርፍ አት ርፎበታል ማለት ይቻላል፡፡ የሀገሬው ህዝብ ተቃዋሚዎችን እንዲታዘብ ሲያደርግ ኃያላኑ ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ጠንካራ ተቃዋሚ እንደሌለ እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል፡፡

በተቃዋሚው ጎራ ያሉት በአሁኑ ሰዓት ከመሰባሰብ ይልቅ አዳዲስ ፓርቲዎች እንደአሸን መፍላቱን ተያይዘውታል፡፡ ይህ የፓርቲዎች በየቀኑ እንደአሸን መፍላት አምባገነናዊ ስርዐቱ በሰፈነባት ሀገራችን ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ በሆኑት ሀገራት የኮበለሉት ሳይቀር የተጠናወታቸው በሽታ ነው፡፡ የተቃዋሚው ጎራ በራሱ የተከፋፈለ ሀሳብ ይዞ ይንቀሳቀሳል፡፡ ገሚሱ ያለውን መንግስት በመደገፍና ለአምባገነናዊ አገዛዙ ድጋፍ በመስጠት ተቃዋሚ የሚለውን ዓርማ በመሸከም ብቻ የህዝቡን መከራና ሰቆቃ ሲያባብሰው ይታያል፡፡ ገሚሱ ደግሞ በትክክል ይቃወማል፤ እርስ በርሱም ይቀዋወማል፡፡ በዚህም እርስ በርሱ ሲቀዋወም አንድ ዓላማና ግብ ቢኖውም አንዱ አንዱን የሚያጠፋ ስራ እየሰራ በተቃራኒው ገዢው መንግስት እንዳሻው እንዲሆን በማድረግ የህዝቡን የመከራ ጊዜ ያራዝማል፡፡

ጉንዳኖች ትንንሽ ነፍሳቶች ናቸው፡፡ ትልቁን ወንዝ ግን ተያይዘው ይሻገሩታል፡፡ ጉንዳኖች ወንዝ ሲሻገሩ አንዱ ጉንዳን አንዱን ጉንዳን ነክሶ በመያዝ እየተቀጣጠሉ ወንዙን መሻገር ይጀምሩና የመጀመሪያው ጉንዳን ወንዙን መሻገሩን ሲያውቅ ከወንዝ ወዲያ ማዶ ያለውን አፈር ወይም ቅጠል ነክሶ በመያዝ የልተሻገረውም እንዲሁ ይነክስና ድልድይ ይሰራሉ፡፡ ሌሎች ጉንዳኖች ከስር በተዘረጋው የጉንዳኖች ድልድይ በሰላም ይሻገራሉ፡፡ ድልድይ የሆኑት ጉንዳኖች ወንድሞቻቸው ከተሸገሩ በኋላ መሻገር ይጀምራሉ፡፡ ሁሉም ግን ወንዙን አይሻገሩም፡፡ ከተቃዋሚው ጎራ ድልድይ የሚሆን ያለ አይመስልም፡፡ ሁሉም መሻገር ይፈልጋል፡፡ አንዱ አንዱን አይዝም፡፡ ብቻ መሻገር ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ አንዱ አንዱን ይዞ ተያይዞ መሻገር ሳይሆን እያንዳንዱ በራሱ ብቻውን መሻገር ስለሚፈልግ እንዲሁ ባሉበት ይቀራሉ፡፡ አንዳንዶችም በጎርፍና በውሃው ሙላት ይወሰዳሉ፡፡

የሀገራችን የተቃዋሚዎች ያለመስማማት በሽታ እንደወረርሽኝ ከሀገር ቤት አልፎ በተሰደዱበት ሀገር ሁሉ መዘመቱ በእጅጉ አስገራሚ ነው፡፡ ታዋሚዎች ባለመስማማታቸው ይህን ሁሉ ዓመት ኪሳራ እንጂ ትርፍ ባያስገኝላቸውም ለትርፍ ቆም ብሎ ከማሰብ ይልቅ በኪሳራ መንቀሳቀሱን ተያይዘውታል፡፡ አንዳንዶቹ በእርግጥ ምን እንደሚቃወሙም ማወቁ ይከብዳል፡፡ እዚህ ሀገር ቤት ገዢው ፓርቲ የሚሰራውን በዘር የመከፋፈል ዘዴ እነርሱ በስደት ሀገር ሆነው ሲያራምዱት ይታያል፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ በእርግጥ ከገዥው ፓርቲ ስውር ካድሬዎች ተልዕኮ አይሆንም ብሎ መጠራጠር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም እርስ በርስ በዘር መከፋፈላችን ለአንድነታችን ገደል ነውና በዘር ተከፋፍለን የምንታገል ከሆነ እንዴት አንዱ አንዱን አምኖ አጠገቡ ሊቆም ይችላል፡፡ ስለዚህ ምናልባት ይህ ዓይነቱ አካሄድ ለተጨማሪ አመታት በአምባገነኖች ከመጋት ዉጪ ጥቅም የለውም፡፡

እኔ በአንዳንድ የፓልቶክ ውይይቶችና የውጭ ሀገር ሚዲያዎች መገንዘብ እንደቻልኩት ብዙዎች ስለሀገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ ግንዛቤ የላቸውም፡፡ ኢንፎርሜሽኑን የሚያቀብሏቸውን ሰዎች ማንነት መገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ያለበለዚያ እኛ ከአለመስማማት ወደ አለመስማማት በሄድን ቁጥር ተጠቃሚው ኢህአዴግና ኢህአዴግ ብቻ ይሆናል ባይ ነኝ፡፡

ለዚህ መፍትሄው ተቃዋሚዎች እንደጉንዳን ከውጭም ከውስጥም ያለነው እርስ በርስ መያያዝ እና ገዳም እንደሚደረገው ጎበዝ በጉልበቱ ሽማግሌና ደከማ በጸሎቱ እንደሚባለው በውጪ ያለው ዲያስፖራ በገንዘቡና በሀሳቡ በውጪው ዓለም ኃያላኑ በአምባገነኑ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳርፉ በማድረግ መተጋገዝ ሲሆን ሀገር ቤት ያለው በቀጥታ አቋምን በማስተካከል ህዝቡን በማደራጀት ወደፊት በመሄድ ማሸነፍ ይቻላል፡፡ አለበለዚያ እንደዚህ ዓይነት መንግስት የቀብርጥሶ ፓርቲ ብሎ በሀገር ቤት መሰረት የሌለው ፓርቲ ይዞ መሄዱ ለልጆች መጫወቻነት ከሚክቡት የእንቧይ ካብ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡

ሽንገላና የአፍ ወለምታን መከተል እስካልቆሙ ድረስ ውጤት ስለማይመጣ ዝም ብሎ መቀመጡ የተሸለ ነው፡፡





## የትልቅ ህዝብ ትንሽ . . . ከገጽ3 የዞረ

የኢህአዴግን ፕሮጀክት የተቃወሙት አባላት ራሳቸውን በኦነግነት ላላማስጠርጠር ፀጥ እንዲሉ ነበር፡፡

ወ/ሮ አስቴር ማሞ ኦህዴድ ኢህአዴግ ውስጥ ከሚወክላቸው ዘጠኝ የስራ አስፈፃሚ አባላት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ ነገር ግን የሴትዮዋን ፖለቲካዊ ተክለ ስብዕና ለማክበድ ኦህዴድ ሳይወክላቸው ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነሩ አቶ ወርቅነህ ገበየሁ ጋር በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባ እንዲገኙ አድርገዋቸዋል፡፡ ይህ ድርጊት ነሐሴ 2004 ዓ.ም በተካሄደው የመጀመሪያው የአዳማ ስብሰባ ወቅት የተካረረውን ልዩነት ለማስታረቅ ይጥሩ የነበሩ የኦህዴድ አባላትንም ጭምር ወደ ጠርዝ እንዲሄዱ እንዳስገደዳቸው ይነገራል፡፡

የኦህዴድ መካከለኛ አመራር ከምንም በላይ የሚያንገበግበው ከአምስቱ ዋና ዋና የአስፈፃሚ ኃላፊነቶች ጠ/ሚኒስትር፣ ም/ጠ/ሚኒስትር፣ መከላከያ ሚኒስትር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትና የደህንነት ጉዳይ ፍፁም መራቃቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል አስቴር ማሞ እጅግ ዝቅተኛ ድምፅ ካገኙበት ዋነኛ ምክንያት አንዱ ህወሓት የሚሄድበት መንገድ እንዲሆን ይነገራል፡፡

በነሐሴው ስብሰባ ከ5ኛው ቀን በኋላ ህወሓት ኩማ ደመቅሳን በመያዝ አስቴር ማሞን ይዞ ብቅ አለ፡፡ ከ5ኛው ቀን በኋላ 51 አባላት ያሉትን የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ለሴትዮዋ ድምፅ ማሰጠት አልቻሉም፡፡ ይብስ ግን የህወሓት የደህንነት ሰዎች የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን በማስፈራራት እንዲቀበሏቸው ቢሞክሩትም ወ/ሮዋ የባሰ ተገለሉ፡፡

በታዛቢነት ስም የተገኙት የህወሓት ‹‹የቤት ሥራ አስፈፃሚዎች››ም በወቅቱ በንዴት ቢሄዱም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም አላማቸውን ለማሳካት እንደማይታክቱ ይገመታል፡፡ ሆኖም በሰሞኑ ሹመት የተከፋውን ኦህዴድ መነካካት “የሞኝ አሸናፊ” አይነት ነገር እንዳያስከትል ለህወሓት ያሰጋል፡፡ በራሳቸው በኦህዴድ አባላት በተደጋጋሚ በጠንካራነቱ የሚወራለት የኦህዴድ መካከለኛ አመራር ከዚህ በፊት የደረሰባቸውን ቢያውቁም ያን ያቀነባበሩት ሰው አሁን በህይወት ባለመኖራቸው የሚፈሩት የለም፡፡

ተንታኞች እንደሚናገሩት በኦህዴድ ላይ የፕሮፖጋንዳ ጥቃት የተጀመረው የመለስ ዜናዊን ቦታ ለመተካት ሩጫ ከተጀመረበት ቅፅበት አንስቶ ነው፡፡ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻው መሪ እንደሆኑ የሚነገርላቸው አቶ በረከት ስምኦን ኦህዴድ የኃ/ማርያም ደሳለኝን መመረጥ እንደተቃወመ በማድረግ እንዲወራ አድርገዋል፡፡ ስለ ጉዳዩ የሚከታተሉ ቡድኖች ግን የኃ/ማሪያምና የደመቀ መመረጥ በ2002 ዓ.ም “የተበላ ዕቁብ” መሆኑን እያወቀ ኦህዴድ እንዲህ አይነት ጥርስ ውስጥ የሚያስገባው ተቃውሞ እንደማያደርግ ይናገራሉ፡፡

ምንም እንኳ ኦህዴድ ከጠ/ሚኒስትርነቱ ፉክክር ውጭ ለመሆን ቢወስንም ህወሓት በበኩሉ አቶ ኩማ ደመቅሳ ኃ/ማሪያምን እንዲፎካከሩ ለማድረግ ስጥር ነበር፡፡ ህወሓት ይህን ሲያደርግ ግብ ነበረው፡፡ የቀሪዎቹን ሦስት ድርጅቶች አባላት አቶ ኃ/ማሪያም ደስአለኝና አቶ ደመቀ መኮንን እንዲመርጡ ሙሉ በሙሉ ካረጋገጠ በኋላ ኦህዴድ ከፍተኛ ኃላፊዎችን ለማይቀር ሽንፈትና ውርደት ያዘጋጇቸው ነበር፡፡ 180 አባላት ካሉት የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ሁሉም የኦህዴድ አባላትና አንዳንድ ደጋፊዎቻቸው እንኳ የኦህዴድን ዕጩ ቢመርጡ መሸነፋቸው እርግጥ ነው፡፡ ነገር ግን በኦህዴድ አባላት ተቃውሞ ከውድድሩ ከወጡ በኋላም ስለ ጉዳዩ ምንም እውቀት የሌላቸው አቶ ሶፊያን አህመድ ዕጩ ሆነው በወ/ሮ አዜብ መስፍን ተጠቆሙ፡፡ አቶ በረከት ሦስተኛው ተሸናፊ ማን እንደሆነ ለመናገር ባይፈቅዱም ጉዳዩ ይፋ ሆኗል፡፡ በወ/ሮ አዜብ መስፍን የተጠቆሙት አቶ ሶፊያን ከ180 ድምጽ 5 ብቻ ያገኙ የኦህዴድ አባል ናቸው፡፡ ቡረኬ ትደመድማለች፣ ‹‹ኦህዴድ በማይደርስበት ቦታ ላይ ፊጥ ያለ የታላቅ ህዝብ ትንሽ ድርጅት ነው፡፡››

## “ስልጣን ከታጋይ እጅ. . . ከገጽ9 የዞረ

ይህንን መናገር ህወሃት ከውስጥም ከውጭም ችግር ውስጥ መውደቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ህወሃት በድንጋጤና በሽኩቻ ማዕበል ውስጥ ነው፡፡ ህዝቡም በተረጋጋ ሁኔታ እየተከታተላቸው ነው፡፡

• ተቃዋሚዎች በአሁኑ ጊዜ መሥራት ያለባቸውን እየሰሩ ነው ብለው ያምናሉ?

እየሰሩ ናቸው ብዬ አላምንም፡፡ በሽግግሩ ወቅት በርካታ ሥራዎችንና እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ይችሉ ነበር፡፡ ኢህአዴግን መከተል ሳይሆን ቀድመው መሄድ ነበረባቸው፡፡ እግር በእግር እየተከታተሉ የትንበያ ትንተና መስጠት ነበረባቸው፡፡ይህ አልሆነም ሆኖም ግን ለአቶ ኃ/ማርያም መመረጥ ተቃዋሚዎች ግፊት አድርገዋል ወይም ተጽእኖ ፈጥረዋል ማለት ይቻላል፡፡

• የተቃዋሚዎች መሠረታዊ ችግር ምንድነው ይላሉ?

የኢትዮጵያን የተቃውሞ ፖለቲካ ስታነሳ በርካታና ግራ የሚያጋቡ ነገሮች አሉ፡፡ በአብዛኛው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ያለው አመራር ረዘም ላሉ ዓመታት የቆየ ቂም ያዘለ ነው፡፡ ተጠራጣሪነት፣ ቁርሾና ብቀላ ተሸክመዋል፡፡ ብዙዎቹ የፓርቲ መሪ ሆነው መቀመጥ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ አዲስ ሐሳብ የላቸውም፡፡ የዙር ስልጣን ይፈልጋሉ፡፡ መሪ እንዳይፈጠር በር ይዘጋሉ፡፡ አዲስ ሐሳብ አመንጪ መሆን አይችሉም፡፡

አዲስ ሐሳብ የሚያመነጭ ሰው ለማግኘትም አይፈልጉም፡፡ እንዲያውም አዲስ ሐሳብና አዲስ ሰው ማየት ይፈራሉ ይጠራጠራሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ትግሉ አንድ እርምጃ ሳይገፋ ባለበት ወይም ወደኋላ ሲጓዝ ይታያል፡፡ ስለዚህ በተቃዋሚው ጐራ አብዮት ያስፈልጋል፡፡ ወደ ህዝብ ዘልቆ መግባት አለባቸው፡፡ አዲስ የትግል ስልት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ከቂም በቀል ከቁርሾ ከጥላቻ አስተሳሰብ መላቀቅ ይገባል፡፡ ቀደም ብለው በኢህአፓ፣ መኢሶን፣ ህወሃት አባልነት የተደራጁት አምነውበት ነበር፡፡ ለዓለማቸው ይሞታሉ፡፡ ዛሬ ተቃዋሚ ውስጥ የሚሰባሰቡት በጊዜያዊ ኩርፊያ፣ በስሜታዊነትና ጊዜያዊ ጥቅም በማጣት ይመስላል፡፡ በቀላል ጉዳይ ከተቃውሞ ጐራ ሲወጡና ሲፍረከረኩ ይታያሉ፡፡ የትግሉን መራራነትና ርዝመት አይረዱትም፡፡ በጽናት የሚታገሉ አባላትን በጥንቃቄና በእምነት መልምሎ መገንባት ያስፈልጋል፡፡

ወጣት ምሁራንን ለማሰባሰብ መስራት አለባቸው፡፡ ዛሬ ኢህአዴግ ቆዳውን ቀይሯል፡፡ ከዚህም በላይ ሊገዛን እየተዘጋጀ ነው፡፡ ይህንን ተረድቶ ህዝብን ሊያንቀሳቅስ የሚችል ስልት መቀየስ ይገባል፡፡ ፓርቲዎች መሰባሰብ አለባቸው፡፡ ልዩነታቸውን ትተው አንድ በሚያደርጋቸው ነጥቦች ተግባብተው በጋራ መታገል አለባቸው፡፡

• በመጨረሻ መጥቀሱ የሚፈልጉት ነጥብ ይኖራል?

ሠላማዊ ትግል የሚዘጋው በምርጫ ነው፡፡ ህዝብን ለምርጫ ማዘጋጀት ይገባል፡፡ መንግስት ህዝብ ካልተባበረው ሊገዛ አይችልም፡፡ ኢህአዴግ ህዝብን በተለመደው ፕሮፓጋንዳና በአርቴፊሻል ሥራ እንዳያታልለው ማሳየት ይገባል፡፡ በድጋሚ መናገር የምፈልገው ተቃዋሚዎች ራሳቸውን መፈተሽ ያስፈልጋቸዋል የሚለውን ነው ፡፡

**ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን በመርዳት**
**በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረገው የነፃነት ትግል ተሳታፊ ይሁኑ**

# ከሰለሞን ወደ ሮብኣም

## እየመጣን እንዳይሆን ?

"... አባቴ በአለንጋ ገርፏችሁ ነበር፥
እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ"



**መንግስት ሆደ ሰፊ በመሆን በትንሹም በትልቁም ጎራዴውን ከሰገባው ከመምዘዝ ሊታቀብ ይገባል። ዜጎችንም ለማጎሳቆልና ለማሸማቀቅ ጥቃቅን ጥፋቶችን ማጠራቀም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ድርጊቱ አገርንም አይገነባም።**

የዛሬውን ፅሁፌን ርዕስ የወሰድኩት ከመፅሀፍ ቅዱስ ነው። ቃሉ የሚገኘውም በመፅሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ምዕራፍ 12 ቁጥር 14 ነው።

የንጉስ ዳዊት የልጅ ልጅ የነበረው ሮብኣም ከአባቱ ከንጉስ ሰለሞን በኋላ በይሁዳና በብንያም ነገዶች ላይ ለ17 ዓመታት (ከ931-913 ዓ.ዓ) ነግሦ ነበር። አባቱ ንጉስ ሰለሞን በሀብቱና በጥበቡ ታዋቂ ቢሆንም በአስተዳደር በኩል ጨካኝ እንደነበር መዛግብት ይመሰክራሉ። ንጉስ ሰለሞን ከሞተ በኋላ ግን ልጁን ሮብኣምን የሰሜኑ ክፍል 10 ነገዶች በአባቱ ወንበር ላይ እንዳይነግስ በመቃወማቸው የእስራኤል መንግስት ለሁለት ተከፈለ። እነዚህ 10 ነገዶች ንጉሥ ሰለሞን በህይወት ሳለ ከእርሱ በታች አለቃ የነበረውንና ከነቢዩ አኪያ ጋር በመገናኘቱና ከእግዚአብሄር የተላለፈውን ትንቢት በመስማቱ ወደ ግብፅ ያሳደደውን ኢዮርብአምን እንዳነገሱ መፅሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ንጉስ ሮብኣም አባቱ ንጉስ ሰለሞን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ነገዶች ሁሉ እንዲያነግሱት በሴኬም እንዲሰባሰቡ አደረገ። ቀደም ሲል በአባቱ ሞት ምክንያት ከስደት የተመለሰው ኢዮርብአምና የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ወደ ነጋሲው ቀርበው "አባትህ ቀንበር አክብዶብን ነበር አሁንም አንተ ፅኑውን የአባትህን አገዛዝ፣ በላያችንም የጫነውን የከበደውን ቀንበር አቃልልን፣ እኛም እንገዛልሃለን" ብለው ነገሩት። ሮብኣም ግን የሽማግሌዎችን ምክር ችላ በማለትና የአማካሪዎቹን ድምፅ በመስማት በህዝቡ ላይ ዛተ።

"አባቴ ቀንበር አክብዶባችሁ ነበር፣ እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገርፏችሁ ነበር፣ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ።" ሲል በድፍረት ተናገረ። በዚህን ጊዜ አሥሩ የእስራኤል ነገዶች የናባጥን ልጅ ኢዮርብአምን አነገሱ። እሱም የሰሜናዊው መንግስት የመጀመሪያ ንጉስ ሆኖ ከ931 እስከ 910 ዓ.ዓ በሴም ነገሠ።

ከአቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ ህይወት በኋላ በብዙ የፖለቲካ ውዝግብ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን የሥልጣን መንበር የተረከቡት አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ከንጉስ ሰለሞን ልጅ ከሮብአም ሊማሩ ይገባቸዋል። ከሞታቸው ማግስት ጀምሮ ዛሬም ድረስ "ጀግናው መሪ፣ የአፍሪካ ጠበቃ፣ የአለማችን ላይብረሪ፣ አባይን የደፈረ መሪ፣ የክፍለ ዘመኑ ድንቅ መሪ፣ አቻና ወደር የማይገኝለት መሪ" እየተሰኙ የሚወደሱት አቶ መለስ ሰውናቸውና ከጠንካራ ጎናቸው ጐን ድክመቶችና ሕፀፆች እንደነበሩባቸው ማመን ተገቢ ይመስለኛል። በጠቢብነቱና በዕውቀቱ ታላቅ የተባለው ንጉስ ሰለሞን አገዛዙ አምባገነን እንደነበር የእግዚአብሄር ቃል ያስተምረናል። አቶ መለስም ብልህና ጀግና መሪ ከመሆናቸው ጋር በሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት በብርቱ ሲወገዙ እንደነበር ሊካድ አይገባም። በኤርትራ መገንጠል የአገሪቱ ወደብ አልባ መሆን የሳቸው ዘመን የጣለብን የማይድን ጠባሳ ነው። የአኙዋክና የሲዳማ ብሄር ተወላጆች እልቂት፣ በ97 ዓ.ም ምርጫ ሳቢያ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች የተጨፈጨፉ ኢትዮጵያዊያን፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ጋዜጠኞች እስርና ስደት የመልካም አስተዳደር እጦት፣ በመላ አገሪቱ የተንሰራፋው አስከፊ ሙስና፣ ሕይወትን ፈታኝ ያደረገው ድህነትና የኑሮ ውድነት ወዘተ የመለስ የአመራር ዘመን አስከፊ ገፅታዎች ነበሩ።

አቶ ኃ/ማርያም ሹመታቸው በፓርላማ ፀድቆ ቃል ኪዳን ሲፈፅሙ በአቶ መለስ መንገድ ከመንዝ ውልፍት እንደማይሉ ይልቁንም አጠናክረው እንደሚቀጥሉ መናገራቸው ከንጉስ ሮብኣም አቋም ጋር ያመሳስላቸዋልና እንደ መፅሀፍ ቅዱስ አማኝነታቸው ቆም ብለው ቢያስቡና አምላካቸው ፊት ተንበርክከው ቢፀልዩ ሳያዋጣቸው አይቀርም።

### የዮሐንስ ራዕይ Vs የመለስ ራዕይ

ራዕይ ሰው ሳያንቀላፋ በተመስጦ የሚያየውና የእግዚአብሄር ቃል የሚገለጥበት እንደሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ወደፊት ሊሆን ሊደረግ የሚገባውን ክስተት አመላካች ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርገቱ በኋላ ከአባቱ የተሰጠውን ራዕይ ለሽማግሌው ሐዋርያው ዮሐንስ በእስር ላይ በነበረባት የፍጥሞ ደሴት ገለጠለት። ዮሐንስም በእስያ አውራጃ ለነበሩት ለ7 አብያተ ክርስቲያናት በፅሁፍ እንዳስተላለፈላቸው ይሰበካል። ይህ የዮሐንስ ራዕይ የመፅሐፍ ቅዱስ የመደምደሚያ ምዕራፍ ይመስለኛል። ይህ ራዕይ ወደ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ወደ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የሚያደርስ መሆኑን የመፅሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይስማሙበታል። በሀጢአት ብዛት የቀድሞው ሰማይና ምድር ያልፉና በክርስቶስ የዳኑ ህዝቦች የሚኖሩባትን መንግሰተ ሰማያትን ዘላለማዊ ህይወት አብሳሪ ነው የዮሐንስ ራዕይ። የዲያቢሎስና የተከታዮቹ የመጨረሻ ፍርድም በዚህ ራዕይ ተተንትኗል። አማኞችም በአፅመ ሥጋ ሳሉ ለፈጣሪ ቃል ራሳቸውን በማስገዛት ለነፍሳቸው የሚያድሩት በክርስትና አስተምህሮት የሚጠበቀውን ሰማያዊ መንግስት ለመውረስና ሞትን ድል ነስተው ከአምላካቸው ጋር ለዘላለም ለመኖር ነው። ይህ ራዕይ አማኞችን በብርቱ ያፅናናል።

የሰው ልጆችም በምድር ሳሉ የግልና የጋራ ራዕይ አላቸው። ለነገ የተሻለ ራዕይን ይሰንቃሉ። የምድር ነገስታትም እንደዚሁ አገርን ለመምራት ሥልጣን ሲጨብጡ መልካም ስማቸው ከመቃብር በላይ ይውል ዘንድ ሰናይ ራዕይን መሰነቅ ግድ ይላቸዋል።

አቶ መለስ የኢትዮጵያን ህዝብ ከወታደራዊው ደርግ ጨቋኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ከትግል አጋሮቻቸው ጋር ደደቢት በረሀ የከረሙት ራዕይ ኖሯቸው ነበር። ከድል በኋላ ከስልጣን መንበራቸው ላይ ሲወጡም ስለ ነገዋ ኢትዮጵያ ራዕይን መሰነቅ ቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑ አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ ለአገር ዕድገት፣ ለዜጎች ነፃነትና ሕልውና አብነት የሚሆኑትን የአቶ መለስን ራዕይ በቀጣይ የመተግበር ሀላፊነቱ የሁላችንም ነው፤ በእሳቸው የስልጣን ዘመን የተጀመሩት የልማት ተቋማት ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው እናምናለን። ታላቁ የህዳሴ ግድብም ጅማሬው ከፍፃሜ መድረስ ይኖርበታል። ድህነትን ታሪክ ለማድረግ በትጋት መስራት ተገቢነቱ አያጠያይቅም። የኢህአዴግን የሥልጣን ዘመን ለማራዘም ሲባል ግን የዜጎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚጥሱ ራዕዮቻቸው ፍፁም ሊቀይሩ ይገባቸዋል። የአቶ መለስ ራዕይ የዮሐንስ ራዕይ አይደለምና። ዮሐንስ በራዕዩ የመጨረሻ ምዕራፍ (ምዕራፍ 22፥18) እንደገለፀው በመፅሀፉ ውስጥ አንዳች ሀሳብ የሚጨምርና ከመፅሐፉም የሚቀንስ የሚገጥመው መቅሰፍት መስፈሩ የራዕዩን ፍፁምነት የሚያረጋግጥ ነው። መቀነስ መጨመር፣ መበረዝ ከቶ አይቻልም።

ከአቶ መለስ ሞት በኋላ ራዕያቸው ያለአንዳች መበረዝና መቀነስ እንደሚተገበር መሰበኩ





በእጅጉ ያሳዝናል። ዛሬ በዓለማችን የሚታዩ ተለዋዋጭ (Dynamic) ሁነቶችን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። በደቂቃዎች ውስጥ የሚፈጠሩት ክስተቶች አገሮች የሰነቁትን ራዕይ እንዲፈትሹ ያስገድዳቸዋል። ለእነ አቶ ኃ/ማርያምም ይህ ሀቅ ሊዋጥላቸው ግድ ይላል። መሻሻልና መለወጥ የሚገባቸው የአቶ መለስ ራዕዮችን ከወቅቱ የዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማጣጣም የሰለጠነ አካሄድ ነው። እሳቸው ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጣስ የሰነቋቸው ራዕዮች ፍፁም መፈተሽ አለባቸው።

### "ግፍ ሲናኝ ኩበት ሰምጦ ድንጋይ ይዋኝ"

መጋቢት 2004 ዓ.ም ከመምህራን የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ጋር በተያያዘ የአዲስ አበባ ከተማ መምህራን እስከ ሥራ ማቆም የሚደርስ የተቃውሞ ድምፅ ማሰማታቸው ይታወቃል። በዚህም መዘዝ በወቅቱ ስድስት መምህራን ከስራ መባረራቸውና እስከ ዛሬም አለመመለሳቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ነፍሳቸውን ይማረውና አቶ መለስ ዜናዊ ሚያዝያ 9/2004 ዓ.ም በፓርላማ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር በቀጣይም ሌሎች መምህራን እንደሚባረሩ ዝተው ነበርና ይህንን ራዕያቸውን ለማሳካት በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ፊታውራሪነት በመምህራን ላይ ዘመቻ ተከፍቷል።

የትምህርት ጥራት ፓኬጅን ከአቶ መለስ ራዕይ ጋር ለማቀናጀት ለ5 ቀናት የቆየ ውይይት ተደርጎ መምህራን ወደስራ ለመግባት ሲዘጋጁ ዱብዕዳ ወረደ። በአዲስ አበባ ከተማ የየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሹማምንት ግማሹን መምህር ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ከነበረበት ት/ቤት ወደሌላ ት/ቤት በአንዲት ገፅ ደብዳቤ በግፍ አዛወሩት። ሌላውን በሰዓት የሚፈነዳ ፈንጅ አጥምደው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጡት። የተወሰኑትንም ጥቃቅን የስነ ምግባር ጥፋቶችን አጠራቅመውና አስፈራርተው አፉን እንዲዘጋ ነገሩት።

መምህራን ‹‹የደመወዝ እርከን ማሻሻያውን በመቃወም በየት/ቤታቸው ለምን ተንጫጩ›› በሚል የመከራን ገፈት ማስጨለጥ ዜግነትን የሚፈታተን ድርጊት ነው። መምህራንን በየጥቃቅን ምክንያቶች እያስበረገጉና እያሸማቀቁ የትምህርት ጥራትን ማሰብ ምን የሚሉት ተቆርቋሪነት ነው? "ከድጋፍና ከእልልታ ውጭ ለምን ብሶት ትናገራላችሁ? ..." በሚል እየተከታተሉ አናት አናቱን መውገር ምን የሚሉት ዲሞክራሲ ነው? ኢህአዴግውያን ለ17 ዓመታት በረሀ ሽምቀው የታገሉለት ዲሞክራሲ እንዲህ ከሆነ ባፍንጫችን ይውጣ። እኒያ የትግራይና ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በጀግንነት የተሰውለት ዓላማ ነፃነትና ዲሞክራሲን ካላስገኘ የኢህአዴግ ስልጣን መያዝ ትርጉሙ ምን ይሆን?

አሁንስ ግፍ በዛ። የግፍ ፅዋውም ሞልቶ ፈሰሰ። ኢህአዴግ በሙስና የተዘፈቁና የአገርን ሀብት የዘረፉ፣ ህዝብን ያንገላቱና ፍትህ ያዛቡ፤ በአቅም ማነስ የሚተቹ ካቢኔዎቹንና ካድሬዎቹን ከስልጣን አባብሎ እያወረደ የሥራ ዕድልና ቦታ ሲያመቻች በኑሮ ውድነት አንጀታቸው የታጠፈ መምህራንን "ለምን ቀና ብለህ አየኸኝ?" በሚል ሰበብ ሲያንገላታ ለማን አቤት ይባላል? ጩኸትን የሚሰማ ባለስልጣን ማግኘቱ ሰባተኛው ሰማይ የመድረስ ያህል ርቋል።

በአቶ መለስ ዘመን የነበረው መግረፊያ አለንጋ በአቶ ኃይለ ማርያም ንግስና የመጀመሪያ ወር ላይ በጊንጥ መተካቱ ከሰለሞን ወደ ሮብኣም ለመሸጋገራችን ማሳያ ነው።

### ኢህአዴግ Vs የደቡብ አፍሪካው አፓርታይድ

ዓለም በብርቱ ያወገዘው የደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ አገዛዝ ነጩን ከጥቁር በማስበለጥ ዘግናኝ ግፍ የፈፀመ ሥርዓት ነበር። የደቡብ አፍሪካ ጥቁር ህዝብ ነፃነቱን ተነፍጎና ሰው የመሆን ሰብአዊ ክብሩ ተዋርዶ በነበረበት ዘመን የእነ ኔልሰን ማንዴላ ትግል የጥቁርን ህዝብ ነፃነት ማረጋገጥ ነበር። ሥርዓቱ የዘር መድልዎን እየፈፀመና ሰብአዊ መብቶችን እየጣሰ የሚገነባቸው እጅግ ግዙፍ የኢኮኖሚ አውታሮች፣ ሰፋፊና ረጃጅም መንገዶች ውብና ሰማይ ጠቀስ ፎቆች፣ የከበሩ ማዕድናት ማምረቻ ፋብሪካዎች ለጥቁሩ ደቡብ አፍሪካዊ አልተዋጠለትም፤ ከዳቦ ነፃነት ይቀድማልና።

ዛሬም ኢህአዴግ ከደቡብ አፍሪካው የአፓርታይድ ሥርዓት ያልተናነሰ ሆኖብናል። በጣት የሚቆጠሩ የኢህአዴግን የፖለቲካ ጠበል የተረጩ ካድሬዎች የምዕራቡ ዓለም ቱጃሮች የሚኖሩትን ህይወት ይኖራሉ። የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ያልሆነው ህዝብ በገዛ አገሩ ባይተዋር ሆኗል። ወጣቱ ትውልድ በአገዛዙ ተንገፍግፎ ህይወቱን ለሞት እየገበረ ለስደት ተዳርጓል።

ዛሬ ኢህአዴግን ለመውቀስ ከመድፈር ይልቅ ፈጣሪን መውቀስ ይቀላል። ተጨባጭ የሆኑ ወንጀሎችን የፈፀሙ የኢህአዴግ ሹመኞች ከስልጣናቸው ሲነሱ በመረጡት የሥራ መደብና የሥራ ቦታ ሲመደቡ "የደመወዝ ስኬል ማሻሻያው በብዙሃን መገናኛዎች ተጋንኖ መነገሩ ፍትሃዊ አይደለም።" ያሉ መምህራን እንደ ቆሻሻ ዕቃ የትም ሲጣሉ ማየቱ እየከፋ መጥቷል።

### ዛሬስ ኢህአዴግ ኪሎው ስንት ነው?

ይህን ንዑስ ርዕስ የተዋስኩት ከደራሲና ሃያሲ አለማየሁ ገላጋይ ነው። በፍትህ ጋዜጣ እትም ላይ በዚህ ርዕስ የፃፈው ሀሳብ የተደራሲውን ቀልብ የሳበ ነበር። በወቅቱ የፍትህና የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ጋዜጠኞችንና አምደኞችን ለማሰር መረጃ እየተጠናቀረ ስለመሆኑ በማህበራዊ ድረገፆች መለቀቁ ፀሐፊውን ለመፃፍ አስገድዶታል። አንድ የቦክስ ተወዳዳሪ ስፖርተኛ የሚፏቀሰው በኪሎው (በክብደቱ) ከሚመጥነው ቦክሰኛ ጋር እንጂ ከትንሹም ከትልቁም አይደለም። ሁሉም ነገር ከእኩያ ጋር ሲሆን ያምራል። ኢህአዴግ ግን ኪሎውን አያውቅም። ለክብደቱም ሚዛን የለውም። የትንኝ ድምፅም ቦክስ ታስጨብጠዋለች። ታንክና መድፍ ታስደነግጠዋለች። አንድ የ21 ዓመት ጎረምሳ ከአራትና አምስት አመት ህፃን ጋር ለድብድብ ቢጋበዝ እንደ ወፈፌ አሊያም እንደ አዕምሮ ዘገምተኛ ይቆጠራል እንጂ ጤነኛ ነው የሚለው የለም። ኢህአዴግ ከመምህራን ጋር ለመፋለም ቡጢ መጨበጡ ምን የሚሉት ነው? ድህነት ካደቀቀውና "ጠመኔ ትጥቁ" ከሆነው ከሲታ መምህር ጋር ታንክና መድፍ የታጠቀው ኢህአዴግ ለመፋለም ሽሚዙን መሰብሰቡ ዛሬም የኪሎውን ክብደት አለማወቁን የሚያረጋግጥ ነው።

መንግስት ሆደ ሰፊ በመሆን በትንሹም በትልቁም ጎራዴውን ከሰገባው ከመምዘዝ ሊታቀብ ይገባል። ዜጎችንም ለማጎሳቆልና ለማሸማቀቅ ጥቃቅን ጥፋቶችን ማጠራቀም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ድርጊቱ አገርንም አይገነባም። ህገ መንግስቱ ላይ የሰፈሩትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መጣስ በራስ ላይ እሳት እንደ ማቀጣጠል ይቆጠራል።

የነገን ፈጣሪ ያውቃል፣ ለዛሬ ግን አለን፤ ይህም መኖር ከተባለ።

## "ላሜ ቦራ" ብዕሬ

መምህር ቀለሙ ሁነኛው

ብዕሬ ቀለም ላትነጥፍ ከዝክረ እውነት ላትፋታ
የተሰወረን ሀቅ ገልጣ የተገደነን ምስጢር ከፍታ
ፍንትው አድርጋ ልታሳየን የሕዝብን ዋይታ ልታሰማ
ቃላትን መርጣ ከሽና ልታንቆረቁር ውብ ዜማ
ቃልዋን ከቃሌ አፅንታው በእስከ ወዲያኛው ቃል ኪዳን
እውነትን በእውነት ልትዘክር ሽፍጥ ቅጥፈትን ልትኮንን
ወድቃ ላትቀር ልትነሳ እጅ ላትሰጥ ብዕሬ
ደሟ ከደሜ ተዋህዶ ፍቅሯ ተፋቅሮ ከፍቅሬ
የፍርሃቴን ግርዶሽ ቀድዳ ጀግንነቴን እያጀገነች
"ላሜ ቦራ" ናት አልባታለሁ ዛሬም ቀሰሟን አልነጠፈች
የውስጤ ግለት ነበልባል የተዳፈነው እረመጥ
የወላፈኑ ግርፋት ብረት አምጭ የምገላገለው
የነፍሴን ጥማት የማረካው በብእሬ እምቅ ኃይል ነው
ምንም ብታሰር እግር ተወርች ስቃዬ ከቶ ቢበዛም
የህይወቴ ክር ብትቀጥን የነፍሴ ልባስ ብትሳሳም
ፍቅራችን እስከ መቃብር ዝንተዓለም አንረሳሳም

የግጥሜ መታሰቢነት
ቃሊቲ ወህኒ ቤት በግፍ ለታሰሩት ለጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ
ለጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ይሁን

# የቃሊቲና ቂሊንጦ ወህኒ ቤቶች ገመና

ከኢንጂባራው ዘላለም

ውድ አንባቢያን፣ ባለፈው ፅሁፌ ላለፉት ዓመታት የገጠሙኝን የእስር ቤት ገመናዎች ከብዙ በጥቂቱ ዋና ዋና ነጥቦችን እንዳስቃኘኂችሁ የሚታወስ ነው፡፡ ስለ ሸዋ ሮቢት ወህኒ ቤት ላስጐበኛችሁ ቃል ገብቼ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ደጋግሜ ሳስበው ስለቃሊቲና ስለ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤቶች ለአንባቢያን ያስተላለፍኩት መልዕክት በቂ መስሎ ስለአልታየኝ እንደገና መፃፉን መረጥኩኝ፡፡ ለዛሬ ደግሞ ባለፈው ፅሑፌ በፍሬ ሃሳብ ደረጃ ብቻ የጠቀስኩትን በፌዴራል ማ/ቤቶች አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮችና የገዥው መደብ አባላት በሆኑ መኮንኖች የሚፈፀመውን ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የስልጣን መባለግና ውንብድና እንዲሁም የነኝህ ግለሰቦችም ሆነ የስርዓቱ አባላት ስብእና እስከ ምን ድረስ እንደሆነ እንደ ማሳያ ሊቀርብ የሚችል እውነታ ይዤ ቀርቤያለሁ፤ መልካም ንባብ፡፡

በመሠረቱ በወይኒ ቤቱ (ማ/ቤቱ) የሚገኙ ከፍተኛ መኮንኖችም ሆኑ አጠቃላይ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ላይ የሚገኙ የሥርዓቱ ታማኝ ከፍተኛ መኮንኖች የተሸከሙትን ማእረግ ሆነ ኃላፊነት መሸከም የማይችሉ እና ለለበሱት ማዕረግ የማይመጥኑ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን የሥልጣን እርከን ለመቆናጠጥ የብዙ ንፁህ ኢትዮጵያውያን ህይወት ገብረውና በብዙ ሚስኪኖች ደም እጃቸውን የታጠቡ በመሆኑ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸውም ሆነ አስተሳሰባቸው ይህን ሲፈፅሙ የኖሩትን ወንጀል ሚስጢራዊነት ከመጠበቅ አንፃር የተቃኘ ነው፡፡

በተጨማሪ የገዥው ሥርዓት ጉሰኛ የሆነ የስነ አስተዳደር ፖሊሲ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ከመሆኑም ሌላ ለለበሱት ዩኒፎርም ለለበሱት ማእረግ እንዲሁም ዛሬ ለሚዘምሩለት የትላንቱ ትግል ዓላማ ክብርም ግንዛቤም የሌላቸው ናቸው፡፡

ለዚህ ደግሞ ዋንኛ መገለጫው መኮንኖቹ የሚፈፅሙት ከተራ የሌብነት ተግባር አንስቶ እስከ ከፍተኛ የሙስና ቅሌቶች አንዱ ነው፡፡ ከገዥው ስርዓት የተለየ አመለካከትና አስተሳሰብ ያለውን ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ እንደ ውጭ ጠላት ቆጥሮ ሲጨፈጭፉ የሚኖሩና በመጨፍጨፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪ ልዩነትን የሚያስተናግደው አስተሳሰባቸው የትምክህትና የጐሰኛነት አስተሳሰብ ተደምሮበት እስር ቤቶቹን ወደ መግደያና ማጐሪያ ስፍራነት ቀይሮታል፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደ ሞከርኩት በቃሊቲና በቂሊንጦ ወይኒ ቤቶች በመንግስት አመራር ማረሚያ ቤቶች በተዋረድ ከላይኛው የሥልጣን እርከን እስከታች የተቀመጡትን ባለ ስልጣናት ምንነትና ማንነት አስቃኛችኂለሁ፡፡

የቃሊቲ ወይኒ ቤት የተመሠረተው እ.ኤ.አ 19 97 ዓ.ም በክረምት ወራት ሲሆን ከዛ ቀድሞ በአሁኑ ሰዓት የአፍሪካ ህብረት ዋና መስሪያ ቤት ያለበት በቀድሞ ስሙ ዓለም በቃኝ ወይኒ ቤት እየተባለ ከሚጠራው እስር ቤት የነበረው እስረኛና ጠባቂ ፖሊስ ሙሉ በሙሉ ወደ ቃሊቲ በተዘዋወረበት ወቅት ነበር፡፡

ከዛ ቀድሞ በነበሩት ብዙ አመታት በዓለም በቃኝ ወይኒ ቤት የእስረኛ አስተዳደርና የሰብአዊ መብት አያያዙ ጥሩ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለያየ ጊዜ በፖሊሶችና በእስረኛው መካከል በተነሳ ግጭት ተከትሎ ለእስር ቤቱ አመፅ በመነሳቱ ከ19 በላይ የሚሆኑ እስረኞች ተገድለዋል፡፡ ነገር ግን ከዚያን ጊዜ በኂላ በዋነኝነት በዓለም በቃኝ እስር ቤት የተከሰቱ ግጭትና ግድያ ዋነኛው በ1995 የተከሰተው ነው፡፡ በዚህ ወቅት አጠቃላይ በማማ ላይ ካሉ ፖሊሶች በተተኮሰ ጥይት እና ኂላ ስማቸው እየተጠራ ወጥተው ባዛ የቀሩ እስረኞች ከ40 እስከ 50 ይሆናሉ፡፡

ይህንን ግድያ ከፈፀሙት መካከል ዛሬም በስራላይ ያሉ ሲሆን ድርጊታቸው እንደ ጀብዱ ሥራ ተቆጥሮ እስከ እንስፔክተር የደረሱ አሉ፡፡ ኢንስፔክተር ከእነዚህ ውስጥ በቂሊንጦ ወይኒ ቤት ሃላፊ ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ (ዞን ማለት በእስር ቤቱ ከሚገኙ የእስር ግቢዎች አንዱን ይወክላል) ይህን ግለሰብ እንደ ማሳያ አነሳሁ እንጂ በወቅቱ ጭፍጨፋ ላይ ከተሳተፉት ከ10 በላይ አመራሮች ዛሬም በተለያዩ የስልጣን እርከን ላይ ይገኛሉ፡፡

ወደ ቃሊቲ እንመለስና ነገሮች እየከፉ የመጡት ከመጀመሪያውነው ምክንያቱ ደግሞ የቃሊቲ ወህኒ ቤት በራሱ የተመሰረተው ምርጫ 97 በኂላ የነበረውን ግርግር ተከትሎ በመሆኑ ነው፡፡

በሆነውም ባልሆነውም እያሳበቡ እስረኛውን አውጥቶ መደብደብና ማሰቃየት በሰንሰለት ማሰር እየበረታ መጣ በተለይ በወቅቱ በእስር ቤቱ ከፍተኛ ቁጥር የያዙትና መከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ ያሉ የኦነግ አባላትና ምርጫ 97ን ተከትሎ እየተለቀሙ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በመሆናቸው አብዛኛው እስረኛ የጥቃቱ ሰለባ ሆነ፡፡

በ1998 ዓ.ም በቃሊቲ አስከፊ ጭፍጨፋ ተፈፀመ፡፡ በቃሊቲ እስር ቤት ዞን 2 የተጀመረው ጅምላ ተኩስ ከመቅስፈት ወደ ዞን 3 እና ሌሎችም ሲስፋፋ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ርሸና ከዞን ሁለት 86 ሰው ሲገደል እና ከ50 በላይ ሲቆስል በአንፃሩ በሌሎች ዞኖች የተወሰነ ወጣት ህይወት ጠፍቷል፡፡ የሚያሳዝነው ደግሞ ከሟቿች መካከል ታማሚዎች፣ በእንቅልፍ ላይ የነበሩ ፀጉር ቤት ፀጉር ሲስተካከሉ የነበሩ ይገኙበታል፡፡ እጅግ የሚያስገርመው ደግሞ ጭፍጨፋው በተፈፀመ ዕለት ማታ ETV ሁለት ሰዓት ላይ በነበረው የዜና እወጃው ከቃሊቲ ማ/ቤት ሊያመልጡ የሞከሩ ሌቦች ክራውን ሆቴል ጀርባ 7 ሰው መገደሉን መዘገቡ ነበር፡፡

በወቅቱ የነበረው የሃገሪቱ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከሰማንያ በላይ እሬሳ በቪዲዮ ቀርፆ ቢወስድም ከ50 በላይ ቁስለኞች ህክምና ሳይሰጣቸው ግቢ ውስጥ ዝናብና ሐሩር ሲፈራረቅባቸው ባይናቸው ተመልክተው ቢሄዱም በዚህ ጉዳይ ላይ አንዲትም አስተያየት ሲሰጡ አልተደመጡም፡፡ የኢፌዴሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ የማይወጣ ተቋም የሆነበትና በታሪኩ ጥቁር ነጥብ ያስመዘገበበት ነው፡፡

በወቅቱ የተረሸኑት እስረኞች አስከሬን በጅምላ መቃብር ተቀብሮ በጊቢ ውስጥ ሁለት ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ማንም ይህን እውነታ ማረጋገጥ የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በወቅቱ በቃሊቲ የነበሩ ከ4500 በላይ እስረኞች ዛሬም በዝዋይ፣ ቃሊቲና ቂሊንጦ ስለሚገኙ በፈለገው መንገድ ማጣራት ይችላል፡፡

ይህን ተከትሎም በወይኒ ቤቱ አዲስ ወይም ቀድሞ ከነበረው የከፋ የጥበቃ ስራዓት ተግባራዊ ተደረገ፡፡ ይኸውም አዳዲስ ጭለማ ቤቶች ከ8 በላይ የሆኑ እያንዳንዳቸው ከ3 ክፍል ድረስ ያላቸው ቤቶች ተሰሩ በተጨማሪ በየማማው ስር አንድ ሰው በአግባቡ የሚያስተኙ የቅጣትና የማሰቃያ ቦታዎች ተዘጋጁ፡፡ ይህ የሆነው በሁለት ዋንኛ ምክንያቶች ሲሆን አንደኛ የተፈፀመውን ወንጀል ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ሁለተኛ ለበቀል፡፡

ጭለማ ቤቶቹ ከመገንባታቸው በተጨማሪ በነዚህ ጭለማ ቤቶች ለጥበቃም ሆነ ለድብደባ የሚመደብ የጥበቃ ቡድን የተመሰረተ ሲሆን ይህ ቡድን በአንድ ጨካኝ ግለሰብ የተባለ ግለሰብ የሚመራ ሆኖ አጠቃላይ አባላቱ ትግርኛ ተናጋሪ ሲሆኑ በ1998 ጭፍጨፋ የተሳተፉ መኮንኖች የሚመሩት ሁኖ ተዋቀረ፡፡ ይህም አንደኛ የመደብደብም ሆነ የማሰቃየት መመርያ ሲሰጣቸው ያለመንገራገር እንዲፈፀም፤ ሁለተኛ ለሚፈፀሙ በደሎች ሚስጥራዊነት (ምስጢር ለመጠበቅ) ምቹ ሁኔታን ፈጠረ፡፡

እነኚህ የጭለማ ቤቶች እንደተገነቡ ወደነዚህ ጭለማ ቤቶች የመግባት እጣ የገጠማቸው አቶ ስዬ አብርሃ አቶ ታምራት ላይኔ፣ አቶ ሙኒር የሱፍ፣ መስፍን ኢታና ቴዲ አፍሮ (ቴድሮስ ካሳሁን) ከፍያለው ተፈራ አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል አንዱዓለም አራጌ እና ሌሎችም ታዋቂ ሰዎች የሚገኙበት ነበር፡፡ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት ግን የቅንጅት አባላት የነበሩና ከተለያየ አካባቢ የኦነግ አባላት ናቸው እየተባሉ የታሰሩ ናቸው፡፡ አቶ ስዬ በመጽፋቸው ለምን እንዳልዘረዘሩት ገርሞኛል፡፡

በ------------- ወር ደግሞ አዲስ ነገር ተከሰተ ኢህአዴግ ከ40 በላይ የሆኑ የአማራ ተወላጆችን ሰብስቦ አሰረ፡፡ የእስራቱ መንስኤ ደግሞ የግንቦት 7 አባል ናቸው የሚል ነበር፡፡ ከታሰሩትም ሰዎች መሀከል ወታደራዊ ጄነራሎችእና ከፍተኛ መኮንኖች ይገኙበታል፡፡ ከታሰሩበት ወቅት ጀምሮ በማዕከላዊ የተለየ ጥበቃና ምርመራ ሲከናወንባቸው ቆይተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኂላ በቀጥታ ወደ ቃሊቲ በመምጣታቸው ምክንያት በቃሊቲ የነበረው ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ ወረደ፡፡ በቃሊቲ ያሉ ጭለማ ቤቶች በሙሉ በአዲስ መልክ ጥበቃ ተመደበላቸው፡፡ በነዚህ ጭለማ ቤቶች በጥበቃ የተመደቡ የጥበቃ አባላት በሙሉ ትግርኛ ተናጋሪ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ተመርጠው የሚመሩት ቡድን በእስር ቤቱ ያሉ ጭለማ ቤቶችን ይቆጣጠራል፤ ይደበድባል፤ በሰንሰለት ያስራል ወዘተ

እኚህ ተከሳሾችም ከማእከላዊ እንደ መጡና ክሳቸው በፍርድ ቤት የመታየት ላይ እያለ እንደ ማንኛውም እስረኛ ዞን 3 (የቀጠሮ ዞን) መቆየት ሲገባቸው ልክ እንደ መጡ ወደነዚህ ጭለማ ቤቶች ተጋዙ፡፡ በተለይ ጄነራል ተፈራ ማሞ፣ ጄነራል አሳምነው ጽጌ፣ ኮረኔል ደምሰው አንተነህ፣ ሻለቃ መኮንን ወርቁ የተባሉ 2x2 በማይሆኑ ጠባብ ክፍሎች ውስጥ ለብቻቸው እንዲታሰሩ ተደረገ፡፡ ይህም ከሆነ በኂላ እነኚህ ተከሳሾች ከቤተሰብ ጋር መገናኘት ቢፈልጉም ሆነ ህክምና ማግኘት ቢፈልጉ





ቀድሞ በተቋቋመውና ለጥበቃ በተመደበው ቡድን እና በነየ በጐ ፍቃድ ብቻ ይከናወናል፡፡

ከዚህ በዘለለ የመብት ጥያቄ መጠየቅ በተለይ ከግል ጠበቃ ጋር መገናኘት የማይታሰብ ሆነ፡፡ አስከፊው ነገር ደግሞ እኚህ ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ስለመብታቸው ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት ወደ ወይኒ ቤቱ ከተመለሱ በኂላ ፍርድ ቤት በህግና በዳኞች ፊት ባቀረቡት ጥያቄ ምክንያት ለሊት ድብደባ ይፈፀምባቸው ነበር፡፡ ለአብነት ይህል ጄነራል ተፈራ ማሞና ሻለቃ መኮንን ወርቁ በተደጋጋሚ ለድብደባ ተዳርገዋል፡፡ ድብደባውን የሚፈፅሙት ከላይ ስማቸው የተጠቀሱት ለድብደባ ያዘጋጁት ቡድን ሲሆን እነኚህ ፖሊሶች ይህን ግፍና በደል ለመፈፀማቸው በህግ መጠየቅ ሲገባቸው የፈፀሙት ወንጀል መሪዎቻቸውን ለማስደሰት የተበረከተ ገፀ በረከት ስለሆነ በተቃራኒው ስልጣን ተጨምሮላቸዋል፡፡

በነዚህ ጭለማ ቤቶች የተሰቃዩና በመስቃየት ላይ የሚገኙት ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ እነኚህ ለአብነት ተጠቀሱ እንጂ ለምሳሌ እነ ኢንጅነር መስፍን አበበና ኢንጅነር ተስፋሁን ጨመዳ የተባሉ የኦሮሞ ተወላጆች ከኬንያ ታፍነው ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ጭለማ ቤቶች ለየብቻ ታስረው ድብደባና እንግልት እየተፈፀመባቸው በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡

የዚህ ወንጀለኛ ቡድን ተግባር ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ቡድን በቀጥታ ከስርዓቱ መረጃና ደህንነት መሪዎች መመርያ እየተቀበለ ያስፈፅማል፡፡ በመሰረቱ የኢህአዴግ የማሰርያና የመግረፊያ ቦታዎች ቃሊቲና ማእከላዊ ብቻ አይደሉም፡፡ በአሁኑ ሰዓት አድራሻቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ያልሆነ የሥርዓቱ መረጃና ደህንነት ቢሮ የሚጠቀምባቸው ከ7 ያላነሱ ቪላ ቤቶች በከተማ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ማንኛውም ፖለቲከኛ ወይንም በነርሱ ቋንቋ ሽብርተኛ ተብሎ የተጠረጠረ ግለሰብ ሲታፈን ተሽከርካሪ ውስጥ ከገባ በኂላ አይኑና እጁ ታስሮ ወደ እነዚህ ቪላዎች ይወሰዳል፡፡ በመቀጠልም አስፈላጊ ነው ተብሎ የታመነበት ነገር ሁሉ ከተፈፀመበት በኂላ በህይወት ከተረፈ ወደ ማእከላዊ ይወሰዳል፡፡

ወደ ተነሳሁበት የእስር ቤት አጀንዳ ልመለስና በየወይኒ ቤቶቹ ያሉት መኮንኖች የፈፀሙት በደልና ግፍ ተቆጥሮ (ዘርዝሮ) ለመጨረስ ብዙ ግዜ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ ስነሳ እንደ ጠቀስኩ በየወይኒ ቤቱ ያሉ መኮንኖች አንዱ ሲሰርቅ አንዱ ሲዘርፍ ሌላው ሲገርፍና ሲያንገላታ ሃይባይ የጠፋበት ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉት፡፡

2 እያንዳንዱ ከተራ አባል እስከ ከፍተኛ አመራር ያለ በንፁህ ኢትዮጵያዊ ደም እጁን የታጠበ በመሆኑ አንዱ ሌላውን የመቃወምም ሆነ የመገሰፅ ሞራል የለውም፡፡ አሊያም አይፈልግም፡፡ 2 ከጅማሮ ይዘውት የመጡት የዘረኝነትና ከደም ጋር የተቆራኘው አስተሳሰባቸው ሌላውን ሌላውን ኢትዮጵያዊ እንደ ጠላት እንዲቆጥሩት ስላስገደዳቸው ሀገር ማለት እነሱ ብቻ ህገ መንግስት ማለት መለስ ዜናዊና የመለስ ዜናዊ ፍላጐት አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህ በመሆኑም ከነርሱ ፍላጐትና ስልጣን የሚወጣ ማንኛውም አካል ይጠፋል፡፡

## ሙስና በቃሊቲ

ይህን በዚህ ልቋጭና በመቀጠል በቃሊቲ የሚፈፀሙና በመፈፀም ላይ ስላሉት ተራ ሌብነቶች አንስቶ እስከ ከፍተኛ የሙስና ወንጀሎች እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች በመጠኑ ላመላክታችሁ፡፡

በየማረሚያ ቤቶቹ የሚፈፀሙት የሙስናና የሌብነት ተግባራት ምንጫቸው 3 ሲሆኑ እነርሱም 1ኛ መንግስት ለእስረኛውና ለእስር ቤቶቹ የሚመድበው ገንዘብ 2ኛ እስረኛው ተከራይቶ የሚገለገልባቸው የተለያዩ የመዝናኛና የመገልገያ ዘርፎች 3ኛ ለእስረኛው ያልተፈቀዱ ነገሮችን በማድረግ ወይም ከከሳሽ ሀብታሞች ገንዘብ በመቀበል የእስረኛውን መብት በመጣስ የሚፈፅሙ ናቸው፡፡

እነኚህን ከላይ የተጠቀሱ ዋናዋና ነጥቦች ስንመለከት በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስር የሚገኙ ማረሚያ ቤቶች በተለይ ቂሊንጦ ቃሊቲ ዝዋይና ድሬደዋ ማረሚያ ቤቶች እጅግ ሲበዛ ተቆጣጣሪ የሌላቸውና ማንኛውም ነገር በግለሰቦች በጐ ፍቃድ የሚከናወንና የሚተዳደር ነው፡፡

የድሬደዋ፣ ዝዋይ፣ ሸዋሮቢትና ቃሊቲ ማረሚያ ቤቶች ላለፉት ብዙ አመታት ከ4 የማይበልጡ ኂላፊዎች እየተፈራረቁ ያስተዳደሩት ሲሆን በዚህም ለታራሚው ለምግብ አቅርቦት የሚመደበው ባጀት የሕክምና አገልግሎት መስጫ መሳርያዎችና መድሃኒቶች መንግስት እያቀረብኩ ነው ቢልም በነዚህ ማረሚያ ቤት የሚገኝ ቁጥሩ ከ18000-19000 የሚገመት ታራሚ (እስረኛ) የሚመገበውን ምግብ መሰል ነገርም ሆነ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት ማየት የፈለገሰው ከእለታት አንድ ቀን ብቅ ብሎ መጐብኘት ይችላል፡፡

እስረኛው ለምግብ እጥረት ከመሰቃየቱ በላይ ለፅዳት የሚሆን ሳሙና እንኳ በወቅቱ ስለማይቀርብለት በብዛት ለህመም ይጋለጣል፡፡ በታመመለትም ወቅት ወደ ህክምና ለመቅረብ ያለው ቢሮክራሲ እንዲሁም በቂ የመድሃኒት አቅርቦትና የሰለጠነ የሕክምና ባለሙያ በሌለበት ለህልፈተ ህይወት የተጋለጡ እስረኞች ቁጥር ብዙ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ስም ዝርዝራቸውን መግለጽ ይቻላል፡፡

በአንፃሩ ለህክምናና ለምግብ የሚመደበው በጀት የሚቆጣጠረው ካለ መኖሩም በበይ በተለይ በቃሊቲ ወይኒ ቤት በቀን ከ170-100 እስረኛ አዲስ ስለሚገባና ከተለያዩ እስር ቤቶች ከዝዋይ ቂሊንጦ፣ ድሬደዋ፣ ሸዋሮቢት እስር ቤቶች ከ500 የሚበልጡ እስረኞች ስለሚገቡና ስለሚወጡ በቀን የሚመደበው ወጪ ተለይቶ ስለማይታወቅ ለሙስና እጅግ በር የከፈተ ነው፡፡ በተጨማሪ በየ እስር ቤቶቹ ያሉ የፋይናንስ አስተዳደር አካላት ከላይ ጀምሮ በተዘረዘሩ ወንጀሎች በሙሉ የተሳተፉና የአንድ አይነት ጐሰኛ አስተሳሰብ ተከታዬች በመሆናቸው የመጠቃቀምና የእከክልኝ ልከክልህ ጨዋታ እጅግ ይበረክታል፡፡

ሁለተኛውና እጅግ የሙስና ምንጭ የሆነው ዘረፋ ደግሞ በማረሚያ ቤቶቹ የሚገኙ የመዝናኛና የአገልግሎት መስጫ መስኮ ገቢ ሲሆን ይህ ዘርፍ የተሌ የሚያደርገው ደግሞ ከሙስና ምንጭነቱ በተጨማሪ የዘረኝነት ጥቅም ማስጠበቂያና የዜጐች ምራል መግደያ ሆኖ ማገልገሉ ነው፡፡ በቃሊቲ እስር ቤት ለእስረኛው ተከራይቶ አገልግሎት የሚሰጥ አስር የሻይ ቡና ክበባት አሉ፡፡ አንዱ ክለብ የሚከራይበት ዋጋ በወር ዝቅተኛው 11.000 (አስራ አንድ ሺ) ሲሆን ከፍተኛው 37.000 ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ይህንን ክበብ ተከራይቶ የሚሰራ ሰው የመስራት የውሃ፣ የታክስ ወጪ ስለሌለበትና የሠራተኛ ደሞዝ ከፍተኛው 80 ብር ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ጥራቱ እጅግ የወረደ ቡና ሻይ ወተት ቁርስ እጅግ ባልተመጣጠነ ዋጋ ስለሚያቀርብ ነው፡፡

በዝቅተኛ ዋጋ የሚከራየው የዞን አንድ ክበብ ነው፡፡ ከፍተኛው ዞን ሁለትና ሦስት ነው፡፡ አጠቃላይ በጊቢው 8 የወንድ ዞኖችና 2 የሴት ዞኖች ስለሚገኙ በወር ምን ያህል ገቢ ከክለብ እንደ ሚሰበሰብ መገመት ቀላል ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ሌሎች የገቢ ምንጮች በየዞኑ በአማካይ 3 ከረንቡላዎች አሉ፡፡ የአንዱ ከረንቡላ ዋጋ በወር ከ850-1000 ብር ሲከራይ ሁለት ሁለት ቴኒስ መጫወቻ ያለ ሲሆን በየዞኑ የአንዱ ዋጋ ከ450-600 ብር ነው፡፡ በየወሩ ከተለያየ እደጥበብ ስራዎች ቀረጥ ከየዞኑ በወር በአማካይ ከ3500-5000 በየወሩ ይሰበሰባል፡፡ የሕብረት ሱቅ የሚገኝ ትርፍ በየዞኑ ከ6000-7500 ብር ይደርሳል፡፡

እንግዲህ እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት የገቢ ማስገኛ ዘርፎች በእስር ቤቶቹ መተዳደርያ ህግ መሠረት እስረኛው እራሱ በሚመርጣቸው እስረኞች ተወካዮች ወይም አጠቃላይ ኮሚቴ አማካይነት የሚተዳደሩና የሚሰበሰበው ገቢ ለእስረኛው የተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለሕክምና፣ ለትምህርት፣ ለሕግ አገልግሎት ለምግብና አልባሳት ድጐማ ለሳሙና ምላጭና ሌሎች የመፀዳጃ መሳርያዎች ግዥ እንደሚውል ይደነግጋል ሆኖም ግን ለይስሙላ እስር ቤቱ የፈቀደውን ግለሰቦች እያደራጀና በነዚህ ሰዎች አማካይነት ይህን ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን ከዚህም ለእስረኛው አገልግሎት እንዲሰጥ ገንዘብ ተመድቦ አይተንም ሰምተንም አናውቅም፡፡ እንግዲህ ይህ ከላይ የጠቀስኩት የገንዘብ መጠን በቃሊቲ ብቻ በወር የሚሰበሰብ ሲሆን በሌሎች እስር ቤቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ይሰበሰባል፡፡

ሌላው ከሙስና ይልቅ አስከፊው ነገር ደግሞ ማንም ኢትዮጵያዊ የሆነ በነዚህ ክበቦች ሆነ ከረንቡላ አሊያም የህብረት ሱቅ አገልግሎት ለመስጠት በሚወጣው ጨረታ ተወዳድሮ ቢያሸንፍ መስራት ያለመቻሉ ሲሆን ምናልባት የአንደኛ ዜጐች እጥረት አጋጠመ በወቅቱ ያሸነፈ ግለሰብ ለነሱ (ለእስር ቤቶቹ አመራሮች) ጥቅም የማያጋራና ወሬ የሚያመላልስ ከሆነ እንዲሰራ ይፈቀድለታል፡፡ ይህ ደግሞ አዲስ የባለጊዜዎቹ ሰው እስኪመጣ ብቻ ነው፡፡

ይህ ከላይ የጠቀስኩት እኩልነት ስለ ማስፈንና ስለ ኪራይ ሰብሳቢነት መጥፎነት ጠዋት ማታ ለሚዘምረው ኢህአዴግ ከፍተኛ መኮንኖች የሚፈፅሙት አሥነዋሪ ተግባር ነው፡፡ ሦስተኛው የገቢ ምንጭ በእስር ቤቱ ያሉ ባለ ሀብቶችና በእስር ቤቱ ያሉ ሀብታም ያሰራቸው እስረኞች ናቸው፡፡

ኢህአዴግ ባለፉት አመታት እጅግ በጣም ብዙ ሀብታሞችን ማሰሩ ለነዚህ ህጋዊ ሌቦች ጥሩ እድል ሆኖዋቸዋል፡፡ በተለይ አራጣ አበዳሪዎች የአዲስ አበባን መሬት ቸረቸሩ በሚል የታሰሩ የሪል ኢስቴት ባለቤቶች መዕንዲሶች ወርቅ ያጭበረበሩ ቅሸባ እንደ ታምራት ገለታ ያሉና ሌሎችም እንደ አጋጣሚ እነኚህ ግለሰቦች ሁለት አመት በማይሞላ ግዜ ተሰብስበው የታሰሩ በመሆኑ ከጥበቃ አንስቶ እስከ ከፍተኛ አመራር ሎተሪ የደረሳቸው ያህል ተደስተዋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በ100 ሚሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ በልተዋል በሚል በሙስና የተከሰሱ በታክስና ቫት ማጭበርበር የተከሰሱ ጅምላ ነጋዴዎች አስመጪና ላኪዎች ይገኙበታል፡፡

በቃሊቲ ገንዘብ ስድስትና ከዚያም በላይ የስሜት ህዋስ ነው፡፡ ገንዘብ ያለውና ገንዘብ የሌለው እኩል አይታይም፡፡ ገንዘብ ያለው በሰበብ አስባቡ ታጅቦ ከተማ ሲመላለስና በየቀኑ ሪፈር በሚል ሰበብ እየወጣ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ሲውል ገንዘብ የሌለው ግን ቢታመም አዛኝ የለው፤ ሪፈር ቢባል ነዳጅ የለም ወይም አጃቢ የለንም በሚል ተልካሻ ሰበብ ሕክምና ይከለከላል፡፡

ገንዘብ ያለው የግል ላፕቶፕ ኮንፒዩተር አስገብቶ ሲጠቀም፣ ሞባይል እንደ ልቡ ሲጠቀም፤ ጫት ዊስኪና የግል ዲቪዲ ሲገባላት ድሃው ግን ለቤተሰቡ ደብዳቤ ፅፎ እንኳን በሰንሱር ምክንያት ይህን ሰርዝ ይህን ቀንስ ይህ ማለት እንዲህ ሊሆን ይችላል እየተባለ ይሰቃያል፡፡

ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ እንዲሉ በቃሊቲ ገንዘብ ካለና ፖለቲካቸው ካልተነካ የተፈለገው ድርጊት ሁሉ ይከናወናል፡፡ ሀብታሙ ዊስኪ አስገብቶ ሲጠጣ ደሃው ንፁህ ውሃ ታሽጐ ቢመጣለት አይገባለትም፡፡ሀብታሞቹ ይህን አገልግሎት በማግኘታቸው ለአፀፋው ቲንሽ ቤት ጀምሬ ቆርቆሮ አነሰኝ ቤት እንዳልሰራ ሲሚንቶ ተወደደ ወዘተ እየተባሉ በሚሰጡት ገንዘብ ከG+2 እስከ G+4 ቤት የገነቡ ሁለትን ሦስት ተሳቢ ኤሮትራከር የገዙ

ወደ ገጽ 18 ዞሯል

# የመረራ ትንቢትና የኑሮ ውድነቱ



## መንግስት የኑሮ ውድነቱ ህዝቡ ሊሸከመው ከሚችለው አቅም በላይ መውጣቱን የሚረዳ ቢሆንም የደህንነት ኃይሉን በማጠናከር በብሶት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ህዝባዊ ቁጣዎችን ለማፈን በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ኢህአዴግ በመሬት ባለቤትነት ዙሪያ ከዚህ ቀደም ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ጠንካራና ቀጠን ያለ ምላሽ "መሬት የሚሸጠው ወይም የሚለወጠው በመቃብራችን ላይ ነው" የሚል መሆኑ አይዘነጋም፡፡ በመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ እንደሚያምን ምሎ ተገዝቶ የሚናገረው ገዢ ግንባር የራሱን ፖለቲካዊ አቋም የሚቃረን አመለካከትን ለመቀበል ‹‹በእኔ መቃብር ካልሆነ›› በማለት መናገሩ ለተቃራኒ ሃሳብ ቦታ እንደሌለው ማሳያ ነው፡፡ ገዢው ግንባር ከያዛቸውና ከቆረበባቸው አመለካከቶች ሌላኛው የአገሪቱን አመታዊ እድገት የሚያመላክትበት ቁጥር ነው፡፡ ከምርጫ 1997 በኋላ አገሪቱን በየአመቱ 11 ከመቶ አሳድጊያታለሁ ማለትን መለያው አድርጎታል፡፡ የግንባሩ ቁንጮ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የተናገሩትን ነገር እንደወረደ በመቀበል እንደ ገደል ማሚቱ የሚያስተጋቡ በቀቀኖችም የአመታዊ ምርት እድገቱን ከ11 በመቶ ሳያንሱና ሳያስበልጡ በየዕለቱ በቁጥጥራቸው ስር ባደረጓቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ይደሰኩሩናል፡፡

መንግስት ‹‹ አገሪቱን በእድገት ጎዳና ላይ እንድትራመድ አድርጊያለሁ›› በማለት በየዕለቱ በልሳኖቹ ከሚደሰኩረው ውጪ የዜጎች ህይወት በድህነት አረንቋ እየተዘፈቀ፣ ወጣቶች ‹‹ ሞትን ቁጭ ብለን ከምንጠብቀው እርሱ ወዳለበት ብናመራ ይሻለናል›› በማለት በየአቅጣጫው ስደትን ተያይዘዋል፡፡ መንግስት ግን በየዕለቱ የነዋሪዎቹን ዕለታዊና አመታዊ ገቢ ያላገናዘበ የምርት እድገቱን በየአጋጣሚው በመደስኮር ልማታዊ መንግስት አድርገን እንድንመለከተው እየወተወተን ይገኛል፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በዚህ አመት የኢኮኖሚ ግሽበቱን ወደ አንድ ዲጂት በማውረድ የዋጋ ግሽበቱንና የኑሮ ውድነቱን በቁጥጥር ስር እንደሚያውሉት ነግረውን ነበር፡፡ ከመለስ በፊት የነበሩት የአገሪቱ ርዕሰ ብሄር መንግስቱ ኃ/ማርያም ‹‹ተፈጥሮን በቁጥጥራችን እናውላለን›› ይሉን እንደነበር ሁሉ መለስም ቁጥር ባለመፍራት ይሁን ባለማወቅ ‹‹ ግሽበቱን እንቀንሳለን›› ብለውን ነበር፡፡ መንግስቱ ተፈጥሮን መቆጣጠር ሳይችሉ ወደ ሀራሬ እብስ እንዳሉት ሁሉ መለስም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ግለት ተሟሙቀው ግሽበቱን እናወርደዋለን በማለት ፎክረው ነበር፡፡ ነገር ግን ግሽበቱ ወደ ላይ መመንደጉን ማሳየት በጀመረበት ቅጽበት መለስ ላይመለሱ ወደላይኛው ቤት ሄደዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሴንትራል ስታስቲክስ ኤጀንሲ በየወሩና በየአመቱ የአገሪቱን የግብይት ሪፖርት በድረ ገጹ በማቅረብ መረጃዎችን ከገዢው ፓርቲ ቅኝት አንፃር ያቀርባል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ እምነት የሚጣልበትን ተቋም ማግኘት ፈተና የሆነውን ያህል ስታስቲክስ ኤጀንሲውም በብዙዎች ዘንድ የሚያወጣቸው ሪፖርቶች በነፃና ገለልተኛ ጥናት የተደገፉ ስለመሆናቸው ጥርጣሬ ነግሷል፡፡ ለዚህ አይነተኛ ማስረጃ የሚሆነን ኤጀንሲው በእለት ግብይት ውስጥ የሚቀርቡ ምርቶችን ዋጋ በማስመልከት የሚያቀርባቸውን ዝርዝሮች በመመልከት በድረ ገፁ በተጠቀሰው ዋጋ ምርቶቹን ለመሸመት ወደ ገበያ የሚወጡ ሰዎች የሚያጋጥማቸው ተቃራኒው መሆኑ ነው፡፡ ኤጀንሲው የምርት ውጤቶችን ዋጋ በመቀናነስ ከገዢው ፓርቲ አገሪቱ አድጋለች ከሚለው አቋሙ የማይጋጭ ምዘና ለማቅረብ በመታተሩ ወይም ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ጫና ያለበት በመሆኑ የተነሳ ከእውነታው የተጣረሰ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ይህንን ፍረጃዬን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ያህል ኤጀንሲው በሐምሌና በነሐሴ ወራት ያወጣቸውን ሪፖርቶች እንመልከት፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ የግሽበት መጠን ከወር ወር ከፍተኛ የቅነሳ መሻሻል እያሳየ ነው›› የሚለው ሪፖርቱ ‹‹በግንቦት ወር የነበረው ግሽበት 25% የነበረ ሲሆን በሰኔ ወር ወደ 20.9% ወርዷል፡፡›› በማለቱ ሳይወሰን ‹‹ የምግብ ዋጋ በግንቦት ወር የ29.2% ጭማሪ አሳይቶ የነበረ ሲሆን በሰኔ ወር ወደ 21.5% ቀንሷል›› ብሏል፡፡ ባለፈው አመት የካቲት ወር ላይ 32% የነበረው የአገሪቱ አመታዊ የግሽበት መጠን በኤጀንሲው ትንበያ መሠረት በመጪው ህዳር ወር ወደ አንድ ዲጂት የግሽበት መጠኑ ይወርዳል፡፡›› ኤጀንሲው ከሚያስቀምጣቸው የግሽበት መጠንን የሚገልጹ ቁጥሮችና የሸቀጦች ዋጋ ንረት በተቃራኒው የሸቀጦች ዋጋ በታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረሱ የወቅቱ የአገሪቱ የገበያ ውሎ ደረቱን ገልጦ ይናገራል፡፡

መንግስት የኑሮ ውድነቱ ህዝቡ ሊሸከመው ከሚችለው አቅም በላይ መውጣቱን የሚረዳ ቢሆንም የደህንነት ኃይሉን በማጠናከር በብሶት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ህዝባዊ ቁጣዎችን ለማፈን በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ መንግስት ቁጣዎችን በመስጋት ማምለጫ መንገድ በማዘጋጀት ራሱን ከተጠያቂነት ለማውጣት በዋናነት እየተጠቀመበት የሚገኘው ሌላኛው ስልት ነጋዴውን ከሸማቹ ማጋጨት ነው፡፡ ለኑሮ ውድነት መባባስ ቤንዚን ያርከፈክፋሉ በማለት ነጋዴዎችን በተለይም ለምግብ የሚውሉ ምርቶችን የሚያቀርቡትን በማዋከብ በማሰርና የንግድ ተቋሞቻቸውን በመዝጋት ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያችን በየትኛውም የድርቅ ዘመን በመጠነኛ ዋጋ ይሸመት የነበረው ጤፍ ሳይቀር ለገበያ የሚቀርብበት ዋጋ የሚቀመስ አልሆነም፡፡ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ጤፍን ለገበያ የሚያቀርቡ ነጋዴዎችን የስንግ በመያዝ በተመን እንዲሸጡ እያደረጉ ነው፡፡ በመሰሰረቱ መንግስት የሚገልጸው አመታዊ እድገት ከዜጎች አመታዊና ዕለታዊ ገቢ ጋር የተሰናሰለ ቢሆን ኖሮ ሸማቹ ለኑሮ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን ለመሸመት ባልተቸገረ ነበር፡፡

መንግስት ለጊዜው ራሱን ከህዝባዊ ቁጣ ለማዳን ከሚወስደው እርምጃ ውጪ ህዝቡን ከተጫነበት የኑሮ ውድነቱ በቋሚነት ሊያወጣው የሚችልን አማራጭ ሲያቀርብ አይታይም፡፡ የመለስ አድናቂዎች ሟቹን ጠቅላይ ሚኒስትር "የልማት አርበኛ" በማለት ሲያወድሷቸው ቢቆዩም ባለፉት 21 ዓመታት አገሪቱ በምግብ ሰብል ራሷን መቻል ተስኗት የውጪ እጆችን ለእርዳታ መዘርጋት ስትጠብቅ ኖራለች፡፡ ገዢው ግንባር የርሃብተኞችን ቁጥር ለፖለቲካ ፍጆታው በማሰብ በመቀነስ ምግብ የሚያሻቸውን ዜጎች በመደበቅ ከኢንተርናሽናል ኮሚዩኒቲ ጋር ሌባና ፖሊስ ሲጫወት መቆየቱ አይዘነጋም፡፡

ከዚህ ቀደም መንግስት ገበያን ለማረጋጋት በማሰብ በተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ተመን ማውጣቱ ይታወሳል፡፡ ተመኑን በኃይል በመጫን ገበያውን ለማረጋጋት ቢሞከርም ተመን የወጣላቸው ሸቀጦች ገበያ ውስጥ መገኘት አልቻሉም፡፡ መንግስትም ያለ ጥናት በጭፍን የወሰደው እርምጃ የትም እንደማያደርሰው በመገንዘብ የተመን ዋጋውን ለማንሳት ተገልዷል፡፡ አሁን ባለው የገበያ ዋጋ በተለይም ለምግብነት የሚውሉ ምርቶች የሚቀመሱ አልሆኑም ከ1000 ብር በታች ይሸመት የነበር ጤፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ 1800 ብር ደርሷል፡፡ የሌሎች ሸቀጣሸቀጦች ዋጋም በአገሬው የመግዛት አቅም የሚደፈሩ አይመስሉም ‹‹የኢትዮጵያን ህዝብ በቀን ሦስት ጊዜ እናበላዋለን፡፡›› በማለት ተስፋን የገባልን ገዢ ግንባር አንድ ጊዜ መብላት ቅንጦት ወደ መሰለበት ደረጃ አድርሶናል፡፡ በምርጫ 97 የፓርቲዎች ክርክር ወቅት ዶክተር መራራ ጉዲና ‹‹የተራበ ህዝብ የሚበላውን ሲያጣ መሪዎቹን ይበላል፡፡››ማለታቸውን አስታውሳለሁ፡፡ መንግስት በሚቆጣጠረው የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ውስጥ የሚያቀርበውን የገበያ ውሎና የኑሮ መመቻመች መሬት ላይ ፈልገን ባለማግኘታችን ‹‹የቴሌቪዥኗን ኢትዮጵያ አሳዩን›› ማለታችን አይቀርም፡፡ እርግጥ ነው ለቴሌቪዥኗ ኢትዮጵያ ፍጆታ የዋለ ዜጋ የሆዱን በሆዱ ችሎ በአደባባይ የተደሰተ መስሎ መቅረቡ መንግስትን ያሞኘውም ይመስለኛል፡፡ የማጀትን እውነታ አደባባይ ለማውጣት መነሳሳቱ የተፈጠረ ዕለት ግን የመራራ ትንቢት ቤት ይመታ ይሆናል፡፡





# የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ብሔራዊ ምክር ቤት

ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማፈን ለሚከሰተው አደጋ ኃላፊነቱን የሚወስደው ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ነው
ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/
ኤዲቶሪያል ቦርድ የተሰጠ መግለጫ

የፓርቲያችን ልሳን የሆነችው ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ በአገሪቱ ሕግ መሠረት የተቋቋመችና "የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት እንዲሆን እንታገል" በሚል መሪ ቃል ከሐምሌ 2003 ዓ.ም ጀምራ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በማንሳት ለፓርቲው አባላት፣ ደጋፊዎችና ለሰፊው ህዝብ የምትደርስ ናት፡፡ ምንም እንኳ "የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ" በርካታ ግድፈቶች ያሉበት ቢሆንም ይህን አዋጅ ለማውጣት ያስፈለገበትን ምክንያት በመግቢያው እንደሚከተለው ተገልጧል "መገናኛ ብዙሃን አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ በሕዝቡ መካከል ነፃ የሐሳብና የመረጃ ልውውጥን የሚያመቻችና ዜጎች በነፃ መረጃና አስተያየት ለመሰብሰብ፣ ለመቀበልና ለማስተላለፍ ያላቸውን መብት ሙሉ በሙሉ እንዲያረጋግጡ የሚያስችላቸው ጤናማ የመረጃ ስርዓትና ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ የህዝብ ውይይት መድረክ በመሆን ለማገልገል ነፃ የመገናኛ ብዙሃን ህልውና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣" የሚለው ሀሰብ ይገኝበታል፡፡

ይሁን እንጂ በአዋጁ ላይ የተመለከተው እና በተግባር በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ የተፈፀመው ድርጊት አንዳችም የህግ ጥሰት ሳትፈፅም ወይም መፈፀሟ ሳይገለፅ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ጋዜጣዋን አላትምም ብሏል፡፡ ይህ በአዋጁ መግቢያ ላይ የሰፈረውን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ሁኔታው የሚያሳየው መንግስት ቃሉና ተግባሩ ምን ያክል ተቃራኒ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ላወጣው ህግ ታማኝ አለመሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የነፃ ፕሬስ አስተዋፅኦ ለአንት ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ቀላል የማይባል ሚና አለው፤ ለዚህም ይመስላል ቶማስ ጄፈርሰን «ያለ ነጻ ፕሬስ ከሚኖር መንግስት ያለ መንግስት የሚኖር ነጻ ፕሬስ እመርጣለሁ፡፡» ያለው፡፡

እንደሚታወቀው ለአንድ አገር የዴሞክራሲ ግንባታ ምሰሶ ከሚባሉት አንዱ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ነው፡፡ በአገራችን ይፋዊ በሆነ መልኩ የፕሬስ ውጤቶች እየታተሙ ገበያ ላይ መዋል ከጀመሩ ሁለት አስርት አመታት የተቆጠሩ ቢሆንም በበርካታ ችግሮችና ውጣ ውረዶች የተሞሉ ጊዜያቶችን አሳልፈዋል፡፡ መንግስት በዘረጋውና የሕዝብ አንጡራ ሀብት በሆነ ገንዘብ የሚተዳደረው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የግል ነፃ ፕሬሶች ላይ ግዙፍ የፕሮፓጋንዳ ናዳ እያወረደና ራሱ እየተናገረ የራሱን ንግግር ማንቆለጳጰስ ከጀመረ 21 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በዚህች አገር ጋዜጠኞች የሚዋከቡት፣ የሚታሰሩት፣ የሚሰደዱባትና ጋዜጦች ከገበያ የሚወጡት ትክክለኛ ስራቸውን ስለሚሰሩ ብቻ ነው፡፡ ሕዝብ አማራጭ ሚዲያ ሊያገኝ ይገባል፡፡ መጻፍ፣ ሐሳብን መግለጽና መናገር የሚሉት ጉዳዮች ለይስሙላና "ዴሞክራሲያዊ ነን" ለማሰኘት ብቻ ሊሆኑ ጨርሶ አይገባም፡፡ ዜጎች የተለያዩ ሐሳቦችንና አመለካከቶችን እንዳያገኙ ለማድረግ የአፈና መዋቅርን በተለያየ መንገድ ማጥበቅ ኋላ መበጠስን ያስከትላል፡፡

ሕዝብ የራሴ የሚላቸውን ፍላጎቶች ለማሟላት ከአድሎ ነፃ የሆነ ፣ ለሕግ የበላይነት ተገዢ ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት መንግስታዊ ስርዓት ይፈልጋል፡፡ ፖለቲካዊ መረጋጋት ሊያሰፍን የሚችለው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚመሰረተው፤ ሞያተኛ ፣ ቀልጣፋና ገለልተኛ የሆነ የፍትህ ተቋም የሚኖረው፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህን ሁሉ በጐ ነገሮች ይዞ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚሰራና መስዋዕትነት እየከፈለ የሚታገል ንቁ ሕዝብ ለመፍጠር የሚቻለው የነፃ ሚዲያ መኖር ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ነፃ ጋዜጦችና ጋዜጠኞችን ለማጥፋት በተግባር የታየው ኢ-ፍትሐዊ አካሄድ ጋዜጠኛው ላይ ጫና መፍጠር፤ አለፍ ካለም የፈጠራ ክስ በማዘጋጀት ጋዜጠኞቹን ወህኒ መወርወር ነበር ፡፡ ዛሬ ዛሬ ሁኔታዎቹ ከዚህ የተለወጡ ይመስላሉ፡፡ ቅድመ ሳንሱር በሚመስል መልክ ኢ-ሕገ መንግስታዊ በሆነ መንገድ ማተሚያ ድርጅቱ አገልግሎት ሰጭ መሆኑ ቀርቶ መብት ሰጭና ነሽ በመሆን ጋዜጣችሁን አላትምም ለማለት በቅቷል፡፡

ይህ በፓርቲው ልሳን ላይ የተፈፀመው ህገ ወጥ ድርጊት የፓርቲያችንን ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ከማገዱም በላይ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 31 የተደነገገውን "የመደራጀት መብት" መጨፍለቁን ያረጋገጠበት ነው፡፡ ልሳኗ የሕዝብ ነፃ አመለካከትና አስተያየቶች የሚንሸራሸሩባት፣ የፓርቲያችን ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶች አሰራሮችና አጠቃላይ እንቅስቃሴውን ለአባላቱ፣ ለደጋፊውና ለሕዝቡ የሚያስተላልፍበት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ሐሳብ ከላይ ወደታች እንዲሁም ከታች ወደ ላይ የሚንሸራሸርበት ባጠቃላይ ፓርቲው መዋቅሩን ለማስፋፋትና አባሉን ለማብዛት የሚጠቀምበት አንዱና ዋነኛው መሣሪያ በመሆኗ ምክንያት ድርጊቱ የፓርቲያችንን የመደራጀት መብትም የገደበ ሕገ ወጥ አካሄድ ብቻ ሳይሆን የመድበል ፓርቲ ስርዓትንም የሚያፈርስ ነው፡፡

ሁኔታው በመከፋቱና የአፈና ስልቱ አእምሮን እንዳያስብ፣ አፍ እንዳይናገርና እጅ እንዳይጽፍ እያደረገ ከመሆኑም ባሻገር ፓርቲያችን አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን ከሕግ ውጭ የመዝጋት ያህል ሆኖ ተሰምቶናል፡፡ ህገ ወጡ ድርጊት ከተፈፀመበት ዕለት አንስቶ በኛ በኩል፡-

→ ለኢፌዴሪ ጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት
→ ለኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር
→ ለኢፌዴሪ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
→ ለኢፌዴሪ ብሮድካስት ባለስልጣን
→ ለኢፌዴሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
→ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን
→ ለብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ስራ አመራር ቦርድ

በጉዳዩ ዙሪያ ምላሽ እንዲሰጡንና የተወሰደውን ኢ-ህገ መንግስታዊ እርምጃ እንዲቀለበስ በደብዳቤ ብንጠይቅም አንዳቸውም ምላሽ ሊሰጡን አልቻሉም፡፡ ይህም በመሆኑ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅትን በፍ/ቤት የምንከስ ሲሆን በተጨማሪም በህገ መንግስቱ የተፈቀዱትን የትኞቹንም አይነት ህጋዊ እርምጃዎች ለመውሰድ የምንገደድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ፍኖተ ነፃነት ላይ የተጣለው ህገ ወጥ ማዕቀብ እስካልተነሳ ድረስ ዘመቻ ነፃነት ይቀጥላል!

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ

መስከረም 22 ቀን 2005 ዓ.ም አ/አ

# የቃሊቲና ቂሊንጦ ወህኒ ቤቶች . . .

ከገጽ 15 የዞረ

ከ5-19 ሚሊዬን ብር ባንክ ያስቀመጡ ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖች ሲኖሩ የነዚህ ሰዎች ወርሃዊ ደሞዝ ግን ከ2000 -30000 አይበልጥም። በዚህ የደሞዝ መጠን ልጆች አስተምሮ ቤተሰብ አስተዳድሮ በባንክ ቆጥቦ ለ5 ሚሊዬን ብር በላይ ማጠራቀም የማይታሰብ ነው።

ከከፍተኛ መኮንኖቹ በታች ያሉ የዞን ተጠሪ (ኋላፊዎች) ያቅማቸውን ያህል የሚሰርቁ ሲሆን ይህም እንደ ሚከተለው ነው። አንድ እስረኛ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ሲገባ ከሚገጥሙት ፈተናዎች አንዱ እንደ ሰው ተቆጥሮ መኝታ የማግኘት መብቱ ይነፈጋል። ይህ የሚሆነው ደግሞ ከላይ እንደ ጠቀስኩት በየዞኑ ኃላፊ ተብለው የተመደቡት የኢንስፔክተርና ከዛበታች ማእረግ በትከሻቸው ላይ የተሸከሙ የስርዓቱ ሎሌዎች ነውረኛ ተግባር ምክንያት ነው። ይህ ማለት እስረኛው ወደ እስር ቤቱ ሲመጣ እንደየ አመጣጡ ተገቢውን የመኝታ ስፍራ ማግኘት ሲገባው አልጋና የተሻለ የመኝታ ስፍራ ለማግኘት ከብር 500- 3000 ብር ይጠየቃል። ይህ የሚሆነው በየዞኑ ከመኮንኖቹ ጋር ተመሳጥረው (ተሻርከው) በሚሰሩ የእስረኛ አስተዳደሮች አማካይነት ሲሆን የሚሸጡትን አልጋ ገንዘብ ሰብስበው መንግስት ከኢትዮጵያ ህዝብ መቀነት ፈትቶና ገንዘብ ሰብስቦ ደሞዝ ለሚከፍላቸው መኮንኖች ሲያስረክቡ እንደየ ድርሻቸው ኮሚሺን ያገኛሉ።

እነኚህ አልጋ የሚሸጡ እስረኞች አብዛኞቹ አንባቢዎቼ የምታውቃቸው ሲሆኑ ወታደር የነበሩ የባለሥልጣናትና የመንግስት ተቋማት የነበሩና በነበራቸው ኃላፊነትና በእጃቸው በነበረ መሣርያ ተጠቅመ የአዲስ አበባን ባለ ሀብት በመዝረፍ ያንገላቱና በሚሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ ከባንክ የዘረፉ ናቸው። እስር ቤት ከገቡ በኋላም ለሚናገሩት ቋንቋ ተጠቅመው የእስረኛ አስተዳደር የእስረኛ ስነ ስርዓት አስከባሪ ወዘተ እየተባሉ እስረኛውን ሲጨቁኑና ሲያንገላቱ በአንፃሩ ከዩኒቨርስቲና ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ገበታቸው ኦነግ፣ አርበኛ ግንባር፣ ቅንጅት፣ ግንቦት ሰባት. . . እየተባሉ ታንቀው እስር ቤት የገቡ የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች ያለ እዳቸው በየጭለማ ቤቱ ይማቅቃሉ።

## እንደገና ቃሊቲ ወህኒ ቤት

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና በእያንዳንዱ ቀን ከ70-100 እስረና ወደ ቃሊቲ ወይኒ ቤት ከአሥሩም ክፍለ ከተማና ከማእከላዊ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀልና ትራፊክ አደጋ ምርመራ በተለምዶ ስሙ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ይመለሳል። ከዚህም 90% የሚሆነው ሳይፈረድበት በቀጠሮ ወደ ቃሊቲ የሚመጣ በመሆኑ በቀጥታ ወደዞን 3 ይገባል (ዞን 3 ማለት በቃሊቲ ከሚገኙ ዞኖች ያልተፈረደባቸው በቀጠሮ ላይ ያሉ እስረኞ የሚቆዩበት ዞን ነው)። ይህ በመሆኑም ዞን 3 ገብቶ አልጋ ማግኘት ወይም መሬት ተመቻችቶ መተኛት የማይታሰብ ነው። ገነት ካለ ግን አልጋ ላይ የነበረ እስረኛም ቢሆን ከአልጋ ወርዶ አዲስ ለመጣው ከፋይ እንዲሰጥ ይደረጋል። በተለይ የሚከፈለው ገንዘብ መጠን ከፍ ባለ ቁጥር እንክብባቤው ጥሩ እየሆነ ይመጣል። በአንፃሩ ደግሞ በየቀኑ ወደ ዞኑ የሚገባው የሰው ሃይል ከፍተኛ በመሆኑ ከመግቢያ በር እስከ መፀዳጃ (ሽንት ቤት) ድረስ ለመገላበጥ እንኳ በማይመች ሁኔታ በአንድ ጐን ተኝተው የሚያድሩ ድሃ ዜጐች ቁጥር የትየለሌ ነው። ይህ ሁሉ ፍጡር ጐኑ ታሞ ገሚሱ ተቀምጦ ሲያድር ግን ከ10-15 የማይንሱ አልጋዎች ለነገ ገቤ መጠባበቂያ ሲባል ባዶ ያድራሉ።

ሌላው እጅግ የሚያስከፋው ጉዳይ ደግሞ ዛሬ ኢህአዴግ ሃገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረ ከ21 አመታት በኋላም ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያዊ የሚበልጥበት መስፈርት መኖሩ በንጉሱ ወይም በደርግ ዘመን ሳይሆን ዛሬ በኢህአዴግ ዘመን መሆኑን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ቃሊቲን ማየት ነው።

አንድ በጣም የታመመና ሆስፒታል መተኛት የሚገባው ህመምተኛ ወይም ምርመራ ላይ ከመጠን በላይ ተደብድቦ መራመድ የማይችል እስረኛ ሌላ ጤነኛና ወጣት የሆነ ትግርኛ ተናጋሪ እኩል ቢመጡ ትግርኛ መናገሩ ብቻ ለትግሬው ቅድሚ ያሰጠዋል። አልጋ ወዲያው ይሰጠዋል፤ ገንዘብ አይጠይቅም፤ በጊቢው ውስጥ በሌላ ኢትዮጵያዊ ተይዞ የነበረ የገቢ ማስገኛ ክበብ፣ ከረንቡላ፣ የህብረት ሱቅ እና ሌሎችም ተቀምቶ ይሰጠዋል። እንዲሁም ወደ እስር ቤቱ በመጣ በአጭር ቀን ውስጥ የእስረኛ አስተዳዳሪ ተደርጐ ይሾማል። ይህ ሁሉ ሲከናወን በእስር ቤቶቹ የተለመደ ተግባር በመሆኑ ጥያቄ የሚያነሳ የለም።

ሌላው ጉዳይ ደግሞ መንግስት 24 ሰዓት ሙሉ ጥፋተኞችን የማስተማርና ብቁ ዜጋ የማድረግ ፖሊሲ እንደሚከተል በETV እየገለፀ ባለበት ወቅት ቃሊቲ ያሉ የፖሊስ መኮንኖች እስር ቤቱን የመጠጥና የጫት የሐሺሽ መነገጃ ማእከል በማድረጋቸው በህግ የሚጠይቃቸው አንድም ባለሥልጣን ወይም ህግ የለም።

ይህ የሐሺሽና የሲጋራ ትንሽ ስለቂሊንጦ በቃሊቲ ብቻ የተወሰነ አይደለም እንደ ቃሊቲ ሁሉ በቂሊንጦና በዝዋይ እስር ቤቶች ይካሄዳል ለዛሬ ግን በጥቂቱ የቂሊንጦ ወይኒ ቤትን አስጐበኛችኋለሁ። የቂሊንጦ እስር ቤት ሶስት ዞኖች ያሉት ሲሆን በያንዳዱ ዞን ከ550-650 እስረኞች ይገኛሉ በአጠቃላይ በ3ቱም ዞኖች የሚገኘው እስረኛ ቁጥር ከ11750 በላይ ነው።

አብዛኞቹ የቂሊንጦ እስር ቤት አመራሮች በሙሉ ከቃሊቲ ወደ ቂሊንጦ የተዘዋወሩ በመሆኑ የውንብድናውን ስራ ተክነውበታል። በቂሊንጦ የፈጠሩት የገቢ ምንጭ የተለየ ነው። በዚህም መላውን እስረኛ ሰብስበው ሲጋራ ለጤና ጠንቅ መሆኑን እና ከኢኮኖሚ አንፃርም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ካስረዱ በኋላ ሲጋራ ማጨስ እንዲቆም መወሰኑን ገልፀዋል። ይህ ሲሆን ግን መፃኢ እድላቸው ምን እንደሆነ ቀድመው የገመቱ እስረኞች ነበሩ። ከሣምንት በኋላ ሲጋራ እንደ ሚጀመርና 60 ሳንቲም የነበረውን ሲጋራ በ10 ብር እንደሚገዙ የገመቱ ነበሩ።

የተገመተውም አልቀረም ሣምንት ሳይሞላ ቂሊንጦ ሲጋር እንደ ልብ ይጨስ ጀመር። የአንድ ሲጋራ ዋጋ ከ12-15 ብር የአንድ ፓኬት ሲጋራ ዋጋ (20 ፍሬ) ከ240-300 ብር ተሸጠ። ይህ ማለት አንድ ካርቶኒ ሲጋራ 6000 ወደ 100,000 እና ከዛ በላይ አደገ ማለት ነው።

በቀን በአንድ ዞን ከሁለት ስቴካ በላይ ሲጋራ ይገባል። ይህ ደግሞ በ24 ሰዓት ከአንድ ዞን እስከ 3000 ብር ትርፍ ይገኛል ማለት ነው። አብዛኛው እስረኛ አጫሽ ነው የ60 ሳንቲም ሲጋራ በአሥር ብር እየገዛ ያጨሳል። ብቻውን ያልቻለ ለሁለት ለሦስት እየሆነ ያጨሳል ይህ ደግሞ በቀላሉ ለተላላፊ በሽታ እንዲዳረግ በር ይከፍታል።

በአጠቃላይ እስረኛው ላይ በሚፈፀመው ብዝበዛ ማንም ደፍሮ የሚጠይቅ የለም። ቢኖር እንኳ የሚጠበቀው እድል እጁ በሰንሰለት ታስሮ ጭለማ ቤት ይወረወራል። አብዛኛው እስረኛ ለምን ሲጋራ አታቆምም ተብሎ ሊጠየቅ አልቻለም። ባይኖር አቆማለሁ ነገር ግን አጠገቤ እየተጨሰ እንዴት አድርጌ እተዋለሁ ይላል። እድለኛ የሆነ ደግሞ በሽያጩ ይሳተፋል። የእንጀራ ጉዳይ ስለሆነ አልፈረድበትም። ሆኖም ግን ወይ ቸባሬ መሆን አለበት። አሊያም ትግሬ ጓደኛ ሊኖረው ይገባል።

የከፋው ነገር ደግሞ ሲጋራውን አስገብተው የሚሸጡት መንግስት በኃላፊነት መድቦ ያስቀመጣቸው ኃላፊዎች መሆናቸው ነው። ከዚህ መስመር ውጭ ያለ ማንኛውም አካል ቢያደርገው አይደለም ቢያስበው አበቃለት።

ለአብነት ያህል በግንቦት ወር 2004 ዓ.ም ተመስገን አበበ የተባለ እስረኛ እና ተክላይ የተባለ የጥበቃ አባል የሆነ ፖሊስ ሲጋራ ሲቀባበሉ ተያዙ ተብለው ተመስገን አበበ የተባለው እስረኛ በአስከፊ ሁኔታ ተደብድቦ በሰንሰለት ሲታሰር ተክላይ የተባለው ፖሊስ እንደ ህፃን እጁ ወደኋላ ታስሮ ከተገረፈ በኋላ ከስራ ተባሯል። ይህን እውነት ማንኛውም አካል ወደ ቂሊንጦ መጥቶ ተመስገን አበበን አሊያም በወቅቱ ተጠርጥሮ የተደበደበውን እስጢፋኖስ ኃይሉን ማነጋገርና እውነታውን መረዳት ይችላል። ይህ አላይ እንደ ማሳያ የተጠቀሰው እውነታ የሚያመለክተው እኒህ የሌብነት መረብ የዘረጉ መኮንኖች በጥቅማቸው የመጣ ማንንም (የራሳቸውን) ሰው እንኳ ቢሆን እንደ ማይምሩ ይጠቁማል።

በቃሊቲ እስር ቤት ከሚገኙ ዞኖች ዞን 6 እየተባለ የሚጠራው ገቢ በተለምዶ ሰሙ የዱርዬ ዞን በመባል ይታወቃል። እስር ቤቱ እንዲህ ብሎ ይሰየም እንጂ እዚያ ዞን የሚገባው ሁሉ ዱርዬ ነው ማለት አይደለም። ከሌሎች ዞኖች ጋር በአንፃራዊነት ሲታይ ግን ወጣት የሚበዛበት ገቢ ነው። ይህ በመሆኑም በዞኑ አስተዳደሮች ጥሩ የገቢ ምንጭ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ከሚጨስ ሲጋራ ጀምሮ በክርንና በአፍንጫ እስከ ሚወስድ አደንዛዥ እፅ ድረስ እያስገቡ ይሸጣሉ። ይህ ደግሞ የሚፈፀመው ከዞን ኃላፊ መኮንኖች ጋር በሚሰሩ መኖርያቸውን በዚሁ ላደረጉ ተመላላሽ እስረኞች አማካይነት ነው። ጫትና መጠጥ ገንዘብ ላለው ሰው በቀላሉ ይቀርቡበታል።

ይህንን ህገ ወጥ ስራ ለመስራት ቅድሚያ ለትግርኛ ተናጋሪ የሚለው ህግ ሳይፃፍ የተደነገገ ሳይታወጅ በሁሉም አይምሮ የፀደቀ በመሆኑ ተግባራዊ ይደረጋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ቃሊቲ ዞን ሁለትም ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች በሙሉ ይከናወናሉ። ይህ ማለት በሌሎች ዞኖች የለም ማለት ሳይሆን እነዚህ ሁለት ዞኖች ለማሳያ ያህል የቀረቡ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ማንኛውም ይህን እውነት ማጣራት የሚፈልግ አካል በራሱ መንገድ ማጣራትም ሆነ ማጥናት ይችላል።

በአጠቃላይ የሥርዓቱ ሎሌ የሆኑ መኮንኖች የሚፈፀሙት በደል ግፍና ቅሌት ይህ ተብሎ የማያልቅ ሲሆን የስርዓቱና የስረዓቱ ተከታዮች የስብእና መለኪያ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል።

በሚቀጥለው ፅሁፌ የተደራጁ ወንጀለኞች ምሽጋቸውን በእስር ቤት አድርገው ከተማው ውስጥ እንዴት ማጭበርበር እንደሚፈፅሙ የእስር ቤት አዛዦች በዚህ ላይ ያላቸው ሚናና ተሳትፎ እንዲሁ በአንድ የሃገሪቱ ቱጃር ገንዘብ እየተከፈላቸው ስለሚያሰቃዩት ግለሰብ ታሪክ ይዤ እቀርባለሁ እስከዚያው ቸር እንሰንብት!!





# ሙስና በማጋለጣቸው የታሰሩ ወጣቶች በህዝብ የተቃውሞ ትዕይንት ተለቀቁ

ከአዲስ አበባ ሰሜን ምስራቅ በቅርብ ርቀት የምትገኘው የለገዳዲ ለገጣፎ ከተማ መስተዳደር በተፈፀመ ህገወጥ የመሬት ወረራ ቅሬታ ያሰሙ የከተማው ወጣቶች መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከሌሊቱ 11:30 ሰዓት በአካባቢው ፖሊስ ከየቤታቸው ታፍሰው መታሰራቸው ተጠቁሟል። ምክንያቱ ባልተጠቀሰ ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ወጣቶች መኮንን ተስፋዬ፣ ድሪባ ጉዳ፣ ሲሳይ ለማ፣ ገመቹ ወርቁ፣ ጌታቸው ተፈራ፣ ምትኩ ንጉሱ እና እንዳልካቸው መንግስቱ የሚገኙበት ሲሆን ሌሎች ተጠርጣሪዎችም በፖሊስ እንዲያዙ ማዘዣ እንደወጣባቸው ለማወቅ ተችሏል።

የወጣቶቹን መታሰር ተከትሎም አርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም ቁጥራቸው በግምት ከ500 በላይ የሆኑ የከተማው አዛውንት አባቶችና እናቶች እንዲሁም በርካታ ወጣቶች ለገጣፎ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ከጠዋት ጀምሮ እስከተመለስንበት ከቀኑ 10 ሰዓት ድረስ ልጆቻችንን በግፍ አስራችኋልና ልቀቁልን ሲሉ ለማየት ተችሏል። በስፍራው ካገኘናቸው በርካታ አባቶች መካከል መናገርና መስማት የተሳናቸው አቶ ገዛኸኝ መንገሻ በከተማው ባለስልጣናት 4 የተለያዩ የእርሻ መሬታቸው ተነጥቆ ለክልሉ ባለስልጣናት ተሰጥቶብኝ ባዶዬን ቀርቻለሁ፤ የተፈፀመብኝን በደል ለአካባቢው ባለስልጣናት ባሳውቅም እስካሁን መልስ የሚሰጠኝ ባጣ አሁን ለታሰሩ ልጆቻችን የተፈፀመብንን በደል ለህዝብ አሳውቁልን ብለናቸዋል፣ ዛሬ ግን እነኚህን ልጆቻችንን አስረውብናልና እንዲለቀቁን ለመጠየቅ ነው የመጣሁት ሲሉ በአስተርጓሚያቸው ነግረውናል።

በተለይ የመኮንን ተስፋዬ እናት በበኩላቸው ልጃቸውን የፀጥታ ኃይሎች ከሌሊቱ 11:30 ሰዓት መጥተው አፍነው እንደወሰዱት የገለፁልን ሲሆን ወጣት መኮንን በከተመው የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ጋዜጠኛ ሆኖ ተቀጥሮ እየሰራ መሆኑን በማስታወስ "ልጄ የአካባቢው ተወላጅ እንደመሆኑ መጠን የህዝብ ልጅ ነው፣ በህዝብ ላይ በደል የፈፀሙት አሳሪዎቹ ምስጢራችንን አውጥሃል በሚል ባልተገለፀ ምክንያት ስላሳሩብኝ ነው እዚህ የመጣሁት" ሲሉ ገልፀውልናል።

በዕለቱ በስፍራው ያነጋገርናቸው ወጣቶችም ቤተሰቦቻቸው አርሰው ከሚያበሏቸው መሬት ተፈናቅለው ያለመጠለያና ያለምንም የካሳ ቦታ በመቅረታቸው ምክንያት ወላጆቻቸውንና ታናናሽ ወንድምና እህቶቻቸውን ለመጦር ሲሉ ትምህርታቸውን እንዳቋረጡ ተናግረዋል። በተለይ አንድ ወጣት በያዝነው 2005 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ተማሪ መሆኑን ገልፆ አባትየው ስለሞቱ ወላጅ እናታችን 7 ልጆችን ብቻዋን ያለአባት እንኳ እንዳታሳድግ የእርሻ መሬታችን ተነጥቆ ካሳም ሆነ ምትክ ባለመሰጠቱ ትምህርቴን አቋርጬ የእነሱን ህይወት ለመታደግ የቀን ስራ እየፈለኩ ነው ሲል ተናግሯል። አያይዞም አሁን የታሰሩ ወጣቶች ይህንን የመሰለ አሰቃቂና አሳዛኝ በደል በአካባቢው በመፈፀሙ የአካባቢው ወላጆች መንግስት መልስ መስጠት ባለመቻሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳውቁልን ብለው ስለጠየቀቋቸው ነው የታሰሩት፤ እነሱን ካልፈታችሁ አንሄድም ብለን ነው እዚህ የተሰበሰብነው፣ ወንድሞቻችን በግፍ ታስረው እኛ መቀመጥ የለብንም ብለን ነው እዚህ የመጣነው ሲል ገልፆልናል።

በስፍራው የነበረው ህዝብም ወጣቶቹ የታሰሩት መስከረም 24 ቀን 2005 ዓ.ም በደላችንን በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ለህዝብ ስላሳውቁ ነው፤ ባለስልጣናቱ የአካባቢውን ተወላጅ ከመኖሪያ ቦታው በማፈናቀል ምንም ምትክ ቦታም ሆነ ካሳ ሳይሰጡ የገበሬዎቹን ቦታ ለባለሃብት ሸጠውና የአካባቢውና የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት ለራሳቸው ተቀራምተው ለተፈናቃዩ ህጋዊ የሆነ ቦታም ሆነ ካርታ አልሰጡም ሲሉ ምሬታቸውን ገልፀዋል።

የአካባቢው ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ የአካባቢው ባለስልጣናት አቶ ጨምር አልቀባ፣ አቶ ፋንታሁን ታደሰ፣ አቶ ልሳኑ ቱሉ፣ አቶ ታደሰ ዋቅሹሜ፣ አቶ ጌታቸው ነጋሽ እና አቶ ድሪባ ደምሴ ህዝቡ በአስቸኳይ እንዲበተን ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ሰጥተው በመጡበት ኦሮሚያ ኮድ 4 የታርጋ ቁጥር 03703 ተሽከርካሪ በህዝቡ ጩኸት ከቀኑ 8:30 ሰዓት ላይ ተመልሰው ሲሄዱ ለማየት ተችሏል።

በተለይ የከተማው የኦህዴድ/ኢህአዴግ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ጨምር አልቀባ የዝግጅት ክፍሉን ባልደረባ መታወቂያ ነጥቀው ለማምለጥ ሲሞክሩ በህዝቡ አስገዳጅነት ሊመልሱ ችለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የቀድሞው የለገጣፎ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ በላይ ሙላቱ የራሳቸው እንደሆነች በተጠቆመችው የቤት መኪና የተሰበሰበውን ህዝብ እንዲበተን ሲያስፈራሩ ህዝቡ ሌባ፣ ሌባ በማለት ሲጮህ በፍጥነት ከሥፍራው ሸሽተው ሄደዋል።

ስለተጠርጣሪዎቹ መታሰር ጉዳይ በለገጣፎ የሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ኮማንደር ታደሰን ጠይቀናቸው "ወጣቶቹ ተጠርጥረው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተይዘው ታስረዋል፣ ስለተጠረጠሩበት ጉዳይና ስለህጋዊ ሂደት ዝርዝር ለመግለጽ ግን ያልተጠናቀቁ ጉዳዮች ስላሉ ለዛሬ ልገልፅልህ አልችልም፤ አስፈላጊውን ሂደት ከጨረስን በኋላ ግን እገልፃለሁ" ሲሉ ነግረውናል። ነገር ግን ከቀኑ 10:30 ሰዓት የአካባቢውን ነዋሪዎች ካነጋገርን በኋላ ዳግም ወደ ፖሊስ ጣቢያው ስንመለስ የአካባቢው የፍርድ ቤት ዳኛ ሲያስፈራሩ ከነበሩት ባለስልጣናት መካከል ሁለቱ እና አቃቤ ህግ በፖሊስ ጣቢያ ተገኝተው በመመልከታችን አዲስ ነገር እንዳለ ፖሊሶቹን ጠይቀናቸዋል። ፖሊሶችም ዳኛው የተጠርጣሪዎችና ቃል ተገኝተው የተቀበሉ መሆናቸውን እና የዋስ መብት ተከልክለው እስከ ማክሰኞ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም በፖሊስ ጣቢያ እንደሚቆዩ ለማወቅ መወሰኑን ለማወቅ ተችሏል።

በጉዳዩ ዙሪያ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ምንም የደረሰው መረጃ እንደሌለና እንደማያውቅ ባለሙያው አቶ ወርቁ ጫላ ገልፀውልናል። የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የመረጃ ኃላፊ ኮማንደር አበበ በበኩላቸው በከተማው በተፈጠረው ጉዳይም ሆነ በተጠርጣሪዎች ምንም የደረሰ መረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል። ነገር ግን በንጋታው መስከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም. የአካባቢው ህዝብ በድጋሚ ፖሊስ ጣቢያ በር ላይ በመገኘት ቅሬታ ካሰሙ በኋላ የአስተዳደር አካላት ባሉበት ማዘጋጃ ቤት ተሰብስበው ቅሬታቸውንና ምሬታቸውን በመግለፃቸው የዋስ መብት ተከልክለው ለማክሰኞ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም. የተቀጠሩት ተከሳሾች ቅዳሜ መስከረም 26 ቀን 2005ዓ.ም. በ21 ሺህ ብር ዋስ ተለቀዋል። ታሳሪዎቹ መስከረም 29 ፍርድ ቤት ለመቅረብ ቢዘጋጁም በእለቱ ክስ ሳይመሰረትባቸው ቀርቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የከተማው ከንቲባ አቶ መገርሳን ጨምሮ ሌሎች የከተማው ካቢኔዎች በጉዳዩ ዙሪያ እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም. በአንድ ካቢኔ አባል መኖሪያ ቤት መሰብሰባቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

# ለአዳማ ከተማ ነዋሪዎች የተበከለ ውሃ እየተሰራጨ ነው

በቅርቡ ከሀያ ቀናት በላይ የውሃ መቋረጥ አጋጥሟቸው የነበሩት የአዳማ ነዋሪዎች በፍሎራይድ የተበከለ ውሃ እየተሰራጨላቸው መሆኑን ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ አስታወቁ።

ከአዲስ አበባ 100 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በመትገኘውና ከሶስት መቶ ሺህ በላይ ነዋሪ ባላት በአዳማ ከተማ ካለፈው አመት መገባደጃ ጀምሮ በከተማዋ የተከሰተው የውሀ እጥረት አሁን ድረስ አልተፈታም። ውሃ የሚመጣው በአብዛኛው ለሊት ስለሆነ ነዋሪዎቹ እንቅልፋቸውን አጥተው መጠበቅ ግድ ሆኖባቸዋል።

የአዳማ ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓት ለቀናት ሚዘልቅ የውሃ እጥረት ባያጋጥማቸውም በከተማው ውሃና ፍሳሽ መስሪያ ቤት እየተሰራጨላቸው ያለው ውሃ ግን ከፍተኛ የጥራት ችግር አለበት። ነዋሪዎቹ እንደሚሉት በስምጥ ሸለቆ አካባቢ በብዛት የሚገኘው በፍሎራይድ የተበከለ ውሃ በአዳማ በመሰራጨት ላይ ይገኛል።

በከተማዋ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዘጋቢ ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች አብዛኞቹ በፍሎራይድ የተበከለ ውሃ እንደሚጠቀሙ መረጃው የላቸውም። ሆኖም ጥቂት የማይባሉት ቀደም ሲል ለከተማዋ ነዋሪዎች ይሰጥ የነበረው ውሃ በጥርስ ላይ የመበለዝና የመሳሳት እንዲሁም በጀርባ አጥንት ላይ ጉዳት እንደሚያመጣ ያስታውሳሉ። ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ አንድ የከተማው አስተዳደር ኃላፊ ለከተማው ህዝብ በፍሎራይድ የተበከለ ውሃ እየተሰራጨ መሆኑን አምነው "የከተማው ህዝብ ውሃ እንዲያገኝ ማድረግ የመጀመሪያው ስራ ነው። በቀጣይ ጥራቱን የጠበቀ ውሃ የሚሰራጭበት መንገድ እየተፈለገ ነው" ብለዋል። ባለስልጣኑ ይህን ውሃ ለመጠጥ አገልግሎት ይጠቀሙታል ወይ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ለመጠጥ እንደማይጠቀሙት በአጭሩ ተናግረዋል። ከከተማዋ ውሃና ፍሳሽ መሥሪያ ቤት ምላሽ ለማግኘት ያደረግ ነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም።

# ኳሱን ተውልን!



የኢትዮጵያ ስፖርት በሁሉም አቅጣጫ መነቃቃት ውስጥ ይገኛል፡፡ የሴቶችና የወንዶች ብሄራዊ ቡድናችን ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፋቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ከ17 ዓመት በታች በወንዶች እግር ኳስ የቱኒዚያ አቻውን በጨዋታ ብልጫ የረመረመ ቡድን መገንባት ተችሏል፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳትም ሰሞነኛው የአገራችን ጉዳይ እግር ኳስና እግር ኳስ ብቻ ሆኗል፡፡ ሰሞነኛውን ድባብ ተከትሎ የማደምጣቸው ነገሮች ቢሸነቁጡኝ ሃሳቤን ለነከተብ ብዕሬን አሾልኩ፡፡ የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌደሬሽን አመታዊውን የከተማይቱን ክለቦች በእግር ኳስ የሚያወዳድርበትን መርሃ ግብሩን ይፋ ለማድረግና የዕጣ አወጣጥ ስነስርዓቱን በግልጽ እንደሚያከናውን ለማሳየት ለጋዜጠኞች በሸራተን አዲስ እንዲገኙ ጥሪ በማስተላለፉ ወደ ስፍራው አምርቼ ነበር፡፡ ሰባት ክለቦችን የሚያገናኘው "የሲቲ ካፕ" ዕጣ ፍጹም ግልጽነት በተሞላበት ሁኔታ መውጣቱንም በዚህ አጋጣሚ መመስከር እፈልጋለሁ፡፡

በተቃራኒው ግን ምስጋናዬን የማልቸረው ሁነት በሸራተን ያጋጠመኝ በመሆኑም ምስክርነቴን በማኖር ፌደሬሽኑን መሞገት ዳድቶኛል፡፡ በእርግጥ አሁን በማነሳው ኢ-ስፖርታዊ ድርጊት የምከሰው የአዲስ አበባውን የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ብቻ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያን እግር ኳስና የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኖችን ጭምር ነው፡፡ በሸራተን አዲስ የተከናወነውን የዕጣ አወጣጥ ስነ ስርዓት የመሩት ሁለት ጋዜጠኞች ናቸው፡፡ ጋዜጠኞቹ የፌደሬሽኑ አባላት መሆናቸውም በግልጽ ይታወቃል፡፡ መድረክ መሪዎቹ በስፍራው ለታደምነው ሰዎች እየተቀባበሉ በቅርቡ ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የልማት አርበኝነት፣ በስፖርት ዕድገት የተቃጠሉ መሪ ስለመሆናቸውና ስለ ሌሎች ስብዕናዎቻቸው ሰብከውናል፡፡ የተገኘነው በአንድ የስፖርት ፌደሬሽን ዝግጅት ላይ ወይስ በአንድ የኢህአዴግ ስብሰባ ላይ በማለት እስክንጠይቅ ድረስ ወጣቶቹ መድረክ መሪዎች "ስለ መለስ››ከኢህአዴግ በላይ ነግረውናል፡፡

የሲቲ ካፑ "ለመለስ መታሰቢያ እንዲደረግ መታቀዱ ላይ ችግር የለብኝም፣ የምሽቱ የዕጣ ስነ ስርዓት ለመለስ የህሊና ፀሎት በማድረግ መጀመሩም አይሰነፍጠኝም፡፡ ነገር ግን ጥያቄዬ የሚነሳው ስፖርቱን በካድሬዎች በመምራት የተፈጠረበትን አላማ እንዲስት እየተደረገ መሆኑ ነው፡፡ የስፖርት ፌደሬሽኖች የተመሰረቱበት ህገ ደንብ እንደሚናገረው ከየትኛውም የሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከት ነፃ ሆነው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን መንግስት የተቋማቱን ነፃነት በግልጽ የሚጋፉ ነገሮችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ አልያም በስፖርት ተቋማት ውስጥ የተሰገሰጉ ካድሬዎች ስፖርቱን ለፖለቲካ ትርፍ ሊጠቀሙበት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በውድድር መድረኮች፣ ክለቦችና የስፖርት አመራሮች በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች እግር ጥሎት የመሳተፍ ዕድል ካገኙ የሆነ የፖለቲካ ስብሰባ ላይ እንደተገኙ ሊሰማዎ ይችላል፡፡ ገዢው ፓርቲ የጠቅላይነት ሚናውን በተለያዩ ተቋማት እንዳሰረገ ሁሉ ስፖርቱን እንደ አንድ የራሱ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት እየቀረጸው ይገኛል፡፡

እርግጥ ነው ስፖርታችን አሁን ካለበት ደረጃ በመነሳት ማደግ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ስፖርተኞቹን ጨምሮ የመንግስትና የህዝብ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል፡፡ ነገር ግን መንግስት ለስፖርቱ ድጋፍ የሚያደርገው ተቋሙን የፖለቲካው ማራመጃ በማድረግ አይደለም፡፡ በዚህች አገር በገዢው ፓርቲና በመንግስት መካከል ልዩነት ባለመደረጉ ገዢው ፓርቲ እንደ መንግስት በሚሰራቸው ስራዎች የውለታ ምላሽ ይጠብቃል፡፡ በስፖርት አመራር ላይ የሚገኙ ሰዎችም ለገዢው ፓርቲ ሳይዘምሩ በጀት እንደማያገኙ ስለሚያስቡ በየመድረኮቻቸው ለገዢው ፓርቲ መወድስ ያቀርባሉ፡፡ አበው "ከጳጳሱ በላይ ምዕመኑ" እንደሚሉት የፌደሬሽኑ ሰዎች ከገዢው ፓርቲ በላይ ስለ መለስ ብፅእና ሊሰብኩን ይፈልጋሉ፡፡

እውነት እንነጋገር ከተባለ ላለፉት 21 ዓመታት ኢትዮጵያን የገዙት መለስ ዜናዊ የስፖርት አመራሮቻችንና አፈ ቀላጤዎቻቸው የሚሉንን ያህል ሳይሆን ለስፖርቱ ያበረከቱት አስተዋፅኦ በዜሮ የሚባዛ ነው፡፡ አትሌቶች አሸንፈው ሲመጡ እኮ አፄ ኃይለ ሥላሴና መንግስቱ ኃ/ማርያም በቤተመንግስታቸው ተቀብለው እራት አብልተው በወቅቱ ተገቢ ነው ያሉትን ሽልማት ያበረክቱ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር መለስ ከቀደሙት ገዢዎቻችን ያደረጉት የተለየ ነገር ምንድን ነው?

በአንጻሩ በመለስ ዘመን በተለይ በአዲስ አበባ የነበሩ የመጫወቻ ሜዳዎች ለግለሰቦች እየተሰጡ የህንፃ ማረፊያዎች ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንና ለአገራችን ታላላቅ ክለቦች ባለተሰጥኦ ታዳጊዎች በማፍራቱ ይታወቅ የነበረው የመሳለሚያው ኳስ ሜዳ ህንፃ እንዲገተርበት ተደርጓል፡፡ የትምህርት ቤት ሜዳዎች በተመሳሳይ መልኩ ቤቶች ተገንብተውባቸዋል፡፡ ልጆቻችን የት ይጫወቱ ? ለሚለው የወላጆች ጥያቄ ጆሮውን በጥጥ ደፍኖ የቆየ መሪን ለስፖርቱ እድገት የተጋ በማለት ማንቆለጳጰስ ራስን ግምት ውስጥ ከመክተት አይተናነስም፡፡

መንግስት የአምስት አመቱን የትራንስፎርሜሽን እቅድ በመንደፍ እየተንቀሳቀስኩ ነው በማለት በሚያስተዳድረው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት እየለፈፈ ይገኛል፡፡ ከእቅዱ ይፋ መሆን ጀምሮም የ ኢ ት ዮ ጵ ያ መንገዶች በሙሉ ወደዚህ እንዲያመሩ እየተደረጉ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ከላይ ወደታች የሚሰራ በመሆኑም ወንበሩ ላይ የተቀመጡ ቱባ ባለስልጣናት የተናገሩትን ነገር ሳይቀንስና ሳይጨምር እንደ መዝሙረ ዳዊት መድገም የካድሬዎች ስራ ሆኗል፡፡ ነገር ግን የስፖርቱ አመራሮች ይህንኑ እንደ በቀቀን በየመድረኮቻቸው ሲደግሙልን መመልከት አስተዛዛቢና የተቋቋሙበትን ስፖርታዊ መርህ መከተል ስለመቻላቸው እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡

የስፖርት ፌደሬሽኖቻችን በፖለቲካና በስፖርት መካከል ሊኖር የሚገባውን የልዩነት መስመር መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ስፖርቱ የገዢውን ፓርቲ ተቃዋሚ፣ ደጋፊውንና የተለየ ሃይማኖት ያለውን በሙሉ በእኩልነት የሚያስተናግድ መሆን ይገባዋል፡፡ መለስ ዲሞክራት ነበሩ የሚል ትንተና መስጠት በየትኛውም መመዘኛ ለስፖርት ፌደሬሽኖቻችን የሚመጥን አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በመለስ አምባገነንነት የሚያምኑ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያዊያን በስፖርቱ ልዩነቶቻቸውን በመርሳት መዝናናት ይፈልጋሉና፡፡

ኢህአዴግ ለነፃ ተቋማት መኖር ታግያለሁ ያላለንን ያህል አሁን የተቋማቱን ነፃነት በመግፈፍ ሎሌዎቹ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡ በፕሮፌሽናቸው አምነው ሳይሆን በተለየ መሳሳብ ወደ ተቋማቱ አመራርነት የሚመጡ ሰዎችም ቀድሞውኑ በቋፍ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው እምቢ ለማለት ይቸገራሉ፡፡ የሸራተኑን የአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌደሬሽን የዕጣ አወጣጥ ስነ ስርዓትን በመድረክ መሪነት ካገለገሉ ሁለት ወጣቶች አንዱን ከጳጳሱ በላይ ክርስቲያን ስለሆነበት ምክንያት ጠይቄው ነበር "በመድረክ ላይ የተናገርኩት ነገር በሙሉ ተጽፎ የተሰጠኝ ነው፡፡ ደግሞም በእንጀራዬ ላይ ለመቆየት የተባልኩትን መፈጸም ይኖርብኛል፡፡" ብሎኝ ነበር፡፡ ሰዎቻችን ህሊናቸውን በመዘጋት በሆዳቸው ለሆዳቸው መኖር ከጀመሩ ሰንብተዋል፡፡ ነገር ግን መንግስት የስፖርት ተቋማትን ነፃ ማድረግ ይገባዋል፡፡ አመራሮቹም ለመጣው ሁሉ ከማጎብደድ ይልቅ የተቋሙን ነፃነት ማስከበር መቻላቸውን ከምንም ነገር በላይ ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የኢትዩጵያ ብሄራዊ ቡድን ከ31 ዓመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ በተፈጠረለት የተለየ አጋጣሚ በመጠቀም ማለፉን ተከትሎ እየሰማናቸው የምንገኛቸው ነገሮች የእግር ኳስ ፌዴሬሽኑንና በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኘውን ሚዲያ እንድንታዘብ አድርጎናል፡፡ በሁሉም መልካም ነገር ስሙ እንዲጠራ የሚፈልገው ገዢ ግንባር የብሄራዊ ቡድናችንን ስኬት የትራንስፎርሜሽኑ አካል በማድረግ እየተረከልን ነው፡፡ለኢትዩጵያ እግር ኳስ ባለፉት 21 ዓመታት ምንም አይነት አስተዋእጾ አበርክተው የማያውቁት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ቡድኑ እዚህ እንዲደርስ እንደረዳ መሪ ውዳሴ ሲደረደርላቸው መስማት በስፖርቱ ዙሪያ ሲሰሩ የቆዩ ሰዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክብር ከመንፈግ ተለይቶ አይታይም፡፡ለስፖርት ሚዲያውም ሆነ ለፌዴሬሽኑ የሚጠቅመው ነገር እወደድ ባይነት ሳይሆን እውነታውን በመንገር ስፖርቱ የሁሉንም ርብርብ ማግኘት የሚችል ከሆነ የተሻለ ነገር ማግኘት እንደሚቻል ነው፡፡ነገር ግን በባዶ ሜዳ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መሞከር ለአገር እንደ አገር አለማሰብ ነው፡፡